አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3560 | ቅዳሜ የካቲት 7 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# እየተጠናከረ የመጣው አጋርነት

"የማቴ እቅድ ኢትዮጵያ ቅድሚያ ሰጥታ ከምትሰራባቸው ዘርፎች ጋር የተጣጣመ ነው"

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

5




ፎቶ- ከገፀ ድር

ሁለተኛው የጣሊያን-አፍሪካ ጉባዔ ትላንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል

## የአዲስ አበባ አዲስ መልክ

16



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

ሜክሲኮ አካባቢ የመንገድ ፅዳት ስራ ሲከናወን

## የፕላስቲክ ከረጢት እገዳና የአዋጁ ትግበራ

24



ፎቶ- ከገፀ ድር

ፌስታል አለመጠቀም የአካባቢን ስነ ምህዳር ከመጠበቅ አንፃር ትልቅ አበርክቶ አለው

## የአንድነት መዝሙር - የነፃነት ዜማ

19



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአፍሪካ ህብረት የአንድነትና የነፃነት ምልክትነት ከሚያሳዩት መካከል የህብረቱ መዝሙር ተጠቃሽ ነው



ፎቶ- ከፋይል

የዓድዋ ድል መታሰቢያ የአፍሪካውያን ድል የሆነውን ዓድዋ ለትውልድ የሚያሸጋግር የታሪክ መነጽር ነው

# የአፍሪካውያን ድል መታሰቢያ

በስንታየሁ ምትኩ

ካዎቼ ካውንዳ የቀድሞ የዛምቢያ መሪ ኬነት ካውንዳ ልጅ ናቸው። አባታቸው ኬኔት ካውንዳ የአፍሪካ ህብረት (የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት) መስራች አባቶች ከሚባሉት መካከል አንዱ ናቸው። ከአንድ ወር በፊት የዓድዋ ድል መታሰቢያን ሲጎበኙ የአባታቸው ፎቶ ከሚገኝበት የሙዚየሙ ክፍል ሆነው፣ "አባቶቻችን አፍሪካን አንድ የማድረግ ሀሳብ ይዘው በመስራት አሳክተዋል። አሁን ያለነው ልጆቻቸው የእነሱን ህልም ማስቀጠል ካልቻልን፤ አፍሪካን ነፃና አንድ የማድረግ ህልም ከእነሱ ጋር አብሮ ይሞታል፡፡ እነሱ የለኮሱትን ችቦ ይዘን ወደፊት መሄድ አለብን፡፡" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል




# ቀጣዩ ምርጫና የፓርቲዎች ሚና

- ለምርጫው ስኬታማነት የበኩላቸውን እንደሚወጡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገልጸዋል

በመለሰ ተሰጋ

ምርጫ የፖለቲካ መረጋጋትና የሥልጣን ቅቡልነትን የሚወስን ቁልፍ ሥርዓት ነው፡፡ የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫ እና የዴሞክራሲያዊነት አንዱ መለኪያ እንደሆነም ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያ አቶ አህመድ ሰይድ ይናገራሉ፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፣ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ብዝሃነት፣ ዘመን ያስቆጠረ የሀገረ መንግስትነት

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀፅ



## የአዲስ አበባ የልማት ስኬቶች የአፍሪካ መዲናነትን ከፍታ የሚያጠናክሩ ናቸው!

አዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት እያስተናገደቻቸው ያሉት በርካታ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ጉባኤዎች እንዲሁ የተገኙ ሳይሆኑ፣ ከተማዋ ስሟን የሚመጥን ግዙፍ የልማት ስራዎችን በማከናወኗ የተገኙ የድካም ውጤቶች ናቸው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያስመዘገበቻቸው ስኬቶች የዲፕሎማሲ መዳረሻነቷ እንዲያብብ፣ ለዓለም እና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች ተመራጭ እንድትሆን አድርጓታል። በተለይም ሰሞኑን የተካሄደው 2ኛው የኢጣሊያ-አፍሪካ ጉባኤ እና 39ኛው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እንዲሁም ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ የተስተናገዱት ከ150 በላይ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች አዲስ አበባ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁነቶች ያላትን ዝግጁነት በተግባር ያረጋገጡ ናቸው። ይህ ዝግጁነት የአፍሪካ መዲናነቷን ከፍታ በሚያጠናክሩት የልማት ስራዎቿ የተገኘ ነው፡፡

የከተማዋን ገፅታ የቀየሩና ለነዋሪዎቿም ሆነ ለእንግዶች ምቹ ሁኔታን የፈጠሩት የኮሪደር ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማትና ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶች መዲናዋን የአፍሪካ ኩራት አድርገዋታል። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ "አዲስ አበባን ለአህጉሪቱና ለዓለም ተምሳሌት ለማድረግ የጀመርነው የልማት ጉዞ፣ ዛሬ እንግዶቻችንን በኩራት የምንቀበልባትና የኢትዮጵያን ብልጽግና የምናሳይባት ከተማ እንድትሆን አስችሏታል፤ የሰራናቸው ስራዎች ሁሉ የከተማዋን ክብርና የዲፕሎማሲ ከፍታ ለመመለስ ያለሙ ናቸው" ማለታቸው ይታወሳል። ይህ ንግግር ከተማዋ ያከናወነቻቸው ስራዎች ለስብሰባዎች የሚመጡ እንግዶች ልዩ ምቾትና ደህንነት እንዲሰማቸው በማድረግ ረገድ ያላቸውን ሚና ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ወቅት የነበራት ታሪካዊና ግንባር ቀደም ሚና ዛሬም ድረስ በአዲስ መልክ እየታደሰ ይገኛል። ይህንን የአፍሪካዊነት ኩራትና የነፃነት ተጋድሎ ወካይ አድርጎ የተገነባው የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ አዲስ አበባ ለአህጉሪቱ ያላትን ተምሳሌትነት ዳግም አብስሯል። መታሰቢያው የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ምልክት ከመሆኑም ባለፈ፣ ለከተማዋ አዲስ የቱሪስት መስህብና የዲፕሎማሲ ጥንካሬ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። ለስብሰባ የሚመጡ መሪዎችና እንግዶች የሚሰጡት ምስክርነትም ከተማዋ በውበትና በፅዳት ብቻ ሳይሆን በታሪካዊ እሴቶቿም ጭምር ተምሳሌት እየሆነች መምጣቷን የሚያረጋግጥ ነው።

የኮሪደር ልማት ስራዎች መዲናዋን ከነበረችበት የተጎሳቆለ ገፅታ አውጥተው ወደ ዘመናዊና ስልጡን ከተማነት ቀይረዋታል። ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች፣ የብስክሌት መስመሮች፣ አረንጓዴ ስፍራዎችና ማራኪ የብርሃን ስራዎች በነፃነትና በደስታ ለመንቀሳቀስ የሚያስችሉ ናቸው። እነዚህ የልማት ውጤቶች ለስብሰባ የሚመጣባት ብቻም ሳይሆን የሚዝናኑባት፣ የሚዘዋወሩባትና የአፍሪካን ብልጽግና በተግባር የሚመለከቱባት ማሳያ አድርጓታል። ይህም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ትልቅ አቅም ፈጥሯል።

በአጠቃላይ አዲስ አበባ ዛሬ ላይ የደረሰችበት የዲፕሎማሲ ከፍታ የልፋትና የቆራጥ አመራር ውጤት ነው። ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለእንግዶቿ ደግሞ ሳቢ የማድረጉ ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉ አህጉራዊ ተቀባይነቷን ይበልጥ ያሳድገዋል። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ህብረት ምስረታና ለጥቁር ህዝቦች ነፃነት የነበራትን አስተዋፅኦ አሁን ባለው የልማት ስራ በማጀብ፣ አዲስ አበባን የአፍሪካ የተስፋ ብርሃንነቷን በተግባር ማስመስከር ችላለች። ይህ ጉዞ ለቀጣይ ትውልድ የሚተርፍ ታላቅ የታሪክ አሻራ ሆኖ በደመቀ ሁኔታ የሚመዘገብ እና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው።

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ከመሶብ አገልግሎት ልንማር የሚገባው

**በሳሮን ከጊዮርጊስ**

"ደንበኛ ንጉስ ነው" የሚለውን በተግባር መተርጎም ያስፈልጋል። ይህን እንድል ያነሳሳኝ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ባልተገባ መንገድ የሚፈጥሩት ክፍተት ለተገልጋይ እንግልት፣ ለተቋም እድገትም ሆነ ለውጥ እንቅፋት መሆናቸውን በመመልከቴ ነው፡፡ አገልጋይ ተገልጋይም እንደሆነ ትኩረት የማይሰጡ በየደረጃው ከመኖራቸው በተጨማሪ በራሳቸው ስህተት ምክንያት የመረጃ መዘበራረቅ፣ የተሳሳተ አሰራር ሲገጥም እንኳን ይቅርታ የማይሉ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡ ባለጉዳይ ቆሞ አገልግሎት እየፈለገ ወይም ለማግኘት እየጠበቀ በተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ስለግል ጉዳያቸው ያወራሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን ስላደረጉ ማካካሻ ይሆን ዘንድ ከመውጫ ሰዓታቸው መሸረፍ አይፈልጉም፡፡

በቅርቡ ካጋጠሙኝ ጉዳዮች አንዱን ባነሳ ወደድኩ፡፡ ለአገልግሎት በሄድኩበት ተቋም መስተናገድ እየቻልኩ ባለሙያዋ በግላዊ ጉዳይ ስክል ላይ ጊዜ ስላጠፋች የምሳ ሰዓት ደርሷል የሚል ምክንያት በመስጠት ከሰዓት እንድመለስ ነግራኝ ቢሮውን ለቃ ወጣች፡፡ መመለስ እንደማልችል እና እንድትተባበረኝ ብጠይቃትም ለማዳመጥም ሆነ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡

ለምሳሌ ያህል በቅርብ የገጠመኝን አንኳን ጉዳይ አነሳሁ እንጂ በስራ ሰዓት የግል ስልክን ለራስ ጉዳይ በመጠቀም የስራ ሰዓትን ያለአግባብ ማሳለፍ በየተቋማቱ ይስተዋላል፡፡ በእርግጥ የተለያዩ የግል ጉዳዮች ይገጥማሉ፤ የሞባይል አንዱም ጠቀሜታው ባሉበት ሆኖ የሚገጥሙንን ጉዳዮች (ችግሮች) መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን አንገብጋቢ ባልሆኑ ጉዳዮች ተገልጋይን በሚያጉላላ መልኩ ሊሆን አይገባም፡፡

ይህ ግን የሁሉም አገልጋይ መገለጫ አይደለም፡፡ መሰል የስልክ ጥሪ ሲገጥማቸው በአጭሩ አውርተው ወደ አገልግሎታቸው በቶሎ የሚመለሱ አሉ፡፡ ይህ ራስን ያስመሰግናል፤ ተቋምንም በበጎ እንዲነሳ ያደርጋል፡፡

ከላይ የጠቀስኩትን ችግር የሚቀርፍ አሰራር ወደዘረጋ አንድ ተቋም በቅርቡ ለአገልግሎት ሄድኩ፤ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት። ማዕከሉ በአንድ ጣራ ስር የተለያዩ የመንግስት አገልግሎቶችን በማጣመርና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚሰጥ ነው። የማዕከሉ አገልግሎት ካስደነቀኝ አንዱ ፈጣን አገልግሎታቸው ነው። ጉዳዬን እስክጨርስ ድረስ የተመለከትኩት ሁሉም በሚባል ደረጃ አገልግሎት ሰጪዎች በእጃቸው ላይ ተንቀሳቃሽ ስልክ አለመጠቀማቸው ነበር፡፡ ትኩረታቸው ተገልጋይ ላይ ብቻ ነው፡፡ ወደ ማዕከሉ ሲገባ ጀምሮ የአገልግሎት ሰጪዎቹ መልካም አቀባበል ሙያን ያከበረ ተግባር ነው። በመገልገል ላይ እያለሁ በማየው ነገር ተደንቄ አንዱን አገልግሎት ሰጪ የጠየኩት ጥያቄ "ሞባይል በእጃቸው ላይ እንዳይኖር ለምን ተደረገ" የሚል ነበር፡፡ በሰጠኝ ምላሽም እያንዳንዱ አገልጋይ ወደ ስራ ሲገባ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) አስቀምጦ ስራ እንደሚጀምር፣ በስራ ሰዓት ትኩረቱ ተገልጋዩ እንደሆነ እና በዚህም ውጤታማ መሆን እንደተቻለ አብራርቶልኛል፡፡ በውስጤ ይህ ተሞክሮ ለሁሉም ቢዳረስ ተመኘሁ፡፡

የሄድኩበትንም ጉዳይ ያለምንም ጊዜ መፍጀት እና መጉላላት ልጨርስ ቻልኩ። "ሆድ ይመርቅ" የሚል ሀገርኛ ብሂል አለ፡፡ እኔም ይህን አልኩ። ነገር ግን በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ዜጎቻችን ላይ ምሬት የሚፈጥሩ አሰራሮችን ፈትሾ ማስተካከል ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ሆኖ ለዚህ ቁርጠኝነታቸን አንዱ ማሳያ የሆነውን መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማስፋት ላይ በትኩረት ሊሰራ ይገባል እላለሁ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች**

**ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ**

**ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ዓዴ
አብርሃም ገብሬ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንትና የዋና ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ ትውልድ ፓርቲ (አትፓ) ፕሬዝዳንት አቶ ሰለሞን ታፈሰ




ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እዩኤል ሰለሞን

## ቀጣዩ ... ከገጽ 1 የዞረ

ታሪክ እና ብዙ ህዝብ እንዲሁም ፍላጎት ባለባቸው ሀገራት አሳታፊ፣ ሰላማዊና ፍትሐዊ ምርጫ ማድረግ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው፡፡

ባለሙያው አክለውም፣ ኢትዮጵያ ሰፊ የማደግ ተስፋና አቅም አላት፡፡ ይህንን ዕድል በአግባቡ ተጠቅሞ የሀገርን ሁለንተናዊ ከፍታ ለማስቀጠል ደግሞ በሀገሪቱ የሚደረጉ ምርጫዎች አሳታፊ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆነው እንዲጠናቀቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ከፍ ያለ ነው ብለዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ስልጡን ተወዳዳሪ ሆነው በመቅረብ፣ ያላቸውን አማራጭ ሀሳብ ለመራጩ ህዝብ በማቅረብ፣ ስለ ምርጫ ሕግ አባላቶቻቸውም ሆኑ ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው በማንቃትና የስልጣን ባለቤት የሆነው መራጩ ህዝብ በካርዱ የሰጣቸውን ድምፅ በጸጋ በመቀበል፣ ለሀገር ሰላምና ዕድገት ከአሸነፈውም ሆነ ከተሸናፊው ፓርቲ ጋር አብሮ በመስራት ለህዝብና ለሀገር፤ ለእውነትና ለዴሞክራሲ መቆማቸውን ሊያስመሰክሩ ይገባል ብለዋል አቶ አህመድ ሰይድ፡፡

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ካደረጉ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች መካከል የአዲስ ትውልድ ፓርቲ (አትፓ) ፕሬዝዳንት አቶ ሰለሞን ታፈሰ እንደሚሉት፣ ምርጫን የሚያደርጉ ሀገራት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሀገራቸው እውን እንዲሆን የሚፈልጉ ናቸው፡፡

ይህንንም ተከትሎ ኢትዮጵያ 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ ለማድረግ ጥቂት ጊዜያት ቀርተዋታል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የክልልም ሆነ የፌዴራል መንግስታት ለምርጫው ፍትሐዊነት፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊነት ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

በሌላ በኩል ግን እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ እንደሀገር የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለአብነትም ፓርቲዎች እንዳለፉት ምርጫዎች ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል መሄድ ሳይጠበቅባቸው እጩዎቻቸውን ቢሯቸው ተቀምጠው በዲጂታል መንገድ መመዝገብ የሚችሉበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡ ይህም ቀደም ሲል የነበረውን መንከራተትና ተያያዥ ችግር መቅረፍ ችሏል ብለዋል፡፡

ከምንም በላይ ሀገር ይቀድማልና ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የበኩላችንን እንወጣለን ያሉት አቶ ሰለሞን፣ ለዚህም አባላቶቻችን እና ደጋፊዎቻችንም በምርጫው ሕግ መሰረት ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን እንዲጠቀሙ እንሰራለን፡፡ እንደ ፓርቲም የስልጣን ባለቤት የሆነው ህዝብ የሰጠንን ውጤት በጸጋ እንቀበላለን ብለዋል፡፡

አቶ ሰለሞን አክለውም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ መንግስትና የጸጥታ አካላት እንዲሁም የስልጣን ባለቤት የሆነው ህዝብ ቅድሚያ ለሀገር ሰላምና ከፍታ ቦታ በመስጠት ምርጫው አሳታፊ፣ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ መስራት እንዳለባቸውም አመላክተዋል፡፡

እንደ ፓርቲ የሀገራችንን ሕግና ደንብ አክብረን ወደ ምርጫ ገብተናል ያሉት የፓርቲው ፕሬዝዳንት፣ ወደ ምርጫ ሲገቡም ለምርጫው ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ እጩዎችን መልምለው በምዝገባ ላይ እንደሆኑም ጠቅሰዋል፡፡

በዚህ ሂደትም ተወዳዳሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎቻቸው የምርጫ ሕጉን አክብረው እና መራጩ ህዝብ የሚሰጣቸውን ውጤት በጸጋ ለመቀበል የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ ፓርቲ ከአመራር ጀምሮ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመው፣ በቀጣይም ከአባላቶቻቸው ጋር መሰል የግንዛቤ ስራዎች እንደሚከናወኑና ሀገርን ያስቀደመ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እዩኤል ሰለሞን በበኩላቸው፣ ምርጫው አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱ ተቋማት አሉ፡፡ ይህንንም ተከትሎ በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርሻ አማራጭ ሀሳባቸውን ማቅረብ፣ ይህንን አማራጭ ሀሳብ ማስፈጸም የሚችል አመራር ማፍራት በምርጫ ሰዓትም መሳተፍ ነው፡፡ ምርጫው አሳታፊና ዴሞክራሲ እንዲሆን እንደ አንድ ሰላማዊ የፖለቲካ ፓርቲ በየትኛውም ሁኔታ ምርጫውን ከሚረብሽ አሉታዊ ከሆነ ድርጊት የመቆጠብ ኃላፊነት አለብንም ብለዋል፡፡

ኢዜማ ከተመሰረተ ጀምሮ ይህ ሁለተኛ የምርጫ ተሳትፎው መሆኑን ያስታወሱት የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እዩኤል፣ በመሆኑም እንደ ፓርቲ ሀገሪቱ ያስቀመጠቻቸውን ሕጎች ማክበር ግዴታ እንዳለብን እናምናለን፤ ይህንንም ለአባላቶቻችን በበቂ ሁኔታ አሰልጥነናል፤ በምርጫ ወቅት ልንከተላቸው የሚገቡ ሂደቶችን የተመለከቱ ማንዋሎችንም አዘጋጅተናል ሲሉ አክለዋል፡፡

በተለይም በምርጫ ወቅት ማህበራዊ ትስስር ገጾችን እንዴት መጠቀም አለብን? የሚለውን ጨምሮ የተለያዩ ጠቃሚ ማንዋሎችን በማዘጋጀት አባላት ስርዓት ባለው መልኩ መብታቸውን እንዲጠቀሙና ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስችል ተግባራትን እያከናወኑ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

ፓርቲው በሰላማዊና በሕግ አግባብ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቅሰው፣ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ እንደ ሰለጠነ ፖለቲካ የመፎካከር ዓላማን እንይዛለን፡፡ ፓርቲዎችም ምርጫ ግለሰባዊ ጠብ ሳይሆን የሀሳብ ልዩነት መሆኑን በመረዳት መንቀሳቀስ እንዳለባቸውም ጠቁመዋል፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንትና የዋና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ በበኩላቸው የ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የፓርቲው ማኒፌስቶ ትናንትን በማከም፣ ዛሬን በሚገባ መጠቀምና መተለም ማዕከል ያደረገ ነው ብለዋል፡፡

በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ፉክክርና ትብብር ሚዛን እንዲጠበቅ በግንባር ቀደምትነት እንደሚንቀሳቀሱ የገለጹት አቶ አደም፣ በዚህ መሰረትም 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ በሀገራችን

> “የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ መንግስትና የጸጥታ አካላት እንዲሁም የስልጣን ባለቤት የሆነው ህዝብ ቅድሚያ ለሀገር ሰላምና ከፍታ ቦታ በመስጠት ምርጫው አሳታፊ፣ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ መስራት አለባቸው”

ዴሞክራሲን የምናጸናበት እንዲሆን በቁርጠኝነት እንሰራለንም ብለዋል፡፡

ትልማችን የፖለቲካ ምህዳሩን ይበልጥ ጤናማና ለትብብር የሚመች ማድረግ፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሀሳብ የሚፎካከሩበት እና የህዝብ ድምፅ ብቻ የስልጣን ምንጭ የሚሆንባት ኢትዮጵያን ማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳትም በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ብልፅግና ፓርቲ ሁለት ዋና ዋና ግቦችን ለማሳካት ይሰራል ያሉት የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንትና የዋና ጽህፈት ቤት ኃላፊው፣ የመጀመሪያው ምርጫውን ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሐዊ እና ተአማኒ በሆነ መልኩ ማከናወን ሲሆን፣ ይህም እንደ ፓርቲ መርህን፣ ሕግን እና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በማክበርና በመተባበር ለስኬታማነቱ በቁርጠኝነት የምንታገልለት፣ በሁሉም ፖለቲካ ተዋንያን እና በህዝባችን ትብብር የምናሳካው እና በኢትዮጵያ መትከል የጀመርነውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን የምናሳካበት ወሳኝ ግብ ነው ብለዋል፡፡

ሁለተኛው ግብ ምርጫውን በህዝብ ይሁንታ በማሸነፍ ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር ማሸጋገር ነው፡፡ ለዚህም ፓርቲው በተግባር ተፈትሾ ብቃቱን ያስመሰከረ ቢሆንም በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ለአሸናፊነት ለመብቃት በሀሳብ፣ በስትራቴጂ፣ በአሰራርና በአደረጃጀት ዝግጅቱን ያጠናቀቀ መሆኑን ባሳለፍነው ረቡዕ በብልፅግና ፓርቲ የ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ማኒፌስቶ እና የምርጫ ምልክት ይፉ ማድረጊያ መርሃ ግብር ላይ ባስተላለፉት መልዕክት አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው በሰጡት ማብራሪያ፣ የዘንድሮው ምርጫ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ልምዶች በተሻለ መልኩ ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና አካታች እንዲሆን መንግሥት በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው መራጮች ለምርጫው እንደ ጡብ፣ ተሳታፊ ፓርቲዎች ደግሞ እንደ ማገር ናቸው በሚል የገለጹ ሲሆን፤ የምርጫ አውዱን ለማስፋት ልዩ ትኩረት እንደተሰጠም መናገራቸው ይታወሳል፡፡

# የማታንቀላፋ መዲና

**“ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን አብዝቶ የሚያስተናግድ ሀገር፣ በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲና ኢኮኖሚ መድረክ ተሰሚነቱ ይጨምራል”**

**የምጣኔ ሀብት መምህር ጉቱ ቴሶ (ዶ/ር)**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት የሩዋንዳዋ ዋና ከተማ ኪጋሊ ማታ ላይ ጭልጭል የሚሉ መብራቶች ብቻ የሚታዩባት፣ የፀጥታ ስጋት የነበረባትና እንቅስቃሴ የተገታባት ከተማ ነበረች። መሪዎቿ ግን ‘ባለ 24 ሰዓት ከተማ’ (24-Hour City) የመሆን ራዕይ ሰነቁ። ከተማዋን በዘመናዊ የጎዳና መብራቶች አጥለቅልቀው አስፈላጊውን መሰረተ ልማት ሲያሟሉላት የምሽት የንግድ ስራዋ መሟሟቅ ጀመረ፤ እርምጃው በዓለም አቀፍ ደረጃ ኪጋሊን በደህንነቷ ቀዳሚ አደረጋት፤ የከተማዋ ነዋሪዎችና እንግዶች እኩለ ሌሊት ላይ በእግር እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል ‘የመተማመን ስነ-ልቦና’ አላበሳት።

ኪጋሊ የምሽት አገልግሎቷን በማራዘሟ ያገኘችው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እጅግ ከፍተኛ ነው። የምሽት አገልግሎት መጀመሩ በቀን የሚሰሩት እንደተጠበቁ ሆነው፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በምሽቱ ክፍለ ጊዜ በሆቴሎች፣ በፋርማሲዎች፣ በትራንስፖርት እና በሱቆች እንዲቀጠሩ አድርጓል።

የ‘ኪጋሊ የ2050 መሪ ፕላን’ (Kigali Master Plan 2050) ሰነድ ላይ እንደተብራራው፣ ነጋዴዎች ቀደም ብለው ሱቆቻቸውን እስከ ምሽቱ 6 እና 7 ሰዓት ድረስ ሳይዘጉ በማቆየታቸው የሽያጭ መጠናቸውን ከ20 በመቶ እስከ 30 በመቶ ድረስ አሳድገዋል። በቀን ብቻ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ መንገዶችና ህንጻዎች፣ በሌሊትም ጭምር አገልግሎት በመስጠታቸው ለከተማዋ የንግድና የኢንቨስትመንት ስራ መስፋፋት ምክንያት ሆነዋል።

ዛሬ ላይ ኪጋሊ በአፍሪካ የ‘ማይስ ቱሪዝም’ (MICE፡- Meetings, Incentives, Conferences, and Exhibitions) ማዕከል ከሆኑ ከተሞች መካከል ተጠቃሽ ሆናለች። ይህስኬት ከምሽት የንግድ እንቅስቃሴዋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሲሆን፣ አንድ የዓለም አቀፍ ስብሰባ ተሳታፊ ቀኑን ሙሉ አዳራሽ ውስጥ ውሎ ሲወጣ፣ ምሽት ላይ የሚዝናናበት፣ የሚገበያይበትና የከተማዋን ባህል የሚቃኝበት አማራጭ ያገኛል። ይህ እንግዶች በከተማዋ የሚቆዩበትን ቀን ያረዝመዋል።

አዲስ አበባም የኮሪደር ልማቱን ተከትሎ የጎዳና ላይ መብራቶችንና ሰፋፊ የእግር መንገድ አማራጮችን በማዘጋጀት፣ ይህንን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ በተግባር እያዋለችው ትገኛለች። አዲስ አበባ ለረጅም ዘመናት ‘ቀን ሰርቶ ማታ የሚተኛባት’ ከተማ ሆና ቆይታለች። ፀሐይ ስትጠልቅ የንግድ ሱቆች በር መዝጊያ ድምፆች ይሰማሉ፤ የከተማዋ እንቅስቃሴም አብሮ ይረግባል። ሆኖም በቅርቡ የተጀመረው የምሽት ንግድና አገልግሎት እንቅስቃሴ ይህንን የታሪክ ምዕራፍ እየቀየረው ነው። ከተማዋ በኮሪደር ልማትና በዘመናዊ መሰረተ ልማቶች ከተዋበች በኋላ፣ ምሽቱ ለተጨማሪ ግብይት፣ ለኢኮኖሚ እድገትና ለከተማዋ ህያውነት አዲስ በር ከፍቷል።



ፎቶ- ከገፀ ድር
አዲስ አበባ በኮሪደር ልማት ስራ ውብ ገፅታን ከመላበሷም በተጨማሪ ለምሽት የንግድ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ ፈጥራለች

ይህን ሀቅ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረን ያነጋገርናቸው ነጋዴዎችም ይመሰክራሉ፡፡

የአፍሪካ ህብረት እና የበርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ በየሳምንቱ በሺዎች የሚቆጠሩ የውጭ እንግዶችን ታስተናግዳለች። ከዚህ ቀደም ስብሰባ ያጠናቀቁ ተሳታፊዎች ከምሽቱ 2 ሰዓት በኋላ የሚንቀሳቀሱባቸው እና የሚገበያዩባቸው ቦታዎች ውስን ነበሩ። አሁን ግን አንድ ዲፕሎማት ወይም የ‘ቢዝነስ’ እንግዳ ቀን ስብሰባውን አጠናቅቆ፣ ምሽት ላይ በነፃነት ወጥቶ የኢትዮጵያን ባህላዊ ምርቶች፣ አልባሳት እና ቅርሳቅርስ መገበያየት እንዲችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። ለዚህም የዝግጅት ክፍላችን ተዘዋውሮ የተመለከታቸው የሾሮ ሜዳ፣ ሳር ቤት፣ አራት ኪሎ፣ ፒያሳ እና መሰል አካባቢዎችን በእማኝነት መጥቀስ በቂ ነው፡፡

አዲስ አበባ ዛሬ ከእንቅልፏ ነቅታለች፤ በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት የከተማዋ የደም ሥሮች የታደሱ ይመስላሉ። በሌሊት ብርሃን የሚደምቁ አዳዲስ አስፋልቶች፣ እንደ መስታወት የሚያብረቀርቁ የእግረኛ መንገዶችና ያለገደብ የሚንቀሳቀሱ ነዋሪዎች ከተማዋን “የምስራቅ አፍሪካ ዱባይ እያደረጓት ነው” የሚሉ አስተያየቶችም ተዘውትረው ይሰነዘራሉ፡፡

አሁን አዲስ አበባ በርካታ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን የማስተናገድ አቅም ፈጥራለች፤ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለከተማዋ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ጉባዔ ባቀረቡት የ2018 ዓ.ም የመጀመሪያው 6 ወራት አፈፃፀም ሪፖርት ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ ከተማዋ ከ150 በላይ ታላላቅ ኮንፈረንሶችን ማስተናገዷን አብራርተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ስብሰባ ያጠናቀቁ እንግዶች በትራንስፖርት ብቻ ይንቀሳቀሱባቸው የነበሩ አካባቢዎች በእግር መጓዝ የሚያስችል ሰፊና ደህንነቱ የተጠበቀ መንገድ ተዘርግቶላቸዋል። ኤድና ሞል እና በአካባቢው ያሉ የገበያ ማዕከላት እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ክፍት በመሆናቸው፣ ዲፕሎማቶች እና ቱሪስቶች በነፃነት እየተገበያዩ ይገኛሉ። ሳርቤትና ካዛንቺስን የመሳሰሉ አካባቢዎች የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ እንደመሆናቸው፣ ካፌዎቻቸውና ሱፐር ማርኬቶቻቸው 24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን በቅኝታችን ወቅት አረጋግጠናል።

ድሮ ፒያሳ ማታ ላይ ጭልጭል የምትልና እንቅስቃሴ የሚገታባት ነበረች። ዛሬ ግን በአዳዲስ መብራቶች ደምቃለች። ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ የሚያቀናው መንገድ ለምሽት የእግር ጉዞና ለግብይት ምቹ ሆኗል። አነስተኛ ነጋዴዎችና የቅርስ መሸጫዎች የሥራ ሰዓታቸውን አራዝመዋል፤ ይህም ‘ፒያሳ አትተኛም’ የሚለውን አባባል በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች የስብሰባ ተሳታፊዎች ከስብሰባ በኋላ በቅርብ ርቀት ወጥተው የሚፈልጉትን ዕቃ መሸመት የሚችሉባቸው ‘ሚኒ ሞሎች’ በስፋት እየተከፈቱ ነው። በኮሪደር ልማቱ የተተከሉ አበባዎች፣ ውብ የፏፏቴዎች እና የጥበብ ስራዎች ለገዥውም ሆነ ለሻጩ አዎንታዊ ስነ-ልቦና ፈጥረዋል። በሌላ በኩል ከተማዋ 24 ሰዓት በብርሃን መጥለቅለቋ ነዋሪው ያለ ምንም ስጋት ንብረቱን ይዞ እንዲንቀሳቀስና ግብይት እንዲፈፅም አድርጎታል።

እንደ ቦሌ እና ሲ.ኤም.ሲ አካባቢዎች በሞሎቻቸውና በዘመናዊ መገበያያ ማዕከሎቻቸው ቀድሞውኑ የምሽት እንቅስቃሴ የነበረባቸው ቢሆንም፣ አሁን ግን የኮሪደር ልማቱ ተጨምሮበት ይበልጥ ደምቀዋል። ሜክሲኮና ሳርቤት ደግሞ በዘመናዊ ካፌዎችና ሬስቶራንቶች ልዩ ድምቀትና ድባብ ተላብሰዋል። በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት ለንግድ ምቹ የተደረጉ ሌሎችም የከተማዋ አካባቢዎች ምቹ ሁኔታ በመፍጠራቸው፣ ነጋዴዎች እስከ ምሽቱ 5 እና 6 ሰዓት ድረስ ምርቶቻቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ሰጥቷቸዋል።

እንደ ኤድና ሞል፣ ደምበል፣ ሴንቸሪ ሞልና ሌሎች ታላላቅ የንግድ ማዕከላት የአገልግሎት ሰዓታቸውን ማራዘማቸው ለመዲናዋ ነዋሪዎችም ቢሆን ትልቅ እፎይታ ሰጥተዋል። ቤተሰቦች ከስራ በኋላ ተገናኝተው የሚገበዩበት፣ ህፃናት የሚጫወቱበትና እራት የሚበሉበት ‘የምሽት ባህል’ እየተገነባ ነው። ይህ ደግሞ ለነጋዴዎች የሽያጭ መጠን ስለመጨመሩና ተጨማሪ ሰራተኞችን ለመቅጠር ዕድል መፍጠሩን በአካባቢው ተዘዋውረን ያነጋገርናቸው የንግዱ ማህበረሰብ አባላት አረጋግጠውልናል፡፡

‘ዘ ክሬኤቲቭ ሲቲ’ (The Creative City) የተሰኘ መጽሐፍ ደራሲና ታዋቂ የከተማ ልማት ባለሙያ ቻርልስ ላንድሪ “አንዲት ከተማ 24 ሰዓት ክፍት መሆኗ ከኢኮኖሚው ባለፈ ማህበራዊ ደህንነትን ያረጋግጣል” ይላሉ። ሰፋፊ የእግር መንገዶችና የጎዳና መብራቶች ‘ተፈጥሯዊ ክትትልን’ (Natural Surveillance) እንደሚፈጥርና ብዙ ሰው በጎዳናዎች ላይ በቆዩ ቁጥር ወንጀል የመፈጸም ዕድሉ ይቀንሳል ባይ ናቸው ቻርልስ ላንድሪ።

አዲስ አበባ ከዚህ አንጻር ስትመዘን አሁን ላይ ‘የከተማ ስነ-ልቦናዋ’ የተቀየረ ሲሆን፣ ይህም ለምሽት ንግድ ትልቅ ዋስትና ሆኗል፡፡ የከተማ ልማት ባለሙያው ቻርልስ ላንድሪ፣ የምሽት ንግድ ከተሞችን ሕያው የሚያደርግ፣ ለነዋሪዎች ተጨማሪ የሥራ እድል እና የመዝናኛ አማራጭ የሚፈጥር መሆኑን ይገልጻሉ።

አዲስ አበባ ቀን ብቻ ሳይሆን ማታም የምትሰራ ከተማ መሆኗ ለኢኮኖሚ እድገቷ ወሳኝ ምዕራፍ ስለመሆኑ የምጣኔ ሀብት መምህሩ ጉቱ ቴሶ (ዶ/ር) ይናገራሉ። የምሽት ግብይት መስፋፋት የከተማዋን የኑሮ ዘይቤ ከማዘመኑ ባለፈ፣ ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠርና የንግድ እንቅስቃሴውን በማሳደግ ረገድ የማይተካ ሚና እንዳለው ጠቅሰው፣ ዛሬ በአራቱም አቅጣጫዎች የሚታየው ብርሃንና እንቅስቃሴ፣ አዲስ አበባ ወደ ዓለም አቀፍ የንግድ ከተማነት እየተሸጋገረች መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ብለዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት የምሽት ኢኮኖሚ ማለት ‘የሀብት ብክነትን ማስቀረት ማለት ነው። በቀን ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ መንገዶች፣ ህንጻዎችና መብራቶች ማታም ስራ ላይ ሲውሉ የሀገሪቱን የካፒታል አጠቃቀም ውጤታማ ያደርጉታል። የሽያጭ ሰዓት ከ8 ሰዓት ወደ 16 ወይም 24 ሰዓት ሲያድግ፣ የንግድ ድርጅቶች የምርት ሽግግር (Turnover) ይጨምራል። ይህ ደግሞ ለወጣቶች ‘የምሽት ፈረቃ’ (Night Shift) የስራ እድል በመፍጠር የስራ አጥነትን ችግር ለመቅረፍ ትልቅ አቅም አለው ይላሉ፡፡

ከዓለም አቀፍ ስብሰባዎች አንጻር ከታየም አንድ እንግዳ በቀን ስብሰባ ውሎ ማታ ሆቴል ውስጥ ብቻ መታጠር የለበትም። ማታ ወጥቶ መገበያየቱ፣ የከተማዋን ውበት ማየቱና የባህል ምግቦችን መመገቡ በከተማዋ የሚኖረውን ቆይታ ያራዝመዋል። ይህም ሲሆን የኢንቨስትመንትና የቢዝነስ አማራጮች እንደሚሰፉና የንግድና የገበያ ግንኙነቶችን ለመፍጠር፣ ውል ለመፈራረም፣ ሽያጭና ግዢ ለመጀመር መልካም አጋጣሚዎችን ይፈጥራሉ ይላሉ የምጣኔ ሀብት መምህሩ ጉቱ ቴሶ (ዶ/ር)። ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችንና ዝግጅቶችን አብዝቶ የሚያስተናግድ ሀገር፣ በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲና ኢኮኖሚ መድረክ ተሰሚነቱ ይጨምራልም ይላሉ።

ዩኤን ሀቢታት ይፋ ያደረገው መረጃ አንድ የዓለም አቀፍ ስብሰባ ተሳታፊ በአንድ ከተማ ውስጥ ደህንነቱ ተጠብቆ የምሽት እንቅስቃሴ ካደረገ፣ በከተማዋ የሚያወጣው ገንዘብ በቀን ብቻ ከሚንቀሳቀስ ተጓዥ እንደሚበልጥ ያብራራል። በኮሪደር ልማት ውስጥ የሚካተቱ ሰፋፊ የእግር መንገዶች እና የብስክሌት መስመሮች የምሽት ቱሪዝምን ከፍ ያደርጋሉ።

# እየተጠናከረ የመጣው አጋርነት

**“የማቴ እቅድ ኢትዮጵያ ቅድሚያ ሰጥታ ከምትሰራባቸው ዘርፎች ጋር የተጣጣመ ነው”**

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ከሁለት ዓመት በፊት የ45 የአፍሪካ ሀገራት እና የአፍሪካ ህብረት ተወካዮች በተገኙበት መድረክ የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ በአፍሪካና ጣሊያን መካከል ባለው ግንኙነት አዲስ ምዕራፍ የሚከፍት የልማት ትብብር ይፋ አደረጉ፡፡ በሮም ይፋ የተደረገው የ“ማቴ እቅድ” (Mattei Plan) የተሰኘው ስትራቴጂካዊ ተነሳሽነት ሲሆን ጣሊያንና አፍሪካ መካከል ዘላቂነት ያለው ልማትና ትብብርን የማጠናከር ዓላማ አለው። የማቴ እቅድ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃትን ተከትሎ ጣሊያን ከተለያዩ ሀገራት ጋር በተለይ በሀይል ዘርፍ ያላት ትብብር ፍትሐዊ፣ የነዳጅ አምራች ሀገራትን ጥቅም ከግምት ያስገባ እንዲሆን ቁልፍ ሚና በተጫወቱት ኢነሪኮ ማቴ ከተባሉ ሰው ስያሜውን እንዳገኘ ጂኦፖለቲካል ሞኒተር ዶት ኮም (Geopoliticalmonitor.com) በገፀ-ድሩ ያሰፈረው መረጃ ያመለክታል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

ሁለተኛው የጣሊያን-አፍሪካ ጉባዔ ትላንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል

አፍሪካ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች፣ ሰፊ የሰው ሀይል፣ እምቅ አቅምና ተስፋ ያላት አህጉር ናት፡፡ በዚህም ምክንያት የብዙ ሀያላንና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራትን ትኩረት እየሳበች ትገኛለች፡፡ ከአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት አንዷ የሆነችው ጣሊያንም ከአፍሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር እየሰራች ትገኛለች፡፡ በማቴ እቅድ ከአፍሪካ ጋር “በእኩል አጋርነት እና በጋራ የማደግ” መርህ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍም እየሰራች ትገኛለች፡፡ ሀገሪቱ ለእቅዱ ፕሮጀክቶች ማስተግበሪያ 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዩሮ በጀት የመደበች ሲሆን በዋናነት ኢነርጂ፣ ግብርና፣ ትምህርትና ስልጠና፣ ጤና፣ ውሃ እና መሠረተ ልማት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የጣሊያን-አፍሪካ ጉባኤ በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን ሁለተኛው ጉባዔ በአፍሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በአዲስ አበባ በአዲስ ዓለምአቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል በትናትናው ዕለት ተካሂዷል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጉባኤው መክፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር የማቴ እቅድ ኢትዮጵያ ቅድሚያ ሰጥታ ከምትሰራባቸው ዘርፎች ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ በሀገር

በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ በተለይ በታዳሽ ሀይል ልማት፣ በግብርና፣ በመሰረተ ልማት፣ በዲጂታል ትራንስፎርሜሽንና በሰው ሀይል ልማት ላይ ከምንሰራቸው ሥራዎች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ትላልቅ የውሃ ሀይል ልማት ፕሮጀክቶችን ከመገንባት አንስቶ ቀጣናዊ ትስስርን ለማጠናከር በባቡር መስመር፣ በአቬሽንና የኢኖቬሽን ማዕከላትን በመገንባት የምታከናውናቸው ተግባራት በአፍሪካ ለዘላቂ ልማትና ለጋራ እድገት መሰረት የሚጥሉ ናቸው ነው ያሉት፡፡

የጣሊያንና አፍሪካ ትብብር ሚዛናዊና ወደፊቱን የተመለከተ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ስደትን ለማስቆም፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል፣ የአፍሪካን አቅም ለማውጣት፣ በወጣቶችና ቴክኖሎጂ ላይ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ለማሳደግ በጋራ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የተገቡ ቃሎችን ወደ ተግባር ለመቀየር፣ በጣሊያንና አፍሪካ መካከል ያለውን ስትራቴጂካዊ አጋርነት ለማጠናከር ትሰራለች፡፡ በጋራ በመሆንም በጥገኝነት ላይ ሳይሆን በመከባበር፣ በብዝበዛ ላይ ሳይሆን በጋራ ብልጽግና ላይ፣ የወደፊቱን የሚያይ አዲስ ግንኙነት በአፍሪካና አውሮፓ መካከል መፍጠር እንደሚቻልም ጠቁመዋል፡፡

የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ በበኩላቸው፣ በጣሊያንና አፍሪካ ትብብር ባለፉት ሁለት ዓመታት በቢሊዮን ዩሮ የሚቆጠር ገንዘብ በመመደብ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶችን መተግበር ተችሏል፡፡ የተጀመረው ትብብር ሁለቱንም ወገኖች ተጠቃሚ የሚያደርግና በተጨባጭ የሚታይ ነው፡፡ በሀይል ልማት በተለይም በታዳሽ ሀይልና በባዮኢነርጂ ልማት ጣሊያንና አፍሪካ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩባቸው ካሉ ዘርፎች መካከል ናቸው፡፡ የምግብ ዋስትና ጥረቶችን በመደገፍ፣ የዲጂታል መሰረተ ልማቶችን በመገንባት፣ የጤናውን ዘርፍ ተደራሽነት በማሳደግ፣ በስራ ዕድል ፈጠራና በሌሎች ዘርፎች ጣሊያን ከአፍሪካ ጋር በትብብር እየሰራች እንደምትገኝም ገልጸዋል፡፡

ይህ የጣሊያን- አፍሪካ ጉባኤ ከሮም ውጭ በአፍሪካ ምድር ሲካሄድ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሲሆን ኢትዮጵያ አፍሪካን ከተቀረው ዓለም ጋር ከማስተሳሰር አንጻር ያላትን ከፍተኛ አቅም እንደሚያሳይ የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ ከትናንት በስቲያ በሰጡት መግለጫ ጠቁመዋል፡፡

**ቀመጫ እና ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔን አጥብቃ የምታራመድ ሀገር እንደመሆኗ፣ የአፍሪካን ጥረት ለማስተባበር እና አጠቃላይ የአህጉሪቱን የልማትና የደህንነት ግቦች ለማሳካት ጣሊያንን እንደ አማራጭ አጋር በመጠቀም በትብብር መስራቷ ምክንያታዊ ነው።**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)፣ ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በሰጡት ማብራሪያ፣ ጣሊያንና አፍሪካ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ቅርብ የሆኑ፣ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጅያ ሜሎኒ ወደ ስልጣን ከመጡ ወዲህ ግንኙነቱ እየተጠናከረ መምጣቱን ይናገራሉ፡፡

ጣሊያን ይፋ ባደረገችው በማቴ እቅድ በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች 14 የአፍሪካ ሀገራት ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በሰሜን አፍሪካ እንደ አልጀሪያ፣ ሞሮኮ፣ ቱኒዝያና ግብፅ እንዲሁም ከሰሀራ በታች ደግሞ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሞዛምቢክ፣ አይቮሪኮስት እና ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ሀገራት በተለያዩ መስኮች ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው፡፡

በኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአውሮፓና አሜሪካ ጥናት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተመራማሪ የሆኑት አቶ ታሪኩ አብርሃ በተቋሙ ገፀ-ድር ላይ Contemporary Italy- AU Cooperation Efforts: Dynamics and Prospects ahead በሚል ርዕስ ባሰፈሩት ጽሑፍ፣ ኢትዮጵያ ከጣሊያን ጋር ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ ግንኙነትና ትብብር ያላት ሀገር ናት፡፡

የጣሊያን ዋነኛ የንግድ አጋርና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ናት፡፡ እንደ ዊ ቢውልድ ግሩፕ (ሳሊኒ) ያሉ የግንባታ ኩባንያዎች በግንባታና ሪል እስቴት ልማት በሰፊው እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በማቴ እቅድም ኢትዮጵያ የጣሊያን ኩባንያዎች በኢንቨስትመንት በስፋት ከሚሰማሩባቸው ዘጠኝ ስትራቴጂክ የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ሆና መቀመጧንና ይህም የኢኮኖሚ እድገትንና ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በእጅጉ የሚደግፍ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ እና ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔን አጥብቃ የምታራመድ ሀገር እንደመሆኗ፣ የአፍሪካን ጥረት ለማስተባበር እና አጠቃላይ የአህጉሪቱን የልማትና የደህንነት ግቦች ለማሳካት ጣሊያንን እንደ አማራጭ አጋር በመጠቀም በትብብር መስራቷ ምክንያታዊ ነው፡፡ በተጨማሪም ከጣሊያን ጋር የሚደረግ ትብብር ከአውሮፓ ህብረት ማዕቀፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች ሀገራት ጋር ተመሳሳይ የፖሊሲ ተነሳሽነቶችን የበለጠ ለማጠናከር መንገድ ይከፍታል። ይህም በአጠቃላይ ኢትዮጵያና አፍሪካ ከአውሮፓ ጋር ለሚኖራቸው የወደፊት የልማት ትብብር እና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን እንደሚፈጥር አቶ ታሪኩ አብራርተዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገፁ ባወጣው መረጃ ኢትዮጵያ ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር በመተባበር ሁለተኛውን የጣሊያን-አፍሪካ ጉባዔን በአዲስ አበባ በማስተናገድ በሁለቱ አካላት መካከል ድልድይ ሆናለች ብሏል፡፡

# የአፍሪካውያን ... ከገጽ 1 የዞረ

"የሰው ልጅ በመንፈሱ ጠንካራ ከሆነ የትኛውም ዓይነት ችግር ቢገጥመው ማሸነፍ ይችላል፡፡ ይህ መታሰቢያ የሚያስረዳው ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ጋር ስትዋጋ ሁሉም ፈቱን ቢያዞርባትም መሰናክሎችን ሁሉ በማለፍ ነፃነቷን አስጠብቃ መቀጠል ችላለች፡፡ ይህም አፍሪካውያን ለነፃነት ለሚያደርጉት ትግል መነሳሳትን ፈጥሯል፡፡ አባቶቻችን ቅኝ ግዛትን በማስወገድ ነፃ የሆነ ሀገር አስረክበውናል፡፡ የእነሱ ወራሾች ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችንን ማረጋገጥ ይጠበቅብናል" ሲሉም ካዎቹ ካውንዳ አክለዋል፡፡

ሌላኛው መታሰቢያውን የጎበኙት ማዳራካ ኔሬሬ ይባላሉ፡፡ የታንዛኒያ የመጀመሪያው ፕሬዝዳንት ልጅ ናቸው፡፡ አባታቸው ጁሊየስ ኔሬሬ ከአፍሪካ ህብረት (የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት) መስራች አባቶች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ማዳራካ ኔሬሬ ከአንድ ወር በፊት የዓድዋ ድል መታሰቢያን በጎበኙበት ወቅት፣ "መታሰቢያው በጣም ነው የማረከኝ፡፡ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ለማስጠበቅ ከኢጣሊያ ጋር ያደረገችውን ጦርነት በተወሰነ ደረጃ አውቀው ነበር፡፡ ከዚህ ጉብኝት በዓድዋ ምን አይነት ዋጋ እንደተከፈለና እንደተሰራ በዝርዝር ተረድቻለሁ፡፡ በእውነት በዚህ የሚታየው ነገር ማንኛውም የአፍሪካ አንድነትን ለሚያቀነቅን (ፓን አፍሪካዊ) ሰው ትልቅ ተነሳሽነትን የሚፈጥር ነው። የአፍሪካ ህብረት መስራች አባቶችም የአፍሪካውያንን አንድነት ለማጠናከር ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትን በመታገል ነፃነቷን አስጠብቃ የዘለቀችበት ታሪክ መነሳሻ ሆኗቸዋል፡፡" ብለዋል፡፡

በአፍሪካ የነፃነት ትግልና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት) ምስረታ ጉልህ ሚና ከነበራቸው መሪዎች መካከል አንዱ የሆኑት የቀድሞው የጋና ፕሬዝዳንት ክዋሜ ንክሩማህ የልጅ ልጅ ክዋሜ ቶማስ መታሰቢያውን ከጎበኙት መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ቶማስ በአስተያየታቸው፣ "ኢትዮጵያ አፍሪካውያንን ወደ አንድነት እንዲመጡ በማድረግ፣ የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ እውን እንዲሆን፣ የአፍሪካ ኩራት በመሆን ወሳኝ ሚና ተጫውታለች፡፡ ይህ ጉብኝት ለእኔ ትርጉም ያለውና ታሪካዊ ነው፤ ምክንያቱም አያቴ ኢትዮጵያ በዓድዋ ድል ለአፍሪካ ነፃነትና ከቅኝ አገዛዝ የመላቀቅ ትግል ምልክት መሆኗን ሲናገር የነበረውን ማየት ችያለሁ፡፡ ...ለእኔ ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ ከታሪኬ (ከአያቴ ታሪክ) በመገናኘቴ ክብር ተሰምቶኛል፤ ምክንያቱም እሱ ዘመኑን የቀደመ ሰው ነበር፡፡ አዲስ አበባ ስመጣ እንደ ጋናዊ ካለኝ የታሪክ ውርሴ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያውያንና ሌሎች አፍሪካውያን ጋር ያለኝን ትስስር ነው ያየሁት። በመታሰቢያው ውስጥ የአያቴ ፎቶ ተሰቅሎና ታሪኩ ተካትቶ በማየቴ በጣም ክብር ተሰምቶኛል" ሲሉ የፈጠረባቸውን ስሜት ገልጸዋል፡፡

ቶማስ እንደገለጹት፣ እነ ክዋሜ ንክሩማህ ካሉ መሪዎች ራሳችንን የቻልን ነፃ ህዝቦች እንዴት መሆን እንዳለብን መንገዱን አሳይተዋል፡፡ ከዚህ አኳያ አንድነታችንን ማጠናከርና በኢኮኖሚ ረገድ የራሳችንን ሀብት መጠቀም፣ በራሳችን መተዳደር ከቻልን አፍሪካውያን ድምፃችን የሚሰማና ተፅዕኖ መፍጠር የምንችል እንሆናለን፡፡



ፎቶ- ከፋይል
የዓድዋ ድል መታሰቢያ የአፍሪካውያን ድል የሆነውን ዓድዋ ለትውልድ የሚያሸጋግር የታሪክ መነጽር ነው

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ኢትዮጵያ ሊወራት የመጣውን የኢጣሊያን ሰራዊት በዓድዋ ያሸነፈችበትና ድል ያደረገችበት ቀን ነው፡፡ ይህ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካና በመላው ዓለም ለሚኖሩ ጥቁር ህዝቦች ልዩ ቀን ነው። ድሉ የኢትዮጵያ ነፃነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ እንዲዘልቅ ከማስቻሉ ባሻገር በቅኝ ግዛት ቀንበር ውስጥ የነበሩ አፍሪካውያንና በመላው ዓለም የሚኖረው ጥቁር ህዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገው ትግል እንዲጠናከር መነሳሻ ሆኗል፡፡

የዓድዋ ድል የአፍሪካ፣ የመላው ጥቁርና ጭቁን ህዝቦች የተነሳሽነትና ኩራት ማሳያ ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት በሚገባው ልክ ታውቆ እየተዘከረ አልነበረም፡፡ ሆኖም ከሁለት ዓመት በፊት ድሉን በሚመጥን ልክ የሚዘከርበት ታላቅ መታሰቢያ በአዲስ አበባ እምብርት ፒያሳ ላይ ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። መታሰቢያውን ኢትዮጵያውያን፣ አፍሪካውያንና ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚመጡ ዜጎች እየጎበኙት ይገኛሉ፡፡

ከቀድሞ የላይቤሪያዋ ፕሬዝዳንት ኤለን ጆንሰን ሰርሊፍ፣ የቀድሞ የቻድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሱክሴስ ማስራ ጀምሮ ለተለያዩ ጉባኤዎች ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች፣ ሚኒስትሮች፣ የቀድሞ የአፍሪካ ህብረት መስራች አባቶች ልጆችና የልጅ ልጆች፣ ወጣቶች፣ በውጭ የሚኖሩ አፍሪካውያንና የካሪቢያን ተወላጆች እንደጎበኙት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ዋና ዳይሬክተር ዮሴፍ ቤኮ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ቅኝ ሊገዛት በመጣው ኢጣሊያ ላይ በዓድዋ ያስመዘገበችው ድል በቅኝ ግዛት ቀንበር ውስጥ የነበሩ አፍሪካውያን 'እኛም ማሸነፍ እንችላለን' የሚል መነሳሳትና ወኔ እንዲሰንቁ አድርጓል፡፡ አፍሪካውያን የነፃነት ታጋዮች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ኢትዮጵያ እንዴት ቅኝ ግዛትን እንዳሸነፈች ተምረዋል፡፡ በሞራል፣ በገንዘብ፣ በስልጠናም ከኢትዮጵያ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡

ዮሴፍ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ መታሰቢያው ለአፍሪካውያን ልዩ ትርጉም አለው፡፡ በተለያየ ጊዜ የአፍሪካ መሪዎች፣ የቀድሞ የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ መሪ የሆኑ ቤተሰቦች ጎብኝተውታል። 'ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ መፈለግ' የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ወደ መሬት ለማውረድ መሰረት የሆነ፣ አይቻልምን በይቻላል የቀየረ፤ የአፍሪካ መልክ በሌላ የታየበት ድል ነው፡፡

አፍሪካውያን፣ የፓን አፍሪካኒስት ልጆችና የልጅ ልጆች ወደ መታሰቢያው በመጡ ጊዜ "እናንተ የዓድዋ አምባሳደሮች ናችሁ" በማለት መታሰቢያውን ሌሎች አፍሪካውያን እንዲጎበኙ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን አሁንም የማስተዋወቁ ስራ በቂ አይደለም፡፡ 'ታሪክህን ራስህ በትክክል ካልተናገርክ ሌሎች በተሳሳተ መንገድ ታሪክህን ይነግሩሃል' እንደሚባለው አሁንም መስራት ይጠበቅብናል፡፡ የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም፣ የማህበራዊ ሚዲያ ሰዎችን (ለምሳሌ በቅርቡ ታዋቂው ዩቲዩበር አይሾውስፒድ ዓድዋን ጎብኝቷል) በመጠቀም የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ፣ የዓድዋ ድል ለአፍሪካና ጥቁር ህዝቦች ያለውን ፋይዳ ማስተዋወቅ ተችሏል። ወደፊትም ብዙ እንደሚሰራ ዮሴፍ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

## በመታሰቢያው የሚገኙ አፍሪካን የሚወክሉ አሻራዎች

መታሰቢያው በውስጡ የዓድዋ ድል እንዴት እንደተገኘ፣ የአፍሪካን የትግል፣ ተጋድሎና ነፃነት ታሪክ የሚያሳዩ ወካይ ምልክቶች፣ ቅርሶች፣ የጽሑፍና የተለያዩ መረጃዎችን አካትቶ ይዟል፡፡ ወደ ዋናው የመታሰቢያ ህንፃ ከመግባታችን በፊት በተለምዶ አራዳ ህንፃ እየተባለ ከሚጠራው ቀጥሎ ሰው ሰራሽ ፏፏቴ፣ እንዲሁም የመታሰቢያው አካል የሆነ 20 ሜትር ርዝመት ያለው የዓድዋ ድል ሀውልት ይገኛል፡፡ ይህ ግዙፍ ሐውልት መሀከል ላይ ዙሪያውን በተለያየ ቅርጻ ቅርፅ ጀግኖች በጦር ሜዳ ጋሻና ጦር ታጥቀው ሲዋጉና ሲዋደቁ፣ ከላዩ ላይ የአፍሪካ ካርታ ይታያል፡፡

የመታሰቢያው ዋና ዳይሬክተር ዮሴፍ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ ሐውልቱ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን አፍሪካ ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ ትናንት ምን ያህል መስዋዕትነት እንደከፈሉ፣ አሁን ያለችው አፍሪካ በተለያዩ ፈተናዎችና ጫናዎች አልፋ ነገ የተባበረች፣ የለማችና የበለፀገች እንደምትሆን እንዲሁም የአፍሪካ የትናንት ትግል፣ የዛሬ ጉዞና መጻኢ እድሏን የሚያሳይ ነው፡፡

በዓድዋ ድል መታሰቢያው ከፍተኛ አስጎብኚ ትዕግስት ሀንጋሶ፣ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፀችው፣ በድል ሐውልቱ ላይ ከላይ የሚታየው የፓን አፍሪካኒዝም መለያ ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ጦርነት መስዋዕትነት በመክፈል ለአፍሪካ ብርሃን እንደሆኑ ያሳያል፡፡ ሐውልቱ ለከተማዋ መለያ የሆነ፣ ነዋሪዎችና እንግዶች ተሰባስበው የሚጎበኙት፣ ለታሪክ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ፎቶ የሚነሱበት ስፍራ ሆኗል፡፡

ወደ ዋናው የመታሰቢያው ህንፃ ሲገባ መሀል ላይ፣ እቴጌ ጣይቱ በመቀሌው ጦርነት የኢጣሊያን ሰራዊት ለማሸነፍ የዘየዱት የጦርነት ስልት መታሰቢያነት ከተሰራው ሰው ሰራሽ ፏፏቴ (ፋውንቴን) ቀጥሎ ባለው ህንጻ ላይ በአሻራ ምልክት በዓድዋ ሙዚየም የአፍሪካ ካርታ ቅርፅ በትልቁ ይታያል፡፡ ይህም የዓድዋ ድል ለአፍሪካውያን የብርሃን ጮራ የፈነጠቀ መሆኑን ለማሳየት የተቀመጠ እንደሆነ ዮሴፍ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

በመታሰቢያው ከፍተኛ አስጎብኚ ትዕግስት ሀንጋሶ እንደገለፀችልን፣ በካርታው ላይ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ወደ አፍሪካ የሚፈነጥቅ ብርሃን የሚታይ ሲሆን ይህም የዓድዋ ድል ለአፍሪካውያን፣ በመላው ዓለም ለሚኖሩ ጥቁርና ጭቁን ህዝቦች ብርሃን መሆን እንደቻለ ያሳያል። ከድሉ በኋላ መላው አፍሪካውያን ይቻላል የሚል መንፈስ በመያዝ ከቅኝ ግዛት ራሳቸውን ነፃ አውጥተዋል፡፡

ሌላው በፓን አፍሪካኒዝም ስም የተሰየመ፣ በመታሰቢያው ከሚገኙ አዳራሾች ሁሉ ግዙፍ የሆነ አዳራሽ አለ። 2 ሺህ 214 ገደማ ወንበሮችን የያዘ፣ የተሟላ የድምፅ ስርዓት የተገጠመለት፣ አቀማመጡም አቃፊ ዓይነት የሆነ፣ በግዝፈቱም አፍሪካ ከዓለም አህጉራት በስፋት ትልቋ መሆኑን፣ የወንበሮቹ ቁጥር መብዛትም ለብዙሃኑ የአህጉሩ ሀገራት መቀመጫ መሆን የሚችል፣ በአንድነት መሰባሰብ የምንችልበት ቦታ አለን የሚል ምልክት ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም ፓን አፍሪካኒዝም ሲባል የተግባባ፣ የተባበረ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር ጋር አብሮ የሚታይ እንደሆነ ዮሴፍ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር በሙዚየሙ ከዓድዋ እስከ አፍሪካ ህብረት (የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት) ምስረታ ድረስ ያሉትን ሁነቶች የሚያሳዩ መረጃዎች የሚገኙበት ክፍል ይገኛል፡፡ የፓን አፍሪካ ኮንግረሶች፣ የፓን አፍሪካኒስቶች እንቅስቃሴ፣ በሁለተኛው የኢጣሊያን ወረራ ጥቁሮች ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙበት ሁኔታ፣ የቀድሞ የአፍሪካ እና የዓለም መሪዎች ኢትዮጵያ በዓድዋ ለአፍሪካ ምን ማለት እንደሆነች ግድግዳ ላይ የሰጧቸው አስተያየቶች ከፎቶአቸው ጋር ይታያል፡፡

ዮሴፍ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ በመታሰቢያው የአፍሪካ ህብረትን (የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት) በመመስረት አስተዋፅኦ የነበራቸው የአፍሪካ ህብረት መስራች አባቶች ታሪካቸው የሚዘከርበት ኮሪደር መኖሩ፣ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካውያንን አንድነት፣

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

የህግ ጉዳይ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017

## ክፍል አንድ

ጣናበል ለማ (ዐቃቤ ህግ)

### መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከታደለችው ሰፊና ብዙ ዓይነት መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ፀባይ የተነሳ፣ የተለያዩ እንስሳት እንዲሰፍሩባትና የተለያዩ እፅዋት እንዲበቅሉባት የሚያስችል ሥርዓተ-ምኅዳር ባለቤት ናት።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከከተሞች መስፋፋት፣ ከሕዝብ ብዛት መጨመር እንዲሁም በተለያዩ ወቅቶች ከሚከሰቱ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ጋር በተያያዘ፣ በተለያዩ መንገዶች ተጠብቀው በቆዩና ለአካባቢያዊ ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ባላቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል። ከእነዚህ ለጉዳት ከተጋለጡ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ደግሞ የውኃ ሀብት ተጠቃሽ ነው።

መንግሥት እንደ አረንጓዴ አሻራ ያሉ የውኃ፣ የአፈር እና የደን ሀብትን የመጠበቅና የአየር ንብረት እንዳይዛባ የማድረግ አዎንታዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ሰፋፊ እና የሀገሪቱን ዜጎች በነቂስ የሚያሳትፉ መጠነ-ሰፊ ተግባራትን እንደ አንድ ዋነኛ የሀገሪቱ አጀንዳ ይዞ ለአፈጻጸሙ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ይገኛል። ይህም ለጉዳዩ የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት የሚያሳይ ነው። ከዚህም ባሻገር በቅርብ ጊዜያት በኢትዮጵያ ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ የወንዝ ዳር የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች ትልቅ የመልካም አስተዳደርና የከተማ ገጽታ ማሻሻያ አካል ሆነው ብቅ ብለዋል።

እነዚህ ፕሮጀክቶች ከውበት እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ከሀገሪቱ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎች ጋር በእጅጉ የሚጣጣሙ ናቸው። ይህ ጽሑፍ የሀገራችንን የአካባቢ ጥበቃ የሕግ ማዕቀፎች በጠቅላላው፣ የወንዝ ዳር የኮሪደር ልማት ለአካባቢ ጥበቃ ሕግ ተፈጻሚነት የሚያበረክተውን አዎንታዊ ተፅዕኖ እና የወንዞች ዳርቻ ብክለት የሚያስከትለውን የሕግ ተጠያቂነት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 እና ሌሎች ሕጎች አንፃር ይዳስሳል።



### 1. የአካባቢ ጥበቃ የሕግ ማዕቀፎች በጠቅላላው

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 545/2016 አንቀፅ 2(2) መሠረት፤ "የአካባቢ ጥበቃ" ማለት የሰው ልጅን ጨምሮ የማንኛውም አካል ሕይወት እና ዕድገት የሚወስኑ የመሬት፣ የውኃ፣ የአየር፣ የአየር ንብረት ሥርዓትና የመሳሰሉት ሌሎች የአካባቢ ሀብቶች፣ ክስተቶችና ሁኔታዎች በመጠበቅ፣ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪውን ትውልድ ዕድል ሳያሰናክል እንዲሟላ ማስቻል ነው። ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ትውልድ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የመጪውን ትውልድ በተፈጥሮ ሀብት የመጠቀም መብት በማይጎዳ መልኩ ሊሆን ይገባል።

የአካባቢ ጥበቃን ከማረጋገጥ አንፃር ሀገራችን የተለያዩ ፋይዳ ያላቸውን ሕጎች በማውጣት እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በማፅደቅ ወደ ትግበራ ገብታለች። በዚህ ረገድ ከተዘጋጁት የሕግ ማዕቀፎች መካከል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መቋቋሚያ አዋጅ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ፣ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ፣ የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ፣ የደን ልማት ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ፣ በቅርቡ የጸደቀው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁጥር 1383/2017፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017፣ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ እና መሰል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከአካባቢ ጥበቃ ረገድ ሚና ያላቸውን የሕግ ማዕቀፎች መጥቀስ ይቻላል።

በ1995 የወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ለአካባቢ ደህንነት ዕውቅናና ጥበቃ የሚሰጥ ሲሆን፤ በአንቀጽ 44 (1) ሁሉም ሰዎች ንጹሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው እንዲሁም በአንቀፅ 92 መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው ጥረት የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ተደንግጓል። በተጨማሪም ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት ያገናዘበ እንዲሆን እና የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲ እና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት በሕገ-መንግሥቱ ተቀምጧል።

ሌላኛው ከአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ጋር በተያያዘ የሚነሳው አዋጅ ቁጥር 300/1995 ሲሆን፤ ከጠቅላላው የአዋጁ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በካይ ነገሮችን ወደ አካባቢ መልቀቅን ይከለክላል። በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጁ መሠረት ማንኛውም ሰው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልገው ፕሮጀክት ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ወይም ከሚመለከተው የክልል አካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ መከናወን እንደሌለበት፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት በፕሮጀክቱ ባለቤት ወጪ መከናወን እንዳለበት እና ባለሥልጣኑም ይህን የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለበት ይደነግጋል።

### 2. የወንዝ ዳር የኮሪደር ልማት ለአካባቢ ጥበቃ ሕጎች ሊያበረክት የሚችላቸው በጎ ተፅዕኖዎች

#### ሀ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ሕጎችን ዓላማ ያሳካል

ከአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ጋር በተገናኘ በተለያየ መልኩ ከወጡ ሕጎች ለአብነት ያህል የአካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 300/1995 ብንመለከት፤ የቆሻሻ አወጋገድን፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓቶችን እና የውኃ አካላትን ብክለት መቆጣጠርን አስመልክቶ ግልጽ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል።

የኮሪደር ልማቱ ከወንዙ ዳር የሚገኙ ቤቶችንና ድርጅቶችን ከሕጋዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓት ጋር በማገናኘት እንዲሁም የቆሻሻ ማጠራቀሚያ እና ማስወገጃ መሠረተ-ልማቶችን በማስፋፋት የአዋጁን ዓላማዎች በተግባር እንዲውሉ ያደርጋል። የወንዞች ንጽሕና ሲጠበቅ የመጠጥ ውኃ ምንጮች ጥራት ይጠበቃል፣ የውኃ ወለድ በሽታዎች ስርጭት ይቀንሳል እንዲሁም ለሰው ልጆችም ሆነ ለእንስሳት ጤናማ የመኖሪያ አካባቢ ይፈጠራል።

#### ለ. የሕገ-ወጥ ቆሻሻ አወጋገድን ማስቀረት

የኮሪደር ልማቱ የውኃ ዳርቻዎችን ለአገልግሎት ክፍት ሲያደርግና የሕዝብ ክትትል ሲኖርበት ሰዎች ቆሻሻን ወደ ወንዝ የመድፋት ልምዳቸው ይቀንሳል። ይህ ደግሞ እንደ ደንብ ቁጥር 180/2017 በመሳሰሉ የሕግ ማዕቀፎች በሕግ የተከለከለውን የውኃ ብክለት በተግባር እንዲወገድ ያግዛል።

#### ሐ. የዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ድጋፍ

የወንዝ ዳር ኮሪደር ልማት የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የሚያስችሉ ዕፅዋትን በመትከል፣ የግንባታ መዋቅሮችን በማበጀት እና የውኃ ፍሰትን በማስተካከል ይረዳል። ይህ በረጅም ጊዜ ለአፈርና ውኃ ሀብት ዘላቂ አስተዳደር ወሳኝ ነው። የአፈር መሸርሸርን መቆጣጠር የመሬት ጥራት እንዲጠበቅ ከማድረጉም በላይ፣ የወንዙ የውኃ ፍሰት መደበኛነት እንዲያገኝ ያግዛል፤ ይህም የመሬት ይዞታ ሕጎችን በተዘዋዋሪ ይደግፋል።

#### መ. በአካባቢ ጥበቃ ረገድ የሕዝብ ተሳትፎን ማሳደግ

የአካባቢ ተፅዕኖ ምዘና ሕግ ሕዝቡ በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ በሚያሳድሩ ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳቡን የመስጠት መብት እንዳለው ይደነግጋል። የኮሪደር ልማቱ ሲጠናቀቅ ለሕዝብ ክፍት በመሆኑ፣ ሰዎች የወንዞችን ውበትና ሥነ-ምህዳራዊ ፋይዳ በአካል እንዲያዩ ዕድል ይሰጣቸዋል። ይህ ደግሞ ለአካባቢ ጥበቃ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያዳብራል።

አንባቢዎቻችን ክፍል ሁለትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ
## የ8ኛ ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ አሸናፊዎች
## ዝርዝር ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በየካ፣ በኮልፌ ቀራንዮ፣ በአዲስ ከተማ፣ በጉለሌ፣ በለሚ ኩራ፣ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በን/ስ/ላፍቶ እና በቂርቆስ ክ/ከተሞች የሚገኙ ለተለያዩ አገልግሎቶች የተዘጋጁ የልማት ቦታዎችን በጨረታ አወዳድሮ በሊዝ ለማስተላለፍ ታህሳስ 25 ቀን 2018ዓ.ም በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሰረት ስማችሁ ከዚህ በታች በተዘረዘረዉ አግባብ 1ኛ የወጣችሁ አሸናፊ ተጫራቾች ይህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር(10) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለም ሆቴል አካባቢ ኤም.ኤ.ህንጻ ላይ በሚገኘዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 303 በመቅረብ የሚጠበቅባችሁን በማሟላት የሊዝ ውል እንድትፈጽሙ ጥሪያችንን እያስተላለፍን አንደኛ የወጡ ተጫራቾች ውል የማይፈጽሙ ከሆነ በሊዝ ደንቡ መሰረት አንደኛ የወጣው ተጫራች በሰጠው ዋጋ ዕድሉ 2ኛ ለወጡ ተጫራቾች የሚሰጥ በመሆኑና 2ኛ የወጡ ተጫራቾችም በተመሳሳይ ውል የማይፈጽሙ ከሆነ 3ኛ የወጡ ተጫራቾች አንደኛ የወጣው ተጫራች በሰጠው ዋጋ እንዲዋዋሉ በሊዝ ደንብ 162/2016 እና በተጫራቾች መመሪያ ላይ በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በውስጥ ማስታወቂያ ጥሪ የምናደርግ መሆኑን እየገለጽን ለጨረታ ከወጡ 125 ቦታዎች ውስጥ የቦታ ኮድ LDR-LIMK-MIX-00015231፣ LDR-KOL-MIX-00014974 እና LDR-KOL-MIX-00014975 ከጨረታ የተሰረዙ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

# የ8ኛ ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የአሸናፊዎች ዝርዝር በክ/ከተማ

### የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | አጅዋ ሪልስቴት ኃ/የተ/የግል ማኅበር | 110,000.00 | 100% | LDR-KIR-MIX-00015132 | 11 | 1919 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሲቲ ላይፍ ሆምስ ሪል ስቴት ኃ/የተ/የግል ማኅበር | 60,000.00 | 80% | | | | |
| | 3 | አዲስ ላይፍ ሪል ስቴት ኃ/የተ/የግል ማኅበር | 83,667.00 | 40% | | | | |

### የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | ሙሉጌታ ስሜ ጉዲሳ | 52,300.00 | 100% | LDR-NIF-MIX-00014090 | 15 | 597 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አህመድ አቡበከር አደም | 51,300.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ነፊሳ መሐመድ አወል | 50,301.00 | 100% | | | | |
| 2 | 1 | አዲሱ ፀጋዬ አስፋው | 61,101.75 | 100% | LDR-NIF-MIX-00014092 | 15 | 557 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | መዓዛ አብረሃ ሀምዛ | 53,860.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አሚር መሓመድ ሺፋ | 53,860.00 | 100% | | | | |
| 3 | 1 | ገ/ጊዮርጊስ ያይንእሸት ገ/እየሱስ | 72,009.00 | 100% | LDR-NIF-MIX-00014142 | 15 | 225 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ቸርነት መኮንን አይቸህ | 65,112.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አይነኩሉ ደጌ ተፈራ | 63,888.00 | 100% | | | | |
| 4 | 1 | ራሔል እንዳሻው ፀሐይ | 27,027.00 | 100% | LDR-NIF-MIX-00015042 | 14 | 369 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ናትናኤል በለጠ ገ/ሃና | 14,092.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ብርሃኔ ወ/ገብርኤል ባራኪ | 11,502.00 | 100% | | | | |
| 5 | 1 | አዲስ አለማየሁ መርሻ | 46,624.00 | 100% | LDR-NIF-MIX-00015044 | 14 | 150 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ምትኩ ወ/ዮሐንስ የሱፍ | 42,019.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሳኒ አብዶ ሸሪፍ | 42,000.00 | 100% | | | | |
| 6 | 1 | ቤተልሔም ንዋይ ፅጌ | 46,624.00 | 100% | LDR-NIF-MIX-00015059 | 14 | 175 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አሚር ሁሴን አብዶ | 40,313.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ኤርሚያስ አሰፋ ማሞ | 40,100.00 | 100% | | | | |
| 7 | 1 | ሲያኔ ሙሉጌታ ወንድሙ | 31,500.00 | 100% | LDR-NIF-MIX-00015060 | 14 | 543 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | መከሊት ጌቱ ሽፈራው | 23,511.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ወንድወሰን ተስፋዬ ኢላላ | 16,200.00 | 100% | | | | |

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | አበበ ተክሌ ሌሊሳ | 37,100.00 | 100% | | | | |
| 8 | 2 | ፍሬሀይወት ገ/ዮሐንስ ገ/መድህን | 36,176.23 | 100% | LDR-NIF-MIX-00015070 | 13 | 387 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ሚኪያስ ተስፋዬ ወረደ | 40,100.00 | 80% | | | | |

## የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | አጃኢባ ነስረዲን ሚፍታ | 31,600.00 | 100% | | | | |
| 1 | 2 | ሰላማዊት ሁሴን ዑስማን | 30,100.00 | 100% | LDR-ADK-MIX-00014014 | 11 | 214 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ነስሬ ያሲን ሱላላ | 28,504.67 | 100% | | | | |

## የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | ሄኖክ ይትባረክ ተክሌ | 35,461.00 | 100% | | | | |
| 1 | 2 | ምህረቱ ደርሶ ሽፈራው | 35,100.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00014971 | 11 | 141 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ዚያድ ሙዜ ፈረጃ | 32,000.00 | 90% | | | | |
| | 1 | አህመድ ሁሴን አሊ | 26,500.00 | 70% | | | | |
| 2 | 2 | አብራር ዘይኔ ሳሊያ | 11,865.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00014972 | 11 | 266 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ነቢል አህመድ አሊ | 14,255.00 | 70% | | | | |
| | 1 | ሽረፈዲን ሽኩር አህመድ | 26,100.00 | 100% | | | | |
| 3 | 2 | ሰኢድ ሀሰን ሰማን | 18,666.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00014973 | 11 | 227 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ኤልያስ  ዲላ ሁሴን | 11,565.00 | 100% | | | | |
| | 1 | ማርሽት ጌቱ ታደ | 30,210.00 | 100% | | | | |
| 4 | 2 | ገነት ጉሳዬ ቱፈር | 25,600.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00014976 | 02 | 137 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ዑስማን ሀሰን ሰማን | 24,444.00 | 100% | | | | |
| | 1 | አብዱልከሪም ከማል መሐመድ | 26,150.00 | 100% | | | | |
| 5 | 2 | ቢላል ሙስጠፋ ኢብራሂም | 19,155.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015013 | 03 | 159 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | አብዱልከሪም ሙስጠፋ ኢብሮ | 22,150.00 | 70% | | | | |
| | 1 | አይመንሐጂ እንድሬ አህመድ | 21,500.00 | 100% | | | | |
| 6 | 2 | ሰዑድ አብደላ ሰይድ | 20,015.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015014 | 03 | 189 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ሽምሱ ዘይኔ ሳሊያ | 18,260.00 | 100% | | | | |
| | 1 | ማርታ በርታ መገንታ | 45,824.70 | 85% | | | | |
| 7 | 2 | ሳዲቅ መሐመድ ሀይሉ | 24,850.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015015 | 03 | 161 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | አብዱልባሲጥ ሲራጅ ሬድዋን | 21,565.00 | 100% | | | | |
| | 1 | ፈይሰል ሙዘሚል ኑሪ | 33,500.00 | 85% | | | | |
| 8 | 2 | ዮናስ ብዙአየሁ ብርሃኑ | 30,000.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015016 | 03 | 180 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ሀይረዲን ሲራጅ መሐመድ | 22,563.00 | 100% | | | | |
| | 1 | እናት ተመስገን ወሊቃ | 85,719.00 | 100% | | | | |
| 9 | 2 | ጀሚላ ሁሴን አህመድ | 73,430.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015147 | 07 | 128 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ኸይሩ አብደላ ሲማ | 62,500.00 | 100% | | | | |
| | 1 | መሐመድ ሙሰማ መሐመድ | 81,100.00 | 100% | | | | |
| 10 | 2 | ሀቢባ አህመድ መሐመድ | 66,400.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015148 | 07 | 87 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | መህቡባ ሀሰን አህመድ | 55,001.00 | 100% | | | | |
| | 1 | አንዋር የኑስ ሲራጅ | 86,725.00 | 100% | | | | |
| 11 | 2 | ባለምላይ ፀጋዬ አለማየሁ | 110,000.00 | 60% | LDR-KOL-MIX-00015149 | 07 | 89 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | አብዱራህማን መሐመድ ሰኢድ | 72,000.00 | 100% | | | | |
| | 1 | ሀሚድ አብዱራህማን አደም | 86,720.00 | 100% | | | | |
| 12 | 2 | ሳሙኤል ጌታቸው ወልዴ | 81,300.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015150 | 07 | 111 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | መሐመድሶሊህ ሰኢድ ስሩር | 93,555.00 | 80% | | | | |
| | 1 | ሰኢድ ነጋ የሻው | 111,755.00 | 100% | | | | |
| 13 | 2 | ሙባረክ ያሲን ፈረጃ | 92,576.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015151 | 07 | 104 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 3 | ነጃት መሐመድሁሴን | 137,000.00 | 50% | | | | |

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | 1 | መህቡባ መሐመድ አብዱላሂ | 126,435.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015152 | 07 | 84 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አሚኑ አህመድ ሙሳ | 110,500.00 | 100% | | | | |
| | 3 | መሠረት መኮንን ቢያዩብኝ | 96,573.00 | 100% | | | | |
| 15 | 1 | ዑመር ይብሬ በሽር | 156,080.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015153 | 07 | 167 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | መብራቱ ሀምዱ ይብራሂም | 132,430.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሰይድ አህመድ ማህሙድ | 132,211.00 | 100% | | | | |
| 16 | 1 | አሊያ ዑመር ሞሳ | 135,300.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015154 | 07 | 186 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ኑሩ አህመድ ማህሙድ | 107,556.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ተቂያ ሁሴን አልወዴ | 101,000.00 | 100% | | | | |
| 17 | 1 | አብዱራህማን ከድር ጃቢር | 23,294.93 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015155 | 07 | 217 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አዳነ እንዳለ በቀለ | 16,200.00 | 100% | | | | |
| | 3 | በሪሁን ስንሻው ደጉ | 15,100.00 | 100% | | | | |
| 18 | 1 | ጀማል ሙራድ ሽፋ | 22,575.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015156 | 03 | 226 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ትዕግስት ሽብሩ በቃና | 18,600.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አድነው ውብአንተ አድማስ | 20,600.00 | 80% | | | | |
| 19 | 1 | ሩቅያ መሐመድ ሲሳይ | 21,300.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015157 | 03 | 188 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሰሚራ አብዱልመጅድ ኸይረዲን | 33,000.00 | 40% | | | | |
| | 3 | ማያሙን ናስር ኑርበገ | 16,000.00 | 100% | | | | |
| 20 | 1 | ያስሚን ሰኢድ ያሲን | 46,527.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015158 | 05 | 309 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሀኒሳ ሙሰማ መሐመድ | 42,100.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሰለሞን አበራ ይርጉ | 40,453.00 | 100% | | | | |
| 21 | 1 | ጅላሎ ኑርሰቦ የሱፍ | 43,521.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015159 | 05 | 283 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሳለሀዲን ሙሰማ መሐመድ | 39,100.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ኢዘዲን መሐመድ ሲማ | 38,000.00 | 100% | | | | |
| 22 | 1 | አብዱልማሊክ ሱልጣን ካሊድ | 35,000.00 | 100% | LDR-KOL-MIX-00015292 | 03 | 199 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ምንተስኖት አሰፋ ነጊያ | 28,473.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ያሬድ ገ/ጻዲቅ ሥራኒ | 25,800.00 | 100% | | | | |

## የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | ክፍሌ ጌትነት አልታሰበ | 50,000.00 | 71% | LDR-AKI-MIX-00013939 | 13 | 429 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሚልኪያስ ተሾመ አድማሱ | 38,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ብዙነሽ አሊ ይማም | 33,000.00 | 100% | | | | |
| 2 | 1 | የኔመንግስት ግዛቸው ወንዴ | 29,600.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014245 | 04 | 322 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዋሲሁን አደም ይመር | 29,500.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ማትያስ መሀሪ ከበደ | 28,556.99 | 100% | | | | |
| 3 | 1 | መቅደስ ተሾመ ገ/ስላሴ | 55,625.85 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014278 | 08 | 106 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዳዊት ጌታቸው በቀለ | 68,000.00 | 60% | | | | |
| | 3 | ማህሌት አለም አሰፋ | 45,780.78 | 100% | | | | |
| 4 | 1 | አማኑኤል አስማረ ተመስገን | 50,125.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014281 | 08 | 104 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ፍቃዱ ቡታ ገመቹ | 47,921.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሀብታሙ ፀጋዬ ፍቅሩ | 45,222.00 | 100% | | | | |
| 5 | 1 | አምሳለ ወ/ጻዲቅ ትርፌ | 48,107.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014283 | 08 | 104 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሙሐመድ ጋሹ ይብሬ | 46,070.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሰአዳ መንግስቱ አህመድ | 43,320.50 | 100% | | | | |
| 6 | 1 | ደጀን እንድሪስ ተሰማ | 66,599.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014332 | 13 | 76 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዮሐንስ ላቀው ተፈራ | 65,123.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ዳርምየለሽ ፍቅሩ ታዬ | 65,000.00 | 100% | | | | |
| 7 | 1 | ፓወር ኮም ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | 37,041.04 | 70% | LDR-AKI-MIX-00014340 | 13 | 749 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ኤክስሊድስ ትሬዲንግ እና ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር | 22,016.02 | 100% | | | | |
| | 3 | ታዛ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህ/ሥራ ማህበር | 23,230.23 | 91% | | | | |

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | 1 | ፍቅረስላሴ ወርቁ ሀብቴ | 44,444.00 | 70% | LDR-AKI-MIX-00014588 | 02 | 232 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ጉዲሳ መሀመድ ገለታ | 28,055.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሀብታሙ ታደሰ ወእሌቦ | 27,000.00 | 100% | | | | |
| 9 | 1 | በቃሉ ሀይሉ ታፈሰ | 28,601.99 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014589 | 02 | 232 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ማርያ ኢንሪኮ ዘሊያኒ | 32,510.00 | 81% | | | | |
| | 3 | አብዱልቃድር ዘይኑ ፍሊ | 20,000.00 | 100% | | | | |
| 10 | 1 | ልቅናው ወልዴ ተስፋው | 37,525.00 | 70% | LDR-AKI-MIX-00014591 | 02 | 213 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ፀሐይ ወልዴ ገሙቹ | 30,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | መስታወት ደመቀ ኃይሌ | 29,420.19 | 100% | | | | |
| 11 | 1 | ኤልሳ አባተ ወ/መስቀል | 62,000.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014688 | 01 | 90 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | በረከት አጥናፉ ዓለሙ | 61,150.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ቤዛዊት ዘመን ታደሰ | 71,600.00 | 75% | | | | |
| 12 | 1 | ጴጥሮስ ተክሌ ዘረዝጊ | 62,000.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014692 | 13 | 165 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ውብሸት ጌታሁን መኩሪያ | 60,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አብረሀም ፈንቴ በዛብህ | 50,051.00 | 100% | | | | |
| 13 | 1 | ኃ/ማርያም ተ/መድህን ገብሩ | 50,000.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014693 | 13 | 167 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዶ/ር ኢማና ቱቾ ዳዋ | 56,001.00 | 86% | | | | |
| | 3 | ካባ ያዘው ዋቅጅራ | 47,200.00 | 100% | | | | |
| 14 | 1 | መዓዛ ታደሰ ልጅአለም | 22,200.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014887 | 04 | 377 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አልጋነሽ ውቤ ናዊ | 25,775.00 | 70% | | | | |
| | 3 | መዲና አማን ሲራጅ | 15,000.50 | 100% | | | | |
| 15 | 1 | አበበ ታደሰ አየለ | 34,285.00 | 60% | LDR-AKI-MIX-00014890 | 09 | 350 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሰለሞን ከበደ ደገፉ | 25,121.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ታደሰ ሲሳይ መለሰ | 23,550.00 | 100% | | | | |
| 16 | 1 | ሄኖክ ግዛቸው ገብሬ | 26,700.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014896 | 09 | 412 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ጋሻው ደምሴ ንጋቱ | 24,356.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሳዲቅ ሱልጣን ጋሮምሳ | 20,100.00 | 100% | | | | |
| 17 | 1 | ሰላማዊት ቦጋለ ሀብቴ እና መንሱር ዑመር ቢነጋ | 33,500.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014897 | 09 | 397 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ቴዎድሮስ ገ/ህይወት ዓለሙ | 25,825.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አብረሃም አሰፋ ወ/ሰንበት | 25,555.00 | 100% | | | | |
| 18 | 1 | አያቱላህ ሁሴን ሸፋው | 27,678.90 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014898 | 09 | 397 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዳኛቸው ቡሎ ለገሰ | 34,500.00 | 46% | | | | |
| | 3 | ቴዎድሮስ እንየው አለባቸው | 30,001.00 | 40% | | | | |
| 19 | 1 | ፀጋ ደሳለኝ መላኩ | 40,125.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014916 | 02 | 221 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ጀማል ሀሰን አህመድ | 34,337.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ቆንጅት በፈቃዱ አንተነህ | 33,823.00 | 100% | | | | |
| 20 | 1 | ሰለሞን አበበ ሰይፉ | 35,555.50 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014919 | 09 | 404 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ፍቃዱ ቶልቻ እና ራሔል ሞገስ ደምለው | 30,100.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ወርቁ ጠመረ ዳንጉል | 23,785.00 | 100% | | | | |
| 21 | 1 | ጀማል ነጅሙ ሻሚል | 28,877.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014922 | 08 | 239 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | በቀለ ፋንታ አስረስ | 42,000.00 | 50% | | | | |
| | 3 | ወርቂ እምሩ ዘውዱ | 27,721.00 | 100% | | | | |
| 22 | 1 | ጌታ ባዘዘው ደምሴ | 32,315.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014927 | 08 | 233 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ኢብራሂም ነጅሙ ሻሚል | 29,377.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ዮሐንስ ሙላት አይኔ | 26,875.00 | 100% | | | | |
| 23 | 1 | ጀንበሩ ይርጋ ወ/አማኑኤል | 29,113.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00014930 | 08 | 344 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ኢሳያስ ተፈራ ታደሰ | 41,100.00 | 50% | | | | |
| | 3 | ሰምሀል ሽፈራው ምህረት | 35,000.00 | 71% | | | | |
| 24 | 1 | ተክልዬ ሀ/ሚካኤል ገ/ሃና | 31,555.50 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015293 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ተክሌ አበበ እፉዬ | 30,219.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ቢተውሽ ከፈለ መኮንን | 32,600.00 | 80% | | | | |
| 25 | 1 | ህይወት ነብዩ መኩሪያ | 31,000.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015294 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አፈወርቅ አሰፋ አባተ | 32,600.00 | 80% | | | | |
| | 3 | እንዳለ አማረ ክፍሌ | 34,500.00 | 70% | | | | |

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 26 | 1 | ምንተስኖት ዘለቀ ገ/ማርያም | 27,890.99 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015295 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሲሳይ ሞላ አየለ | 32,600.00 | 80% | | | | |
| | 3 | ውባንቺ መንግስቱ በሳይ | 27,521.00 | 100% | | | | |
| 27 | 1 | ኑሪያ ሲራጅ አደም | 34,700.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015296 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዑመር ዳውድ መኮንን | 31,425.00 | 100% | | | | |
| | 3 | እሙዬ ወንድሰን ሳህሌ | 29,570.00 | 100% | | | | |
| 28 | 1 | ሳሙኤል አስማማው ሙሉአለም | 29,999.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015297 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ነስሩ አማን ሽፋ | 26,629.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሰላም ገብሩ ጣሰው | 24,121.00 | 100% | | | | |
| 29 | 1 | ጌታቸው ማንደፍሮ ደምስ | 27,580.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015298 | 09 | 275 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሞገስ ሙላት ኃይሌ | 26,775.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሙሉዬ ማረጉ መኮንን | 25,899.00 | 100% | | | | |
| 30 | 1 | ተመስገን አባትፋንታ የሺጋት | 31,221.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015299 | 09 | 272 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዘርፌ አስማማው ሙሉአለም | 29,999.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሀብታሙ አዱኛ ዱጋሳ | 26,839.55 | 100% | | | | |
| 31 | 1 | አዘቤ ርስቱ መለሰ | 33,150.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015300 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዮርዳኖስ አብነት ደበበ | 31,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ፍቅሩ ዘላለም ዘውዴ | 27,500.00 | 100% | | | | |
| 32 | 1 | አህመድ መሐመድ ተማም | 34,500.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015301 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ባቡ ለገሰ ጌታሁን | 31,500.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሚና እንድሪስ ተክሌ | 36,000.00 | 70% | | | | |
| 33 | 1 | ኤፍሬም ሽፈራው በዛብህ | 27,890.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015302 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አስናቁ ከበደ በላቸው | 27,888.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሄለን አብረሃም ውቤ | 30,001.00 | 80% | | | | |
| 34 | 1 | ፍቅርአዲስ በቀለ ወ/ጻዲቅ | 45,565.25 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015303 | 09 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ጌጤ አዱኛ በሊስ | 33,033.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሀለውያ እንድሪስ ሀሰን | 32,200.00 | 100% | | | | |
| 35 | 1 | እታፈራሁ ይርዳው ረታ | 44,923.86 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015304 | 09 | 197 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ደጉ አብረሃም ያየህ | 29,621.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ዮሴፍ ሲሳይ ሹምዬ | 28,337.00 | 100% | | | | |
| 36 | 1 | ታምራለች አለም እስከዚያ | 30,156.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015305 | 01 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ገበየሁ ተስፋዬ ወልዱ | 28,400.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አበበ አማረ ተፈሪ | 27,500.00 | 100% | | | | |
| 37 | 1 | እንድሪያስ በቀለ ወዳጄነህ | 32,750.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015306 | 01 | 400 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ቶሌራ አሰፋ ኢጋ | 32,510.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ተመስገን ደሴ በየነ | 28,600.00 | 100% | | | | |
| 38 | 1 | አብረሃም ግርማ መርጋ | 39,795.00 | 100% | LDR-AKI-MIX-00015307 | 13 | 490 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | የውብነሽ ግዛው ኪታባ | 35,115.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ልዑል እንድሪስ በቀለ | 28,979.59 | 100% | | | | |
| **የጉለሌ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር** | | | | | | | | |
| **ተ.ቁ** | **ደረጃ** | **የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር** | **ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ** | **ቅድመ ክፍያ በ%** | **የቦታው ኮድ** | **ወረዳ** | **የቦታው ስፋት በካ.ሜ** | **ምርመራ** |
| 1 | 1 | ኤሊያስ ታደሰ ስለሺ | 62,050.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00014655 | 07 | 171 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዮሐንስ አሰፋ ቅጣው | 52,701.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ማዕዛ አዱኛ ቸኮል | 51,100.00 | 100% | | | | |
| 2 | 1 | ተስፋዬ ሙሉነህ ማሞ | 52,600.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00014657 | 07 | 175 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሰላማዊት ብርሃን ባይነሳ | 50,050.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ያረጋል ሽፈራው ጫኔ | 50,000.00 | 100% | | | | |
| 3 | 1 | ትዕግስት ግዛቸው ወንዴ | 54,250.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00014658 | 07 | 176 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | እታፈራሁ ሀይሉ ተሰማ | 50,421.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ብርሃኑ ደምሴ ወ/ተንሳይ | 46,156.00 | 100% | | | | |

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | 1 | ትንሳኤ ተከስተ ድረስ | 47,500.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015187 | 07 | 210 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ታሪኳ ፈቃዱ በዳሳ | 61,200.00 | 60% | | | | |
| | 3 | እመቤት ተስፋው አታላይ | 44,600.00 | 100% | | | | |
| 5 | 1 | አርአያ ኪዳኑ አርአያ | 62,244.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015188 | 07 | 227 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ማወቅ ተስፋዬ መንግስቱ | 41,200.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ታደሰ ሁንዴ ሙለታ | 37,555.00 | 100% | | | | |
| 6 | 1 | ጤናው ሞሱ አንተነህ | 50,847.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015189 | 07 | 236 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | መስከረም ለማ አመጠ | 50,700.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሲሳይ ሀብቴ ተረዳ | 47,127.00 | 100% | | | | |
| 7 | 1 | ብዙአየሁ የኔወንድም ደሴ | 47,127.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015190 | 07 | 145 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ተክሌ ጋሼ አስራት | 48,000.00 | 80% | | | | |
| | 3 | ተሁቦ ንጉሴ ፈጠነ | 54,719.00 | 60% | | | | |
| 8 | 1 | አሰግደው ሀ/ሚካኤል ደምስ | 67,000.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015191 | 07 | 255 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ህይወት አብረሃም ገ/ሚካኤል | 51,050.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ገነት ታደሰ ጎንፋ | 68,800.00 | 50% | | | | |
| 9 | 1 | ኤፍሬም ፀጋዬ ታደሰ | 71,343.88 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015192 | 07 | 253 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ተገኜ ታደሰ ሀ/እየሱስ | 67,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ኢብራሂም ሀሰን አህመድ | 53,377.00 | 100% | | | | |
| 10 | 1 | ፍቃዱ አለሙ ውዴ | 47,157.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015193 | 07 | 247 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዳዊት ታደሰ ጎንፋ | 46,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | የቻለወርቅ አሰፋ ቅጣው | 44,215.00 | 100% | | | | |
| 11 | 1 | ቸርነት ክብሩ ውዱ | 67,199.99 | 77% | LDR-GUL-MIX-00015194 | 07 | 143 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ስመሙ ለማ ዳዊቹ | 47,600.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ዮሴፍ አለነ ተረፈ | 47,397.04 | 100% | | | | |
| 12 | 1 | በላይነህ ያቅታል ብዙነህ | 52,888.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015195 | 07 | 144 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ፀሐይ ይትባረክ ሀይሌ | 44,210.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ዳዊት አሉማ መገርሳ | 41,000.00 | 100% | | | | |
| 13 | 1 | በእምነት ጉሳዬ ቢራቱ | 71,900.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015196 | 07 | 145 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ካሰው ይመር ፋንታው | 57,600.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ቸሩ አለምኔ ከበደ | 55,777.00 | 100% | | | | |
| 14 | 1 | ህሊና ጉሳዬ ቢራቱ | 70,300.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015197 | 07 | 147 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | እፁብነሽ ፈቀደ ነጋሽ | 57,723.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ደጀኔ አበራ ፋንታዬ | 56,006.80 | 100% | | | | |
| 15 | 1 | አሰገደች ወንድይፍራው ወ/ስላሴ | 71,177.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015198 | 07 | 148 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ስንዱ አበበ ወርቅነህ | 70,021.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ኤሊያስ ጉሳዬ ቢራቱ | 69,800.00 | 100% | | | | |
| 16 | 1 | ኢቶፕ የስነጥበብ ሥራ ኃ/የተ/የግል ማኅበር | 60,100.00 | 100% | LDR-GUL-MIX-00015199 | 07 | 233 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ፍቅሩ ስንሻው እንግዳው | 52,001.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሰላም አናጋው መንግስቴ | 50,110.00 | 100% | | | | |

## የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | ቢኒያም መልከብርሃን ትርሲት | 35,947.71 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014732 | 04 | 306 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አበባሸት ንጉስ ተሾመ | 27,850.00 | 100% | | | | |
| | 3 | በሪሁን ሰጠ እጅጉ | 27,150.00 | 100% | | | | |
| 2 | 1 | ምስጋናው ልሳኑ ሩፌ | 35,150.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014733 | 04 | 217 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ባንተላይ አቅናቸው በዛብህ | 34,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ለገሰ በላይነህ ማመጫ | 32,455.00 | 100% | | | | |
| 3 | 1 | መሐመድ ኢብራሂም ሀሰን | 27,001.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014776 | 04 | 326 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አስቻለው አለማየሁ ጌታነህ | 22,050.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሲሳይ ጎሮ ጭኮ | 23,051.00 | 75% | | | | |

# ማስታወቂያ

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | 1 | አህመድ አብዱ አህመድ | 40,150.00 | 60% | LDR-LIMK-MIX-00014778 | 04 | 306 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አሰፋ ዘላለም መንግስቱ | 28,355.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አብዱራህማ ወሌ ይመር | 25,556.00 | 100% | | | | |
| 5 | 1 | ወርቃየሁ አየለ ይገዙ | 30,675.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014780 | 04 | 256 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዘውዱ ዮሐንስ ሉሌ | 30,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አብይ ማሞ ጃለታ | 31,251.50 | 90% | | | | |
| 6 | 1 | አለማየሁ ይልማ አየለ | 27,255.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014784 | 04 | 272 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ፍቅርአዲስ ሙሉ ፋንታ | 26,199.99 | 100% | | | | |
| | 3 | ጀሚላ አሊ ኢብራሂም | 25,735.00 | 100% | | | | |
| 7 | 1 | ይትባረክ ማሙዬ ወ/ማርያም | 29,860.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014786 | 04 | 268 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | መኮንን አዲሱ ዋጋው | 28,199.99 | 100% | | | | |
| | 3 | ባምላኩ ደምሴ ተሻለ | 27,985.08 | 100% | | | | |
| 8 | 1 | ስንታየሁ ወ/መስቀል ቅራቶ | 32,212.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014741 | 04 | 300 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | እዮብ ሰይፈ አየለ | 27,355.00 | 100% | | | | |
| | 3 | መስታወት ሽመልስ አበጋዝ | 32,119.19 | 70% | | | | |
| 9 | 1 | ዘውዱ በላይ በዛብህ | 30,101.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014742 | 04 | 395 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዳዊት ደመቀ ንሰራሄ | 27,777.70 | 100% | | | | |
| | 3 | ሰርካለም ብርሃኑ ታዬ | 26,175.00 | 100% | | | | |
| 10 | 1 | አበበ ጃለታ መንጌ | 27,999.16 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014743 | 04 | 335 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | በቀለ ነጋዎ ሔይ | 24,500.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አዲሱ ጥላዬ ክንዴ | 31,642.00 | 65% | | | | |
| 11 | 1 | ተዋቸው አዲስ ደምለው | 29,013.30 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014746 | 04 | 313 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ቴዎድሮስ ብርሃኑ ታዬ | 28,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ብሩክታዊት አሸብር በየነ | 28,777.00 | 87% | | | | |
| 12 | 1 | ስለሺ ወለላው ታምራት | 31,100.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014771 | 04 | 390 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሲራጅ አህመድ አክመል | 25,112.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አስረበብ አደም ይመር | 24,500.00 | 100% | | | | |
| 13 | 1 | ትዕግስት ተስፋ ደሴ | 28,512.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00014760 | 04 | 389 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ናሆም ሰይፈ ወንድአፈራው | 22,900.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አንዋር ሂቡ ፈቄ | 30,001.00 | 50% | | | | |
| 14 | 1 | ፍሬው ተመስገን ወልዴ | 40,027.16 | 85% | LDR-LIMK-MIX-00014798 | 14 | 200 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አበበ በላቸው ጌቴ | 35,616.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አባቡ ፀጋዬ አበበ | 35,150.00 | 100% | | | | |
| 15 | 1 | ያየህይራድ ገዛኸኝ ደስታ | 47,200.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015222 | 14 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ታምራት ሸዋንግዛው ወጋየሁ | 42,121.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ዳዊት መልካ ጉንጆ | 34,600.00 | 100% | | | | |
| 16 | 1 | አብደላ እንድሪስ አብዱ | 54,725.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015223 | 14 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ትዕግስቱ ጥላሁን ሀ/ወልድ | 44,201.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ጌታቸው በድሉ ተሰማ | 42,251.00 | 100% | | | | |
| 17 | 1 | ደረጀ አየለ አይችሉህ | 48,900.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015224 | 14 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሰይድ ይብሬ አድነህ | 46,700.00 | 100% | | | | |
| | 3 | አሸናፊ በድሉ ተሰማ | 36,551.00 | 100% | | | | |
| 18 | 1 | ዘመናይ ጋሻው በዛብህ | 31,019.19 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015228 | 14 | 429 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሳሙኤል ጥላሁን ሀ/ወልድ | 28,720.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ቅዱስ አበባየሁ ወርቁ | 26,670.00 | 100% | | | | |
| 19 | 1 | ያረጋል በየነ እንዳለው | 30,250.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015229 | 14 | 429 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ደስታ ሊሊሶ ሄሜ | 30,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሄኖክ  አሰፋ አስማረ | 35,000.00 | 70% | | | | |
| 20 | 1 | አይደን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | 25,199.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015232 | 14 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሳሙኤል ሽቤ ዋለ | 22,222.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ናትናኤል ግርማ ጌታቸው | 21,820.00 | 100% | | | | |
| 21 | 1 | ህይወት ገበየሁ ጌታሁን | 29,300.00 | 90% | LDR-LIMK-MIX-00015237 | 14 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ያሬድ ገ/ማርያም ጋጋ | 26,244.86 | 100% | | | | |
| | 3 | ዳኜ አበራ አፍራሴ | 23,127.00 | 100% | | | | |

| ተ.ቁ | ደረጃ | የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር | ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ | ቅድመ ክፍያ በ% | የቦታው ኮድ | ወረዳ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | 1 | ኤርሚያስ ኮከቤ አስረስ | 29,000.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015238 | 14 | 500 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሙሐመድ ቃሲም አህመድ | 28,200.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ታደለ ደግነህ አያሌው | 21,700.00 | 70% | | | | |
| 23 | 1 | ቃለአብ ለማ ታደሰ | 126,000.00 | 70% | LDR-LIMK-MIX-00015265 | 10 | 130 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ኤርሚያስ ሀብቴ መላኩ | 81,677.00 | 100% | | | | |
| | 3 | በቃል ኪዳነወልድ አምሳሉ | 77,521.00 | 100% | | | | |
| 24 | 1 | ቃልኪዳን ለማ ታደሰ | 83,459.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015266 | 10 | 130 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ደግሰው በልስቲ ጌታሁን | 81,123.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሀዲስ ረቢ ተ/ማርያም | 77,555.00 | 100% | | | | |
| 25 | 1 | ዮዲት በርሔ ሀይሉ | 91,212.00 | 100% | LDR-LIMK-MIX-00015267 | 10 | 130 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አለሙ ደምሴ ነጋሽ | 80,755.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ሸዊት ዘርዑ ተስፋሁነኝ | 78,170.00 | 100% | | | | |
| **የየካ ክፍለ ከተማ የአሸናፊዎች ዝርዝር** | | | | | | | | |
| **ተ.ቁ** | **ደረጃ** | **የአሸናፊዎች ስም ዝርዝር** | **ለካሬ ሜትር የተሰጠ ዋጋ** | **ቅድመ ክፍያ በ%** | **የቦታው ኮድ** | **ወረዳ** | **የቦታው ስፋት በካ.ሜ** | **ምርመራ** |
| 1 | 1 | ለምለም አበበ ፅጌ | 29,211.00 | 100% | LDR-YEK-MIX-00014647 | 10 | 281 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አበበ መዘምር ተ/አማኑኤል | 30,000.00 | 70% | | | | |
| | 3 | ይርበብ ፀጋው አድማሴ | 21,355.00 | 100% | | | | |
| 2 | 1 | ተስፋዬ ገበየሁ አበራ | 36,219.00 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015270 | 02 | 498 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ስዩም ካሱ ኢርጫፎ | 35,830.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ወንድምአገኝ ሀ/ማርያም ፍትህአወቅ | 25,000.00 | 100% | | | | |
| 3 | 1 | ዶ/ር ሰለሞን ፀሐይ ፈለቀ | 41,216.27 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015271 | 02 | 385 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ባድማው ላቀ አሸናፊ | 28,100.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ባህረስላሴ ስዩም ሃ/ስላሴ | 31,000.00 | 60% | | | | |
| 4 | 1 | አሰፋ ካሱ ኢርጫፎ | 48,600.00 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015272 | 02 | 300 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ጌትዬ መኮንን ወርቁ | 27,321.50 | 100% | | | | |
| | 3 | ሙሉጌታ መኮንን ገ/ህይወት | 27,100.00 | 100% | | | | |
| 5 | 1 | ጤናዬ ከበር ኬረታ | 33,333.33 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015273 | 02 | 270 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ቃለአብ መዝገቡ ተሰማ | 26,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ጳውሎስ ሰለሞን መኮንን | 21,000.00 | 100% | | | | |
| 6 | 1 | ሰብለ በላይነህ ሀይሉ | 57,165.00 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015274 | 02 | 251 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | እሌኒ እስክንድር የሸዋልዑል | 51,276.19 | 100% | | | | |
| | 3 | በላይነህ ካሳሁን ዳምጤ | 50,216.00 | 100% | | | | |
| 7 | 1 | አንሙት አረጋ ዘውዴ | 34,000.00 | 70% | LDR-YEK-MIX-00015275 | 02 | 263 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ዳኛቸው አማረ ምንላርግልህ | 25,600.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ውዳሴ አየለ በቀለ | 25,110.00 | 100% | | | | |
| 8 | 1 | ዱር ኢትዮጵያ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማኅበር | 24,000.00 | 55% | LDR-YEK-MIX-00015276 | 02 | 496 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ሱራፌል ፋንታሁን ተገኝ | 23,750.00 | 50% | | | | |
| | 3 | ኢክራም ጠይብ መሀመድ | 15,200.00 | 100% | | | | |
| 9 | 1 | ሳሙኤል ተሰማ መኮንን | 35,539.00 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015277 | 02 | 376 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | አህመድ መሐመድ ናስር | 35,000.00 | 100% | | | | |
| | 3 | ቶማስ ተስፋዬ ለማ | 33,333.33 | 100% | | | | |
| 10 | 1 | ዳንአል አበበ ሙሉጌታ | 52,000.00 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015278 | 02 | 165 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | ንብረት ተዋበ አሸነፍከ | 46,517.09 | 100% | | | | |
| | 3 | ኤልሻዳይ አለማየሁ ብሩ | 45,827.25 | 100% | | | | |
| 11 | 1 | አማኑኤል ምስጋናው ሽፈራው | 61,223.21 | 100% | LDR-YEK-MIX-00015279 | 02 | 92 | ከ100 ከፍተኛ ነጥብ በማምጣታቸው |
| | 2 | መሐመድ ሲራጅ ዳምጠው | 56,350.60 | 100% | | | | |
| | 3 | ምንተስኖት ዲንሳ ገመቹ | 55,060.00 | 100% | | | | |

# የአዲስ አበባ አዲስ መልክ

- **በኮሪደር ልማት የተሰሩ መንገዶች በፈረቃ አራት ጊዜ እየተጸዱ እንደሆነ ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

አዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያሳየች ባለው ፈጣን ልማትና ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የትላልቅ ጉባኤዎችና ስብሰባዎች መዳረሻነቷ እያደገ መጥቷል። ለዚህ የግማሽ ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተገመገመበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የተናገሩትን ለማሳያነት ማንሳት በቂ ነው፡፡ አዲስ አበባ ባለፉት ስድስት ወራት ከ150 በላይ ትላልቅ ኮንፈረንሶችን አስተናግዳለች፡፡ ዛሬ እና ነገ ደግሞ 39ውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤን ታስተናግዳለች፡፡

ከተማዋ እንደዚህ ዓይነት ትላልቅ ጉባኤዎችን ስታስተናግድ ከዚህ ቀደም በብዙ መልኩ ወቀሳና ትችት እንዲቀርብባት ምክንያት የነበረው የጽዳቷ ሁኔታ ነበር፡፡ የነበራት የጽዳት ሁኔታ ስሟን፣ ዝናዋን እና ሚናዋን የሚመጥን አልነበረም፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ጨምሮ በተለያየ ኃላፊነት ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲው መስክ ያገለገሉት አንጋፋው ዲፕሎማት አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን እንዳጋሩት፣ የአፍሪካ መሪዎች በህብረቱ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ወደ አዲስ አበባ በሚመጡበት ጊዜ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ አንስቶ የሚሰበሰቡበት አዳራሽ እስኪደርሱ ድረስ፣ ከመንገድ በግራና በቀኝ ያሉት ስፍራዎች በቆርቆሮ ይታጠሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም በመንገዱ ላይ ለእይታ ምቹ ያልሆኑ ቆሻሻ ስፍራዎች ነበሩ፡፡

ትውልድና እድገታቸው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ሜክሲኮ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን የሰጡት አቶ መሀመድ ከድር ይህንን ሀሳብ ይጋራሉ። አካባቢያቸው ከዚህ ቀደም የነበረው ጽዳትና ውበት ብዙ ጉድለቶች ያሉበት እንደነበር ያነሳሉ፡፡ ቆሻሻ በየመንገዱ ተዝረክርኮ፣ ዛፎች ቢኖሩ እንክብካቤ ስለማይደረግላቸው በአረም ተውጠው፣ አጥሮቹ ፈራርሰው፣ ቤቶች የተዥጎረጎረ ቀለም ተቀብተውና ውበታቸው ተደብቆ ይታይ ነበር፡፡

የከተማዋ የጽዳት ጉድለት በገጽታዋ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲፈጥር እንደቆየ እሙን ነው፡፡ ሆኖም በኮሪደር ልማቱ የእግረኛ፣ ሳይክልና የተሽከርካሪ ደረጃቸውን የጠበቁ መንገዶችን በመገንባት፣ በአረንጓዴ እፅዋትና አበቦች በማስጌጥ፣ ቤቶችን ተመሳሳይና ደረጃቸውን የጠበቀ ቀለም እንዲቀቡ በማድረግ ከተማዋን እንደ ስሟ አዲስ፣ ውብና ጽዱ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሜክሲኮ አካባቢ በመንገድ ዳር ከተሰሩ መቀመጫ ወንበሮች በአንዱ አረፍ ብለው ነፋሻማውን አየር እየተቀበሉ ያገኘናቸው አቶ አበጋዝ ተሰማ፣ አካባቢው ከዚህ ቀደም ከፍተኛ የሰው ትርምስ ያለበትና ጽዳቱም የተጓደለ እንደነበር



ፎቶ- በገነት ወንድሙ
ሜክሲኮ አካባቢ የመንገድ ፅዳት ስራ ሲከናወን

ያስታውሳሉ፡፡ በተለይ የመንገድ ዳር ንግድ በእግር ለመንቀሳቀስ አዳጋች፣ አቧራና ቆሻሻም ተዝረክርኮ ተጥሎ ይታይ ነበር፡፡

በኮሪደር ልማት ሰፋፊ የተሽከርካሪ፣ እግረኛና ሳይክል መንገዶች ተሰርተዋል፤ ዘመናዊ መብራቶች ተተክለዋል፤ ህንፃዎች በቀለም አሸብርቀዋል፤ የመንገድ አካፋዮች፣ በግራና ቀኝ በሳር፣ አበባና ዘንባባ ተውበዋል፡፡ ዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ስለተገነባም እንደበፊቱ ከቱቦ የሚወጣ የሚሰነፍጥ ሽታ እንደሌለ ይናገራሉ፡፡ "ከተማዋን ውብና ጽዱ ለማድረግ የተሰራውን ስራ አይደለም ማየት የሚችለው የማይችለው እንኳን በዳሰሳ ያውቀዋል፡፡ ይህ ለውጥ የመጣው በአጭር ጊዜ መሆኑ ደግሞ ያስገርማል። እኔ የምኖረው ጎተራ አካባቢ ነው። የስኳር ህመም ስላለብኝ ከጎተራ ወደ ሜክሲኮ መጥቼ እረፍት እያደረኩ በስታዲዬም ቦሌ ወሎ ሰፈር ዞሬ በእግሬ እንቅስቃሴ አደርጋለሁ፡፡ ይህንን የማድረገው መንገዶቹ ምቹና ፅዱ ስለሆኑ ነው" ሲሉ ይመሰክራሉ፡፡

አቶ አበጋዝ አክለውም፤ "ከዚህ ቀደም በውበቱና ጽዳቱ የሚጠቀሰው ቦሌ አካባቢ ነበር፡፡ አሁን ግን ሁሉም ቦሌን መስሏል፡፡ በብዙ አካባቢዎች ወንዞች በመጽዳታቸው እንደ በፊቱ መጥፎ ጠረንና ሽታ የለም፡፡ መንገድ ላይ ቆሻሻ ተጥሎ አይታይም፡፡ አዲስ አበባ አሁን ያላት ገፅታ ከበፊቱ ጋር በምንም ለውድድር የሚቀርብ አይደለም፡፡ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ አህጉርና ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በኩራት ለማስተናገድ ያስችላታል፤ በርግጥም ብዙ ስብሰባዎች እየተካሄዱባት ነው" ብለዋል፡፡

ከተማዋ በጽዳት ረገድ እያሳየች ያለው ለውጥ በዋና ዋና መንገዶች ብቻ የታጠረ አይደለም፡፡ በውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ ሰፈሮች ብሎም በሁሉም አካባቢ ነው፡፡ ወይዘሮ አያልነሽ ካሳው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ነዋሪ ናቸው፡፡ ደረቅ ቆሻሻን የሚበሰብስ፣ የማይበሰብስና አደገኛ በሚል በመለየትና በአግባቡ በማስቀመጥ፣ በሳምንት ሁለት ቀን ማክሰኞና አርብ ቤት ለቤት በሚሰበስቡ የጽዳት ሰራተኞች አማካኝነት እንዲወገድ እንደሚያደርጉ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር በየሳምንቱ ቅዳሜ በመውጣት ከሰፈራቸው ነዋሪ ጋር አካባቢያቸውን ያፀዳሉ፡፡ በዚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ የአካባቢያቸው የጽዳት ደረጃ እየተሻሻለ መምጣቱን ይገልፃሉ፡፡

ሌላኛዋ የሜክሲኮ አካባቢ ነዋሪ ወይዘሮ ጉዳዬ ተሰማም እንዲሁ የአካባቢያቸው የጽዳትና ውበት ሁኔታ እጅግ አስደሳች መሆኑን ይናገራሉ፡፡ አሁን ሜክሲኮ የማናውቃት እስኪመስለን ድረስ ጽዱና ውብ ሆናለች፡፡ ከመንገዶች ባሻገር መናፈሻዎች ስለተሰሩ ከልጆቼ ጋር በመሆን ቅዳሜና እሑድ በመሄድ እንጫወታለን፤ እንዝናናለን፤ መንፈሳችንን እናድሳለን ብለዋል፡፡

የአዲስአበባንጽዳትናውበትበመጠበቅ ረገድ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ከሆኑት መካከል የጽዳት ሰራተኞች ይገኙበታል። በከተማዋ ጽዳትና ውበት ላይ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚታይ ይናገራሉ፡፡ ወጣት ዘላለም አዲሱ ላለፉት አምስት ዓመታት በሜክሲኮ፣ በስታዲዬም፣ አጣና ተራና የተለያዩ መስመሮች የመንገድ ጽዳት ስራ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከዚህ ቀደም በከተማዋ መንገዶች ላይ ቆሻሻ በብዛት ይጣል ነበር፡፡ የመንገድ ዳር ንግድን ጨምሮ ከተለያዩ የንግድ ማዕከላትና ቡቲኮች የሚወጣ ቆሻሻ ለጽዳቱ መጓደል የራሱ አበርክቶ ነበረው፤ ህብረተሰቡ ስለጽዳት ያለው ግንዛቤም አላደገም ነበር፡፡

ኮሪደር ልማቱ ለጽዳት ስራው እገዛ እንዳደረገላቸው ወጣት ዘላለም ይናገራል። በአሁኑ ወቅት ከመንገድ ገባ ያሉና በመልሶ ማልማት የፈረሱ አካባቢዎች ላይ ከሚታዩ አንዳንድ የጽዳት መጓደሎች በስተቀር ልማቱ የደረሰባቸው አካባቢዎች ንፁህ፣ ጽዱና ውብ እንደሆኑ ገልጿል፡፡

እነዘላለም ሜክሲኮ አካባቢ ያሉ መንገዶችን በቀን ሦስት ጊዜ በፈረቃ እያፀዱ ይገኛሉ፡፡ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ በተሰራው ስራ አሁን ላይ በህገ ወጥ መንገድ ቆሻሻ የመጣል እንቅስቃሴዎች ቀንሰዋል፡፡

ወጣት ዘላለም ሌሊት 10፡30 ሰዓት ከገባ እስከ ቀኑ 5፡30 ሰዓት የጽዳት ስራውን ያከናውናል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከተማዋ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ እያስተናገደች እንደመሆኗ ለጽዳቱ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ሰዎች በብዛት የሚንቀሳቀሱባቸውን አካባቢዎች ተከታትሎ በማጽዳት፣ የሚለጠፉ ህገ ወጥ ማስታወቂያዎችን በማንሳት፣ በተጠንቀቅ በመቆም እንግዶች በከተማዋ የሚኖራቸው ቆይታ ያማረና አስደሳች እንዲሆን በመስራት ላይ ናቸው፡፡

በመንገድ ጥርጊያ የጽዳት አገልግሎት ላይ ተሰማርተው ያገኘናቸው ወይዘሮ የሽወርቅ መኩሪያም እንዲሁ የዛሬ አምስት ዓመት አዲስ አበባ በነበራት ጽዳትና አሁን ባለው መካከል ከፍተኛ ለውጥ እንደሚታይ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ቀደም ከተለያዩ ተቋማት፣ ከንግድ ቤቶች (ቡቲኮች) የሚጣሉ ቆሻሻዎች የመንገድ ጽዳት ላይ ፈተና እንደነበሩ እሳቸውም በአስተያየታቸው አጠናክረዋል፡፡

የመንገድ ዳር ንግድ እንቅስቃሴ ባለበት አካባቢ ይጣል የነበረው ቆሻሻ ብዙ ስለነበር በስራችን ላይ ጫና ፈጥሮብን ነበር፡፡ ኮሪደር ልማቱ ይህንን ማስቀረት በመቻሉ ከተማዋ ጽዱና ውብ ሆናለች ይላሉ፡፡

አቶ ግርማ ሞገሴ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት የጽዳት ስራዎች አስተባባሪ ናቸው፡፡ የመንገድ ጥርጊያ ጽዳት ሰራተኞች በየቀኑ በሦስት ፈረቃ ከሌሊት 10፡30 ሰዓት እስከ ምሽት ድረስ ይከናወናል፡፡ በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ደግሞ በሳምንት ሁለት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሦስት ጊዜ ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ ይሰበሰባል። በርካታ ተገልጋዮች ያሉባቸው እንደ ሆቴል ካሉ ድርጅቶች በየቀኑ የማንሳት ስራ ይከናወናል፡፡፡ በየቀኑ ማህበረሰቡ ደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ እንዲለይና የአካባቢውን ጽዳት እንዲጠብቅ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡ በየሳምንቱም ነዋሪው በንቅናቄ አካባቢውን እንዲያፀዳ እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

በወረዳው ከሜክሲኮ እስከ መስቀል አደባባይ ድረስ ያለው ዋና መንገድ በማሽን በመታገዝ የሚፀዳ ደረጃ አንድ መንገድ ነው፡፡ ሌሎች መንገዶች ደግሞ በሰው ሀይል አማካኝነት ይጸዳሉ፡፡ አቶ ግርማ እንደገለፁት፣ ከዚህ ቀደም ቆሻሻ በየመንገዱ ተጥሎ የሚታይበት ሁኔታ ሰፊ ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን በመንገድ ሆነ ከመንገድ ውጪ ቆሻሻ ማየት የማይቻልበት ሁኔታ እየተፈጠረ መጥቷል፡፡ የኮሪደር ልማቱ በተለይ የጽዳት ስራውን በማዘመን ትልቅ ለውጥ አምጥቷል፡፡

የአፍሪካ ህብረት ዋና ጽህፈት ቤት በሚገኝበት አካባቢ የሚገኝ ወረዳ እንደመሆኑ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ጽዱና ውብ በሆነ አካባቢ እንዲካሄድ ህብረተሰቡ የአካባቢውን ጽዳት እንዲጠብቅ ግንዛቤ በመፍጠርና መንገዶች ሁሌም ንፁህ ሆነው እንዲገኙ የዘወትር ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

## እንደ ከተማ ምን እየተሰራ ነው?

አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ በዓመት አንድ ጊዜ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤን ጨምሮ የተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉባኤዎችን እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ጉባኤዎችና ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ውብና ጽዱ እንድትሆን ሰፋፊ ስራዎችን እያከናወነች እንደምትገኝ በአዲስ አበባ ከተማ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የዋና ዳይሬክተር ዋና አማካሪ ወይዘሮ ሀዳስ ኪዱ ይገልፃሉ፡፡

መንገዶች አካባቢ ያሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ (ደስት ቢን) በየቦታው መኖራቸውን የማረጋገጥ፣ የተበላሹትን የመጠገንና የማስተካከል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጽዳታቸውን የጠበቁ፣ እንግዶች በብዛት የሚንቀሳቀሱባቸውን ቦታዎች በመለየት የሚያርፉባቸው ሆቴሎችና የእንግዳ ማረፊያዎች ጽዱና ውብ እንዲሆኑ የሚመነጨውን ቆሻሻ 24 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ እንዲነሳና እንዲጓጓዝ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ዋና አማካሪዋ እንደሚገልፁት፣ የኮሪደር ልማት የተከናወነባቸውም ሆነ ያልተከናወነባቸው መንገዶች ጽዱና ውብ ሆነዋል፡፡ እናቶች፣ ሴቶችና ወጣቶች ሌሊት ከቤታቸው 10፡00 ሰዓት በመነሳት እስከምሽቱ 1፡30 ሰዓት ድረስ በአራት ፈረቃ (እንደየመንገዱ ሁኔታ የሚለያይ ሆኖ) ያፀዳሉ፡፡ የፅዳት ስራው የመብራት ችግር እንደበፊቱ ባለመኖሩ ከሌሊት ጀምሮ እስከ ማታ ይሰራል፡፡ ከዚህ በፊት ከነበረው ሦስት ፈረቃ በተጨማሪ አንድ ተጨምሮ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በኮሪደር

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

# የአፍሪካ ከተሞች ተምሳሌት ፡- አዲስ አበባ

- **ከተማን ለሰው ልጆች ምቹ ከማድረግ አንጻር አዲስ አበባ እያከናወነች ያለው ተግባር የሚደነቅ መሆኑ ተጠቁሟል**

**በደረጀ ታደሰ**

ባለፉት ጥቂት ዓመታት አዲስ አበባ የምስራቅ አፍሪካ የንግድ እና የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን ብቻ ሳይሆን፣ አህጉራዊ የከተማ ልማት ፋና ወጊነቷን በተግባር እያስመሰከረች ትገኛለች። ከተማዋ እያከናወነችው ያለው ግዙፍ የኮሪደር ልማት፣ የፓርኮች ግንባታ እና የወንዞች ዳርቻ ማሻሻያ ፕሮጀክቶች በዓለም አቀፍ ተቋማት እና በጎረቤት ሀገራት ዘንድ እንደ "ተአምራዊ ሽግግር" ተቆጥሯል። ዛሬ አዲስ አበባን የሚጎበኙ አፍሪካውያን መሪዎች፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት ኃላፊዎና ተወካዮች፣ የከተማ ፕላን ባለሙያዎች እና ሌሎች እንግዶች በአዲስ አበባ የሚኖራቸውን ቆይታ አጠናቅቀው የሚመለሱት በቃላት የሚገለጽ አድናቆትን በማቅረብ ብቻ አይደለም፤ ለሀገራቸው እና ከተሞቻቸው የሚሆን አዲስ የልማት ርዕይንም ሰንቀው ነው።

በቅርቡ፣ ማለትም በወርሃ ጥር አጋማሽ 2018 ዓ.ም. ላይ በአፍሪካዊያኑ መዲና፣ አዲስ አበባ አንድ ሁነት ተከናውኗል። ይህ ሁነት የተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች እና የክልል አስተዳዳሪዎች የተሳተፉበት የመማማሪያ መድረክ ነው፡፡ የሁነቱ መነሻ ምክንያት ከአዲስ አበባ ዘርፈ ብዙ ስኬት የሚመነጭ ነው፡፡ በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (UNECA) አማካኝነት በአፍሪካ ከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር (Financial Management) አፈፃፀም ላይ በተካሄደው ጥልቅ የዳሰሳ ጥናት መሠረት፤ አዲስ አበባ ከተማ ከተመዘነችባቸው 6 መስፈርቶች ውስጥ በ5ቱ የላቀ አፈፃፀም በማስመዝገቧ እና የስኬቷን ልምዷን እንድታካፍል በመመረጧ ነው፡፡

ከአዲስ አበባ ከንቲባ ፅሕፈት ቤት ያገኘነው መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ጥናቱ አዲስ አበባን ጨምሮ በስድስት የአፍሪካ ሀገራት ከተሞች ላይ ተካሂዷል። እነዚህ ከተሞች፡- የኬንያዋ ናይሮቢ፣ የታንዛኒያዋ ዳሬሰላም፣ የዛምቢያዋ ሉሳካ፣ የሩዋንዳዋ ኪጋሊ እና የካሜሮኗ ያውንዴ ናቸው፡፡ ከከተሞቹ መካከል አዲስ አበባ የተሻለ አፈፃፀም በማስመዝገብ ቀዳሚ መሆን ችላለች። በተለይም የገቢ እና የፋይናንስ ሀብት አስተዳደርን በማዘመን ረገድ የጀመረችው ሪፎርም ውጤታማና ለአፍሪካ ከተሞች አርአያ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አረጋግጧል።

የአዲስ አበባን ስኬታማ ተሞክሮ ያካፈሉት ከንቲባ አዳነች አቤቤም፤ በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (UNECA) አማካኝነት በአፍሪካ ከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር (Financial Management) አፈፃፀም ላይ የተደረገው የጥናት ውጤት የሚያረጋግጠው የአዲስ አበባን ስኬታማነት መሆኑን ገልፀዋል። "ይህ ስኬት፤ ከተማችን ከምትሰበስበው አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 71 በመቶውን ለልማት ሥራዎች በመመደብ፣ የዜጎችን ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ስናደርግ የቆየነው የሪፎርም ጉዞ ውጤታማነት ማሳያ



ፎቶ- ከገፀ ድር

አዲስ አበባ በፋይናንስ እና በገቢዎች ሥራ አቅሟን ገንብታ ወደ ተግባራዊ ለውጥ የቀየረችበትን መንገድ በተሞክሮነት ባጋራችበት ወቅት

ነው፡፡ ከተለያዩ ከተሞች ለልምድ ልውውጥ የመጡት ተሳታፊ ከንቲባዎች እነዚህን የሪፎርም ሥራዎች በአካል በመጎብኘት፣ አዲስ አበባ በፋይናንስ እና በገቢዎች ሥራ አቅሟን እንዴት ገንብታ ወደ ተግባራዊ ለውጥ እንደቀየረችው ሰፊ ተሞክሮ አጋርታለች" ብለዋል፡፡ መድረኩ የአፍሪካ ከተሞች የወደፊት ዕጣ ፈንታ በጋራ የሚቀረጽበት ታሪካዊ አጋጣሚ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

በአፍሪካዊያን እና በሌሎች የዓለም ሀገራት ላይ የከተማ ልማት ተምሳሌት ተደርጋ እየተወሰደች ያለችው አዲስ አበባ፤ የጁባ እና ናይሮቢ ከተሞች ከፍተኛ አመራሮችንና ልዑካንን በስኬታማ ሥራዋ ስባ ማምጣቷን በአብነትነት መጥቀስ እንችላለን፡፡ ለጉብኝታው መነሻው፣ ከ2010 ዓ.ም. በኋላ በከተማዋ ተዓምራዊ ለውጥ እያመጣ ያለው የኮሪደር ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ እና ተያያዥ ውጤታማ ሥራዎች ናቸው፡፡ የደቡብ ሱዳን ከፍተኛ የልዑካን ቡድን አዲስ አበባን በጎበኙበት ወቅት፣ ዋና ከተማቸው ጁባን ለማዘመን የአዲስ አበባን የኮሪደር ልማት እንደ ዋና መመሪያ ለመጠቀም መወሰናቸውን ገልጸዋል። የደቡብ ሱዳን አመራሮች በተለይ የተደነቁት በህንፃዎቹ ውበት ብቻ ሳይሆን፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ ስራን የመጨረስ የአመራር ጥበብን ነው። "ይህ ለአፍሪካ ከተሞች አዲስ ተስፋ ነው" በማለት ምስክርነታቸውን የሰጡት እነዚህ አመራሮች፣ ኢትዮጵያ የራሷን የውስጥ አቅም ተጠቅማ እንዲህ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መፈጸሟ ለጁባ እድገት ትልቅ ትምህርት መሆኑን ማረጋገጣቸው ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ፣ የናይሮቢው ገዢ ጆንሰን ሳካጃ አዲስ አበባን በጎበኙበት ወቅት በሰጡት አስተያየት፣ አዲስ አበባ "ከተማን ለሰው ልጆች ምቹ ማድረግ" የሚለውን መርህ በተግባር ያሳየችበት መንገድ አድንቀዋል። ናይሮቢ አሁን ላይ የጀመረችውን የኡሁሩ ፓርክ እድሳት እና የናይሮቢ ወንዝን የማጽዳት ፕሮጀክት ከአዲስ አበባው የ"ገበታ ለሸገር" እና የፓርኮች ልማት ጋር የተቆራኘ መሆኑን የኬንያ ሚዲያዎች በዘገባዎቻቸው በስፋት እየመሰከሩ ይገኛሉ።

የዓለም ባንክ እና ሌሎች ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች የአዲስ አበባን በዓይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ፣ በአፍንጫ የሚሸተት፣ "ሠው ተኮር" የልማት ፕሮጀክት ውጤትን በቸልታ የሚያልፉት አልሆነም። ይልቁንም፤ ለአዲስ አበባ ውጤታማ ሥራ ዕውቅና ከመስጠት ባሻገር ሌሎች እንዲማሩበት ልምድ የሚቀምሩባት የልማት አውድማ ሆናቸዋለች፡፡ ለዚህም ነው፤ የዓለም ባንክ አዲስ አበባን "ፈጣን ሽግግር እያደረገች ያለች ከተማ" በማለት የሚገልጻት። በተፈጥሮ ሃብትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን ያደረገው "ዩኤን-ሃቢታት (UN-Habitat)" የተሰኘው ዓለም አቀፍ ተቋም በበኩሉ፤ የአዲስ አበባን የወንዝ ዳርቻ ልማት ለአካባቢ ጥበቃ እና ለከተማ ኑሮ ጥራት እንደ "ምርጥ ተሞክሮ" (Best Practice) ወስዶ ለሌሎች የአፍሪካ አገራት በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል።

የከተማ ልማት አፍሪካዊት ፈርጥ ተደርጋ እየተወሰደች ስላለችው አዲስ አበባ፣ በምሁራዊ ዕይታ ተመልክተው የውጤታማነት ምስጢሩ ምን እንደሆነ እንዲያስረዱን፣ በኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ልማትና ጥናት ኮሌጅ ምክትል ዲንና መምህር ሄርጳ በሪሶን (ዶ/ር) አነጋግረናቸዋል። እሳቸውም፤ "ይህ ዘመን የከተሜነት ዘመን ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተሞች በጣም እየተስፋፉ ነው፡፡ የሠዎች የመኖሪያ መዳረሻ ከተሞች እየሆኑ ነው። በበለፀጉት ሀገራት በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ 90 ከመቶ ደርሷል። አፍሪካ እንደ አህጉር የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ቁጥር 40 ከመቶ አካባቢ ሆኗል፡፡ በኢትዮጵያ ያለው ድርሻ 25 ከመቶ አካባቢ ነው" በማለት ስለ ከተማና ከተሜነት አሁናዊ ሁኔታ አጭር መግለጫ በመስጠት ማብራሪያቸውን ጀምረዋል፡፡

አክለው እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ መንግስት ዘመኑን የተረዳ የመሆኑ ማሳያው በአዲስ አበባ እየተከናወነ ያለው ሁሉን አቀፍ የከተማ ልማት ሥራ ነው። ልማቱን ከሌላው ለየት የሚያደርገው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሠፊ እና ግዙፍ ሥራ መሠራቱ ነው። በዚህም ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ችሏል፡፡

"በአዲስ አበባ የተከናወነውና እየተከናወነ ያለው ልማት ሠው ተኮር ነው፡፡ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ መሰረተ ልማቶችን አስፋፍቷል፤ አዘምኗል፡፡ የሕዝብ መዝናኛ እና ማረፊያ ሥፍራዎችን አበራክቷል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ሽፋንን አሳድጓል፡፡ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ከአደጋ የሚጠበቁበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ይህ ደግሞ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ፅዱ እና ውብ እንድትሆን ትልቅ ሚና ይጫወታል" ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ሄርጳ በሪሶ (ዶ/ር)፤ ከተሜነት ከሚገለጽባቸው መመዘኛዎች መካከል፡- የአገልግሎት አሠጣጥ መዘመንና መሻሻል ሌላኛው ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት አገልግሎትን በዲጂታል ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ የማድረጉ ጅምር በጣም የሚበረታታ ነው፡፡ በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተሠራ ጥናት ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ተሸላ እንድትገኝ፣ ተሞክሮዋንም ለሌሎች እንድታካፍል ያደረጋት ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የፋይናንስ አስተዳደሯ በማሳያነት የሚጠቀስ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

"አዲስ አበባ ከተማ እያሳየች ባለችው ውጤታማ የልማት እንቅስቃሴ የብዙዎችን ቀልብ እየሳበች ነው። የአፍሪካ ከተሞች የልማት ሞዴል ተደርጋም እየቀረበች ነው። አድናቆቱ ሊመጣ የቻለው በአዲስ አበባ የከተማ ልማት ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግዙፍ ልማት መከናወኑና ለውጥ መምጣቱ ነው፡፡ ይህ ዓለም አቀፍ ምስክርነት አዲስ አበባን በይበልጥ ለማስተዋወቅ፣ የከተማዋን ልማትና የቱሪዝም ተጠቃሚነት ለማሳደግ ትልቅ አቅም ይፈጥራል" በማለት የገለፁት ሄርጳ (ዶ/ር)፤ በከተማዋ እየታየ ያለውን የልማት ለውጥ ለማስቀጠልና ዘላቂ ለማድረግ መሠራት ይገባቸዋል ያሏቸውን ምክረ ሃሳቦች አመላክተዋል። የተሠሩ፣ እየተሠሩ ያሉና በቀጣይነት የሚሠሩ የልማት ፕሮጀክቶች በጣም ሰፊና ግዙፍ ናቸው፡፡ እነዚህን የልማት ሥራዎች የሚያስተዳደር፣ የሚከታተል፣ ጥገናና ማሻሻያ የሚያደርግ ጠንካራ ተቋማዊ አቅም መገንባት ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን የልማት ሥራውን አካታችነት የበለጠ ማጠናከር ይገባል፡፡ በልማቱ ላይ የሕዝብ፣ የግል ተቋማትን፣ የባለሃብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

# የመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መርሃ ግብር መቅረባቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ከተሰናዱት መካከልም የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ እና የመጽሐፍት ውይይት ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍ

የአንጋፋው ደራሲና ጋዜጠኛ አበራ ለማ ግለ-ታሪክ መጽሐፍ ከሰሞኑ ለንባብ ይበቃል፡፡ “እንዲህም ተኑሯል” የሚል ርዕስ ያለውና በ550 ገፆች የተቀነበበው የዚህ መጽሐፍ ምረቃ ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት (ወመዘክር) አዳራሽ ከቀኑ 8 ሰዓት ይካሄዳል ተብሎ የነበረ ቢሆንም በአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ምክንያት መራዘሙ ተገልጿል፡፡ አበራ ለማ ከሀገራችን ገጣሚያንና አጫጭር ልብ-ወለድ ጸሐፊዎች አንዱ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ጥናት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመርቋል።

አበራ፣ በ1967 ዓ.ም “ኩል ወይስ ጥላሸት” እንዲሁም በ1974 ዓ.ም “ሽበት” የተሰኙ የግጥም መድብል ስራዎችን ለህትመት አብቅቷል፡፡ ከዚያም “ሕይወትና ሞት” የተሰኘ የአጫጭር ልብ-ወለዶች ስብስብ፣ ቀጥሎም “ሞገደኛው ነውጤን” አሳትሟል፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ስራዎችንም በግሉና በጋራ አበርክቷል፡፡

## የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ

ኢትዮጵያ በ1920ዎቹ በጀርመናዊ ዲፕሎማት “እይታ” በሚል ርዕስ የፎቶ ግራፍ ዓውደ ርዕይ እየታየ ነው፡፡ ዓውደ ርዕዩ በወቅቱ በኢትዮጵያ የጀርመን መልዕክተኛ በነበሩት በሚስተር ፍሪትዝ ዊይስ (Fritz Weiss) እና ባለቤታቸው ሄድዊግ የተቀረጹ 51 ፎቶ ግራፎች እና ቪዲዮዎች የቀረቡበት ነው፡፡ እነዚህ ምስሎች ከቀድሞዋ አዲስ አበባ ከተማ እይታዎች ጀምሮ እስከ ደመቅ ያሉ ባህላዊ በዓላት እና አስደናቂ ገጠራማ ስፍራዎች ድረስ የያኔውን የኢትዮጵያ የዕለት ተዕለት ሕይወት በቅርበት ያሳያሉ ተብሏል፡፡ አውደ ርዕዩ እየታየ የሚገኘው ሃያት ሬጀንሲ በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን በመጪው ሰኞ ይጠናቀቃል፡፡

## ፊልም

“ይቅር ባይ” የተሰኘውና በዛክ ፒክቸርስ ተዘጋጅቶ በኤልያና ኢንተርቴይመንት የቀረበው የዘካርያስ ወንድይፍራው አዲስ ፊልም ከትናንት ጀምሮ ለተከታታይ ሦስት ቀናት በተመረጡ ሲኒማ ቤቶች እየተመረቀ ይገኛል።

ፊልሙ ትናንት ከኤግዚቢሽን ማዕከል ጎን በሚገኘው አዲሱ ሕፃናትና ወጣቶች ቴአትር አዳራሽ በቀይ ምንጣፍ ስነ-ስርዓት የፊልም አፍቃሪያን፣ የኪነ - ጥበብ ባለሙያዎች እና ሚዲያዎች በተገኙበት የተመረቀ ሲሆን፤ ነገም በተመረጡ ሲኒማ ቤቶች መመረቁን ይቀጥላል፡፡ በፊልሙ ላይ ካሳሁን ፍስሐ (ማንዴላን) ጨምሮ አንጋፋና ወጣት ተዋናያን ተሳትፈውበታል፡፡

## ሙዚቃ

የወጣት ሶሲ ግርማ አዲስ ሙዚቃ ለአድማጭ ተመልካች ይፋ ሆነ። “አይጣል” የተሰኘው ይህ የፍቅር ሙዚቃ ትናንት ምሽት በናሆም ሬከርድስ አማካኝነት ለህዝብ ደርሷል፡፡ በዚህ ስራ በግጥም ፍሬዘር አበበወርቅ፣ ዜማ ብሩክ ጃኔ እና በሙዚቃ ቅንብር ብሩክ ተቀባ ተሳትፈውበታል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎቸ በከፊል

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት በወቅታዊ ስራ ምክንያት የቁጥር ጨዋታ ይዘን ባለመቅረባችን ይቅርታ እንጠይቃለን። በዚህም ቅዳሜ ጥር 23 ቀን 2018 ዓ.ም አቅርበንላችሁ ለነበረው ጥያቄ ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል። የመጀመሪያው (2 x 9) – (5 x 3) = 3 ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ (9 x 5) – (3 x 13) = 6 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት ሶስተኛውና የመጨረሻው (7 x 8) – (5 x 6) = 26 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **26** ነው፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የአንድነት መዝሙር - የነፃነት ዜማ

በአብርሃም ገብሬ

ብሔራዊ መዝሙር (Anthem) የአንድ ሀገር ሕዝቦች የጋራ ማንነት፣ ታሪክ፣ እምነትና ተስፋ በዜማና በግጥም የሚገለጽበት ዓርማ ነው። ልክ እንደ ሰንደቅ ዓላማ ሁሉ፣ ብሔራዊ መዝሙር የሀገር ሉዓላዊነትና የአንድነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል።

በአንድ ሀገር ወይም አህጉር ውስጥ የተለያዩ ማኅበረሰቦች፣ ቋንቋዎችና እምነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ብሔራዊ መዝሙር ግን እነዚህን ልዩነቶች አሰናኝቶ “እኛ” የሚል የወል ማንነት ይፈጥራል። ዜጎች መዝሙሩን በአንድ ላይ ሲዘምሩ፣ የግል ማንነታቸውን ወደ ጎን ትተው ለሀገራዊ ወይም አህጉራዊ ማንነታቸው ቅድሚያ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ይህ ድምፅ የወል ማንነት መገለጫም ነው። የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ይህንን መነሻ በማድረግ የአፍሪካ ሕብረት መዝሙርና በውስጡ የያዛቸው አንኳር መልዕክቶች ላይ አጭር ዳሰሳ አድርጓል።

## የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር እንደ የወል ዜማ

ብሔራዊ መዝሙር ለአንድ ሀገር የሉዓላዊነት ምልክት፣ የታሪክ ማኅደር እና የሕዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ እንደሆነ ሁሉ፣ አህጉራዊ መዝሙርም የሚሊዮኖች ድምፅና የጋራ ዕጣ ፈንታ መግለጫ ነው። የታሪክና የተጋድሎ ማስታወሻ ተደርጎ የሚወሰደው የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር “Let Us All Unite and Celebrate Together” (ሁላችንም በአንድነት እንዘምርና እናክብር) በሚል መሪ ሐሳብ ይታወቃል።

የመዝሙሩ ግጥምና ዜማ የአህጉሪቱን ያለፈ ታሪክ በጥልቀት ይዘክራል። አፍሪካ የሰው ልጅ መገኛ ከመሆኗም በላይ፣ ለዘመናት የቅኝ አገዛዝን መራር ጽዋ የቀመሰች አህጉር ናት። መዝሙሩ ይህንን ያለፈውን ዘመን በማስታወስ፣ አፍሪካውያን በጋራ ታግለው ያገኙትን ነፃነት በኩራት እንዲያወሱ ያደርጋል።

የመዝሙሩ ስንኞች የአፍሪካን ልጆች ተጋድሎና ለነፃነት የተከፈለውን መሥዋዕትነት ይዘክራሉ። ይህም ለአዲሱ ትውልድ ነፃነት በዋጋ የተገኘ መሆኑንና ይህንን ነፃነት የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት ያስገነዝባል። ታሪክን መዘከር ብቻ ሳይሆን፣ ካለፈው ቁስል ተፈውሶ ለአዲስ ጉዞ መነሳሳትን የሚሰብክ የድል አዋጅ ነው - የሕብረቱ መዝሙር።

ሌላው የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር ካለፈው ታሪክ ይነሳና ስለ ወደፊቱ ብሩህ ተስፋ ያመለክታል። የአህጉሪቱን የኢኮኖሚ ጥንካሬ፣ የፖለቲካ አንድነትና የሕዝቦችን ብልፅግና እንደ ትልቅ ራዕይ ያስቀምጣል። “አፍሪካን የሰላም እና የብልጽግና ምድር እናድርጋት” የሚለው መልዕክት ዜጎች ለሀገራቸው ብቻ ሳይሆን ለአህጉራቸው ዕድገት እንዲተጉ ያነሳሳል።

## የጋራ ታሪክና ነጻነት ሲዘከር

የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር የተጻፈው በኢትዮጵያዊው ባለቅኔ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን ነው። ሙዚቃውን ያቀናበረው ደግሞ ኬንያዊው አርተር ሙዶጎ ከሞሊ ነው። የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር ለአፍሪካ አህጉር የታሪክ፣ የአንድነት፣ የተስፋ እና የእድገት ምልክት ሆኗል።



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአፍሪካ ህብረት የአንድነትና የነፃነት ምልክትነት ከሚያሳዩት መካከል የህብረቱ መዝሙር ተጠቃሽ ነው

ሁለቱ አፍሪካውያን ከያኒዎች የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር የአፍሪካውያንን ሕብረት የሚያበረታታ፣ አንድነት፣ ኩራት እና ብሩህ ተስፋን የሚፈጥር መዝሙር ለመሥራት ጥረት አድርገዋል።

ከሕብረቱ የመዝሙር ስንኞች እየመዘዝን የመዝሙሩን አንኳር መልዕክቶች አብረን እንመልከት፡-

“Let us all unite and celebrate together
The victories won for our liberation
Let us dedicate ourselves to rise together
To defend our liberty and unity...”

ይህ ግጥም መልዕክቱ ወደ አማርኛ ሲመለስ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

(በአሸናፊነታችን ነጻነታችንን ተጎናጽፈናል
ሁላችንም ተባብረን በጋራ ነጻነታችንን እናክብር
በጋራ ለማደግ በቁርጠኝነት እንጠንክር
ነፃነታችንን እና አንድነታችንን ለማስጠበቅ እንተባበር... ።)

ከላይ የሰፈሩት ስንኞች ከሕብረቱ መዝሙር ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ስንኞቹ በውስጣቸው ጥልቅ መልዕክት ይዘዋል። ለአብነትም “በአሸናፊነታችን ነጻነታችንን ተጎናጽፈናል”(The victories won for our liberation) የሚለው ስንኝ፣ የአፍሪካን ያለፈ ታሪክ የሚዘክር ነው። ነፃነት በስጦታ የተገኘ ሳይሆን በታላቅ አሸናፊነት እና ተጋድሎ የመጣ መሆኑን አጽንኦት ይሰጣል። አፍሪካውያን የቅኝ ግዛትን ቀንበር የሰበሩት በጀግንነት መሆኑን በመግለጽ፣ በትውልዱ ውስጥ የበታችነት ስሜት እንዳይኖር በማድረግ በኩራት እንዲሞሉ ያደርጋል።

የመዝሙሩ መግቢያ ላይ “ሁላችንም ተባብረን በጋራ ነጻነታችንን እናክብር”(let us all unite and celebrate together) ይላል። ይህ ትኩረቱን ያደረገው “አንድነት” ላይ ነው። ነፃነትን ብቻውን ማክበር አይቻልም፤ እውነተኛ ደስታ የሚገኘው መላው አህጉር በአንድነት ሲቆም ነው።“celebrate” (ማክበር) የሚለው ቃል ነፃነትን እንደ ትልቅ ስኬት እንድንመለከተው ያደርጋል፡፡

“በጋራ ለማደግ በቁርጠኝነት እንጠንክር” (Let us dedicate ourselves to rise together) የሚለው ስንኝ ደግሞ፣ ከፖለቲካዊ ነፃነት ባለፈ ወደ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ያተኩራል። “Rise” (መነሳት/ማደግ) የሚለው ቃል አፍሪካ ካለችበት የድኅነት አዙሪት ወጥታ ወደ ከፍታ የመውጣት ራዕይን ያሳያል። ይህም ዕድገት በምኞት ብቻ ሳይሆን በ“ቁርጠኝነት”(Dedication) የሚመጣ፣ ዕድገቱም ግለሰባዊ ሳይሆን የጋራ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል።

“ነፃነታችንን እና አንድነታችንን ለማስጠበቅ እንተባበር” (To defend our liberty and unity) የሚለው ስንኝ መከላከያ ወይም ጥበቃ ላይ ያተኩራል። ነፃነትን ማግኘት አንድ ነገር ሲሆን፣ አስጠብቆ መቆየት ደግሞ ሌላ ትልቅ ስራ ነው። አፍሪካውያን ያገኙትን ነፃነትና አንድነት የሚቀሙ የውስጥና የውጭ አደጋዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህን አደጋዎች ለመከላከል ደግሞ ብቸኛው መሣሪያ መተባበር መሆኑን ይገልጻል።

## አፍሪካን እንደ ሕይወት ዛፍ

የአፍሪካ ሕብረት መዝሙር ውስጥ ታሪክን ብቻ ሳይሆን አፍሪካ በውስጧ የያዘቻቸውን እንቁዎች ጭምር ያወሳል። አፍሪካን “በሕይወት ዛፍነት” ይመስላታል። ለአብነትም የሚከተሉትን ስንኞች እንመልከት፡-

“O Sons and Daughters of Africa
Flesh of the Sun and Flesh of the Sky
Let us make Africa the Tree of life
Let us all unite and sing together
To uphold the bonds that frames our destiny
Let us dedicate ourselves to fight together
For lasting peace and justice on the earth...”

(የአፍሪካ ልጆች ሆይ
የጸሐይና የሰማይ ቀለማት
አፍሪካን የሕይወት ዛፍ እናድርጋት
ሁላችንም ተባብረን በጋራ እንዘምር
ዕጣ ፈንታችንን የሚያጎናጽፉንን ማሰሪያዎች እናጠንክር
በጋራ ለመታገል ራሳችንን እናዘጋጅ
በምድር ላይ ዘላቂ ሰላምና ፍትሕ እንዲኖር...።)

ከላይ የሰፈሩት የግጥም ስንኞች አፍሪካ የወጣቶች መገኛ ምድር እንደመሆኗ፣ ለኑሮ ምቹ፣ ውብ፣ ማራኪና የሰከነ ህይወት የሚኖርባት ምድር እናድርጋት ይላል። ስንኞቹ መዝሙሩን ከታሪክና ከፖለቲካዊ ገጽታው ባሻገር ወደ መንፈሳዊ እና ተፈጥሯዊ ትስስር ከፍ ያደርጉታል። “የፀሐይና የሰማይ ቀለማት” (Flesh of the Sun and Flesh of the Sky) የሚለው አገላለጽ አፍሪካውያን ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ጥልቅ ቁርኝትና የከበረ ማንነት ይገልጻል። አፍሪካን እንደ “ህይወት ዛፍ” (Tree of Life) የመመሰል ርዕይ ደግሞ አህጉሪቱ ለልጆቿ መጠለያና መረጋጋትን የምትሰጥ ምድር እንድትሆን የሚያልም ነው።

“እጣ ፈንታችንን የሚያጎናጽፉንን ማሰሪያዎች እናጠንክር” (To uphold the bonds that frame our destiny) የሚለው ስንኝ በውስጡ ጥልቅ መልዕክት ይዟል። ስንኙ ውስጥ “ማሰሪያዎች” (Bonds) ተብለው የተገለጹት የአፍሪካውያን የጋራ እሴቶች፣ ባህሎችና የታሪክ ትስስሮች ናቸው። ይህም አፍሪካውያንን የሚያስተሳስራቸው ነገር ከሚለያያቸው ነገር እንደሚበልጥ ይነግረናል። የጋራ እጣ ፈንታችን (Destiny) የተገነባው በእነዚህ ማሰሪያዎች ላይ በመሆኑ፣ እነሱን መጠበቅና ማጠናከር የህልውና ጉዳይ መሆኑን የግጥሙ ስንኝ ያስገነዝባል።

በአጠቃላይ፣ የአፍሪካ ህብረት መዝሙር የአህጉሪቱ የነፃነት፣ የአንድነትና የተስፋ ምልክት ነው። ያለፈውን ታሪክ በማስታወስ፣ የአሁኑን ማንነት በማረጋገጥና የወደፊቱን ብሩህ መንገድ በመጠቆም ረገድ የሚጫወተው ሚና የማይተካ ነው። መዝሙሩ የድምፅና የዜማ ስብስብ ብቻ ሳይሆን፣ የአፍሪካውያን የጋራ የልብ ዜማ ነው ሊባል ይችላል።

**ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ**

# ፈጠራን የመጠቀም ብልሃት

**በሄለን ጥላሁን**

ገና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ነበር አዳዲስ የፈጠራ ሐሳቦችን በማመንጨት ከሥራ ጠባቂነት ለመላቀቅ ጥረት ማድረግ የጀመሩት፡፡ አካባቢያቸውን መቃኘት፣ ያለውን ፀጋ መለየት፣ ከችግር ውስጥ መፍትሔን የመሻትን መሰጠት በተግባር መለወጥ፣ "ሥራ ለሠሪው…" የትም እንዳለ ሠርቶ ማሳየት ለመቻል ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ እንዲሉ፤ በማኅበር በመደራጀት በዚህ ደረጃ የሚገለጥ ሥራ ማከናወን የቻሉት ወጣት ዮሐንስ ቡልቲና ጓደኞቹ ናቸው፡፡ በአጃክስ ማምረት እና የተማሪዎች የካፌ አገልግሎት በመስጠት በጋራ ተደራጅተው እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

የማኅበሩ መስራች አባል የሆነው ወጣት ዮሐንስ ቡልቲ ስለ ማኅበሩ አመሠራረት እና ተያያዥ ጉዳዮች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጸው፤ ሐሳቡን ካመነጩ በኋላ ወደ ውጤት ለመለወጥ የሚያስችላቸውን ዕቅድ አወጡ፡፡ ዕቅዳቸውን ወደ ተጨባጭ ውጤት ለመለወጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተወያዩ፡፡ ከዚያም ገንዘብ እና ሙያዊ ሥልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ተስማሙ፡፡ ከቤተሰብ ገንዘብ በመበደር የኬሚካል አሠራር ሙያዊ ሥልጠና በመውሰድ አጃክስ ሳሙና፣ ላርጎ የመሳሰሉ የንፅህና መጠበቂያ ምርቶችን ወደ ማምረት ገቡ፡፡

ይህንን የሥራ ዘርፍ የመረጡበትን ምክንያት ወጣት ዮሐንስ ያስረዳው፤ "የማኅበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማቅለል የሚያስችሉ መፍትሔዎችን ለማምጣት ሲያስቡ በቅድሚያ ከግምት ውስጥ ያስገቡት ጉዳይ ጥራትንና ዋጋን ነበር፡፡ አጃክስ በባሕርዩ እጅ ነጭ ያደርጋል፡፡ ኬሚካሉም ለቆዳ የማይስማማ በመሆኑ በጣም ያሳክካል። ከዚህ በተጨማሪም በተከፈለው ዋጋ ልክ ጥራት ያለው ምርት ማኅበረሰቡ ለማግኘት የማይችልበት አግባብ መኖሩን በማስተዋል ችግሮቹን ለመፍታት በማሰብ ነው ወደ ሥራው የገባነው" በማለት ነው።

ሐሳቡን ወደ ሥራ መለወጥ የቻሉት ወጣት ዮሐንስ እና ጓደኞቹ፤ ፋክክር በበዛበት ዐውድ ውስጥ የሚያመርቱት የንፅህና መጠበቂያ ምርት እና የሚሰጡት የካፌ አገልግሎት በገበያው ላይ አሸናፊ ሆኖ እንዲዘልቅ ራሳቸውን በዕውቀትና በክህሎት እያበቁ መጓዝ ግድ ይላቸዋል፡፡ እነሱም ይህንን በመገንዘብ በአካባቢያቸው ወዳለው አንጋፋው የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በማቅናት የተለያዩ ድጋፎችን ለማግኘት ችለዋል፡፡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁም አጫጭር የቢዝነስ ሐሳቦችን ሥልጠና መስጠትንና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ እንዲህ ዓይነት የፈጠራ ሐሳብ ያላቸውን ሰዎች እንደሚያበረታታ ማወቃቸው የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን አስችሏቸዋል፡፡

ወጣት ዮሐንስ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ያደረገላቸውን ድጋፍ "ኮሌጁ ለአዳዲስ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦች የሚያደርገው ድጋፍ በቅድሚያ ገንቢ እና አበረታች ሞራል ከመስጠት የሚጀምር በመሆኑ ይበልጥ እንድንበረታታ አግዞናል፡፡ የሥራ ሐሳቡን ካቀረብን በኋላ የቢዝነስ ሐሳቦች ምን እንደሆኑ ሥልጠና በመውሰድ አዋጭነት ባለው አካሄድ ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ አግኝተናል፡፡ የቴክኒካል ድጋፍ ጭምር ተደርጎልናል፡፡ በብር ሲተመን 350 ሺህ ብር የሚያወጣ ማሽን ኮሌጁ ሠርቶ አስረክቦናል፤ የማሽን ብድሩን በአራት ዓመት ክፍያ የሚፈጽሙበትን አግባብ አመቻችቶላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኮሌጁ ውስጥ የመሥሪያ ቦታ ድጋፍ ተደርጎልናል" ሲል ገልጾታል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

ለዮሐንስ ቡልቲ እና ጓደኛው ኮሌጁ ሰርቶ ያስረከባቸው የአጃክስ መሥሪያ ማሽን

ኮሌጁ የሠራላቸውን የአጃክስ መሥሪያ ማሽን የተረከቡ ሲሆን፤ ለምርቱ ግብዓት የሚሆኑ የተወሰኑ ኬሚካሎችን በመግዛት ወደ ምርት መግባት ችለዋል። በሥራቸው በመበርታት እና ፈጠራን በማከል ከተለመደው የአጃክስ ሳሙና በቀለም የተለየ፣ በጥራቱ ከፍ ያለ ምርት ለማቅረብ በመንቀሳቀስ ላይም ይገኛሉ። የሥራ ዕድል ከመፍጠር አንፃርም የሚጠበቅባቸውን ለማበርከት ከወዲሁ ጀምረዋል፡፡ አሁን ላይ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የሚያሠሯቸው ሁለት ሠራተኞች ቀጥረዋል፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በማኑፋክቸሪንግ ላይ አንድ ሰው፣ ምርቱ ከወጣ በኋላ የማስጣት እና የማድረቅ ሥራ የሚሠሩ በጥቅሉ አራት ሰዎችን ቀጥሮ ለማሠራት ፍላጎት አላቸው፡፡ ሥራው በተሻለ ሁኔታ ገበያው ላይ ከገባ ከስድስት ወር በኋላ ቁጥራቸው ወደ አሥር ለሚጠጉ ሰዎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጠርም አስታውቋል፡፡

በተጨማሪም፤ አዳዲስ ፈጠራዎችን አስፍቶ ከመሥራት አንፃር የአጃክሱ ማሽን ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ሥራ እስኪገባ ድረስ የስቴሽነሪ እና የካፌ ሥራ መጀመር ተችሏል፡፡ የካፍቴሪያ ሥራውን በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለመሥራት ሲታሰብ በዋናነት ሰልጣኞች፣ አሰልጣኞች ብሎም የአስተዳደር ሠራተኞች በተመጣጣኝ ዋጋ ጥሩ ምግብ እንዲያገኙ የሚቻልበትን አግባብ በማመቻቸት ወደ ሥራ እንደተገባ ገልጿል፡፡ በቀጣይ ይህንኑ አዳዲስ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦች በማጎልበት ብሎም በማዳበር ረገድ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዝ ዳርቻ ሥራዎች ሊያበረክቱ ያሰቡት የሥራ ፈጠራ ሐሳብ እንዳላቸውና ይህም የተለያዩ ጀልባዎችን መሥራት እንደሆነ ገልጿል፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የኢንኩቤሽንና የቴክኖሎጂ የሥራ ፈጠራ ሂደት አስተባባሪ እንዲሁም የአይሶ ኳሊቲ ኃላፊ አቶ ሚካኤል ጎአ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ ኢንኩቤሽን ስንል አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን ማበልፀጊያ የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ይይዛል፡፡ ይህም በዋናነት ቴክኖሎጂ መፈልፈልን እና የሥራ ፈጠራ ሂደትን አጣጥሞ የያዘ ተግባር ነው፡፡ ዓላማውም የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የኢንኩቤሽን ማዕከል አተገባበር እና አሠራርን ከማስቀጠል አንፃር አዳዲስ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦችን እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማበረታታት ነው፡፡ የተሻለ ሐሳብና ዕውቀት ያላቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎች አዋጭነታቸው ተረጋግጦ በየደረጃው ያሉ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት አሰልጣኞች፣ ሰልጣኞች፣ ኢንተርፕራይዞች እና ግለሰቦች አማካኝነት ወደ ተጨባጭ ተግባር እንዲለውጡ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም የከተማዋን ብሎም የሀገሪቷን የእድገት ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልጉ የተሻሻሉ አዳዲስ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦችና ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር (ኢንኩቤት በማድረግ) ለሁለንተናዊ ዕድገትና

> **ኮሌጁ ሥራዎችን የበለጠ ለማሳለጥ የኢንኩቤሽን ማዕከል በማደራጀት ላይ ይገኛል። በቀጣይ ማዕከሉ ላይ የኢንኩቤሽን ክበብ በማቋቋም ሥራዎችን በተደራጀ አግባብ የመከወን ውጥን አለው**

ብልፅግና የማይተካ ሚናውን እንዲወጣ ያግዛል፡፡

እንደ አቶ ሚካኤል ገለፃ፤ ዕውቀትን መሠረት ያደረጉ አዳዲስ የፈጠራ ሥራ ሐሳቦችን በማጎልበት እንደ አገር ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት አስቻይ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት አንፃር በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች አማካኝነት ለኢንኩቤተሮች በተለያየ አግባብ ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ታምኖ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በሰለጠነው ዓለም የቢዝነስና ንግድ ሐሳብ ከማንኛውም ሸቀጥ በላይ ውድ ነው፡፡ የአዳዲስ የፈጠራ ሥራ ሐሳቦች ምን ያህል ገንዘብ ሊያስገኝ እንደሚችል በመገንዘብም ለቢዝነስ ወይም ንግድ ሐሳቡ ከፍተኛ ግምት ይሰጣል፡፡ የቢዝነስና ንግድ ሐሳቦችን በመሸጥ የሚተዳደሩና ሕይወታቸውን የለወጡ ጥቂት አይደሉም፡፡ ጠቀሜታውን አስቀድመው የተረዱ ሀገራት ሰዎች አዳዲስ የንግድና የቢዝነስ ሐሳቦችን እንዲያመነጩና ሐሳባቸው ተወዳድሮ ገበያ እንዲያገኝ የሚያስችል አሠራር እስከመዘርጋት የደረሱ እንዳሉ አስታውቀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ርዕይንና ተልዕኮን ለማሳካት አዳዲስ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦችን የቴክኒክና ሥልጠና በሚሰጥበት ጊዜ አካባቢው ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት በዋናነት ሰልጣኝ፣ አሰልጣኝ፣ ኢንተርፕረነሮች እንዲሁም የኢንኩቤሽን ሐሳብ ያላቸው ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ ሀገር የሚጠቅም እና የሥራ አጥ ቁጥርን የሚቀንስ የአሠራር ሥርዓት መከተል ተችሏል፡፡

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለአዳዲስ ኢንኩቤተሮች ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል፡፡ አዳዲስ የፈጠራ ሥራ ሐሳቦችን ከመሰብሰብ አንፃር ከኮሌጁ ውጭ የሚመጡ ኢንኩቤተሮችን፣ ኢንተርፕራይዞችን እና ሰልጣኞችን ያሳትፋል፡፡ ከኮሌጁ የሚደረግላቸውን ድጋፍ በተመለከተ አቶ ሚካኤል ሲያብራሩ፣ ስለ ኢንኩቤሽን ሥልጠናዎችን፣ ስለ ቢዝነስ ሐሳቦች ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የገንዘብ እና የመሥሪያ ቦታ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ ሚካኤል ገለጻ፤ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አዳዲስ የፈጠራ ሥራ ሐሳብ ያላቸውን ኢንኩቤተሮች በማበረታታት ረገድ በአጃክስ ማምረት፣ በተቋም ውስጥ ቀለል ያሉ ምግቦች ሥራ እንዲሁም ጋርመንት ላይ ተደራጅተው ያሉ አካላትን በኢንኩቤሽን ማዕቀፍ እንዲታቀፉ የማድረግ ሥራ ስለመሠራቱ ጠቁመዋል። የኢንኩቤሽን ሥራውን ከማስቀጠል ባሻገር በቅርበት ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበት አግባብ አለ፡፡ ነባሮችን ኢንኩቤተሮች የማስቀጠል እንዲሁም ደግሞ አዳዲስ የፈጠራ ሥራ ሐሳብ ያላቸውን በየደረጃው በሚደረጉ የምዘና ሥራዎች እየታቀፉ ብሎም እየታገዙ የሚሄዱበት አግባብ መኖሩን ጭምር ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ሚካኤል፤ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ሥራዎችን የበለጠ ለማሳለጥ የኢንኩቤሽን ማዕከል በማደራጀት ላይ ይገኛል፡፡ በቀጣይ ማዕከሉ ላይ የኢንኩቤሽን ክበብ በማቋቋም ሥራዎችን በተደራጀ አግባብ የመከወን ውጥን እንዳለ አብራርተዋል፡፡

# ልጆች፤ ስለ አፍሪካ ህብረት ምን ያህል ታውቃላችሁ?

በፋንታነሽ ተፈራ

ልጆች፤ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብቻም ሳይሆን የአፍሪካ መዲና መሆኗን ታውቃላችሁ? በዛሬው ጽሑፋችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች አደራጅተን ስለ አፍሪካ ህብረት አመሰራረት፣ አዲስ አበባ ለ39ኛ ጊዜ እያስተናገደችው ስላለው የህብረቱ ጉባኤ እና ስላደረገችው ዝግጅት በጥቂቱ ይዘንላችሁ ቀርበናል፤ መልካም ንባብ፡፡

ልጆች የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ሀገራት ተስማምተው የመሰረቱት ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱም ኢትዮጵያን ጨምሮ 55 አባል ሀገራት አሉት።

የዛሬው የአፍሪካ ህብረት የቀድሞው መጠሪያው "የአፍሪካ አንድነት ድርጅት" በሚል ነበር፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቀመጫውን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ አድርጎ በ32 የአፍሪካ ሀገራት ግንቦት ወር 1955 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
የአፍሪካ ህብረት ዋና መስሪያ ቤት

ልጆች፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት የራሱ ዓላማዎች ነበሩት። ይኸውም ቅኝ ገዢዎችን ማስወገድ፣ በአፍሪካ ሀገራት መካከል አንድነትና ህብረትን ማበረታታት፣ ለአፍሪካውያን የተሻለ ህይወት እና እድገት ማምጣት፣ ነፃነትን ማስጠበቅ፣ ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር፣ በአፍሪካ ሀገራት መካከል የሚካሄዱትን ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚሉ ነበሩ።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ2002 "የአፍሪካ ህብረት" የሚል መጠሪያ አገኘ፡፡ ህብረቱ ራዕይ ነበረው። ራዕዩም የተቀናጀች፣ የበለጸገች እና ሰላማዊ፣ በራሷ ዜጎች የምትመራ እና በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ተፎካካሪ የሆነች አፍሪካን መመስረት ነው።

ልጆች፤ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑን የአፍሪካ ህብረት በመመስረት ቁልፍ ሚናን የተጫወቱ የአፍሪካ አባቶች 32 ናቸው፡፡ ከነዚህም አባቶች መካከል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ፣ የጋናው መሪ ክዋሜ ንክሩማህ፣ የኬንያው መሪ ጆሞ ኬንያታ፣ የሴኔጋል የመጀመሪያው ፕሬዝዳንት ሴዳር ሴንጎር፣ የታንዛኒያ ፀረ-ቅኝ ግዛት ታጋይ፣ ፖለቲከኛ እና የፖለቲካ አቀንቃኙ ጁሊየስ ኔሬሬ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

ልጆች፤ የዘንድሮው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ በዋና መሥሪያ ቤት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ አዲስ አበባም በአኩሪ የእንግዳ አቀባበል ባህሏ ተቀብላቸዋለች፡፡ ይህን እያደረገች ያለው ኮሪደሩ እና የወንዝ ዳር ልማቱ በፈጠሩላት ውበትና ጽዳት መሆኑ ለከተማዋ እና ለሀገር ፋይዳው ብዙ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በከተማችን ብሎም በሀገራችን እንድንኮራ ያደርገናል፤ አይደል ልጆች? በዚህ ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር ሀሳብ ተለዋወጡ፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

የሰጡትን የሚበላ ሲያጠጡት የሚጠፋ

**መልስ፦** ሰ. እሳት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሲወስዱበት የሚሰፋ**

ሀ. ገንዘብ

ለ. ውሃ

ሐ. ጉድጓድ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የአዲስ መሶብ ወደ ነዋሪው ደጃፍ የመቅረብ ጉዞ

## እስከ የካቲት 30 ቀን 2018 ዓ.ም. ድረስ አራት አዳዲስ የአዲስ መሶብ ቅርንጫፎች ሥራ ይጀምራሉ

**በደረጀ ታደሰ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷል። ቴክኖሎጂን ከላቀ የአገልጋይነት መርህና ሙያዊ ሥነ ምግባር ጋር አጣምሮ አገልግሎቶችን ወደ ተገልጋይ በማቅረብ ረገድ "የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት" እያሳየ ያለው ተሞክሮ ለብዙዎች ተምሳሌት እየሆነ ይገኛል። ተቋሙ አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በያዘው ዕቅድ መሠረት፣ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ቅርንጫፎቹን እያሰፋ ይገኛል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ፣ በቀድሞው የክፍለ ከተማው አስተዳደር ሕንጻ ላይ፣ ጷጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ሥራውን በይፋ የጀመረው የተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በተገልጋዮች ዘንድ አድናቆትን ያተረፉ እና አዎንታዊ ግብረ መልሶችን ያስገኙ በዓይነታቸው ከ107 በላይ የሚደርሱ የመንግሥት አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛል። ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ "የአዲስ ዓመት ስጦታ" ሆኖ የቀረበው ይህ ዘመናዊ ተቋም፣ የአገልግሎቱን ተደራሽነት ለማስፋትና ለማሳደግ ጥረቱን የጀመረው በቶሎ ነበር። በዚሁ መነሻነት እንደ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያውን ቅርንጫፍ (የቦሌ ቅርንጫፍ) በመክፈት ከመስከረም 28 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ ለአገልግሎት መብቃቱ ይታወሳል።

በዋናው መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ በወራት በሚቆጠር ዕድሜ ውስጥ ለተገልጋይ እየቀረበ ባለው አገልግሎት የተገልጋዮች እርካታ በተጨባጭ መሻሻል ማሳየቱ፣ ተደራሽነቱን የማስፋቱ ተግባር የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክቷል። ለዚህም የቦሌ ቅርንጫፍ ሁነኛ ማሳያ ነው።

ወይዘሮ ፅጌማርያም ታምራትን ያገኘናቸው በዚሁ ቅርንጫፍ ነው። ስላገኙት አገልግሎት ጠይቀናቸው በሰጡት አስተያየት፤ "ቀደም ሲል አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም ከሰነዶች ማረጋገጫ ወደ ክፍለ ከተማ፣ ከዚያም ወደ ንግድ ቢሮ መመላለስ ግዴታ ነበር። ዛሬ ግን በአዲስ መሶብ በአንድ ሰዓት ውስጥ ጉዳዬን ጨርሻለሁ። ሠራተኞቹም በፈገግታና በክብር ነው የሚያስተናግዱት። ይህ የአገልግሎት አሰጣጥ ለአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ትልቅ ዕድገት ነው" ብለዋል።

የቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ትዕግስት ሚሊዮን በአገልግሎቱ ዙሪያ በቅርቡ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ አድርገው ነበር። በአስተያየታቸው እንደጠቆሙት፤ ማዕከሉ በየዕለቱ በአማካይ ከ450 እስከ 500 የሚደርሱ ተገልጋዮችን ያስተናግዳል። በምናቀርባቸው አገልግሎቶች ተገልጋዮች በጣም ደስተኞች ናቸው። ቀደም ሲል በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች



ፎቶ ከገፀ ድር

የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ አየለ



ፎቶ ከፋይል

በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ልደታ ቅርንጫፍ

ይንከራተቱባቸው የነበሩ ጉዳዮች በአሁኑ ወቅት በአንድ ማዕከል በአጭር ጊዜ ማግኘት መቻላቸው እጅግ እንዳስደሰታቸው በተደጋጋሚ ይገልጻሉ።

አገልግሎቱን ተደራሽ የማድረጉ ተግባር በስፋት ተፈጻሚ እንደሚሆን በመንግሥት አቅጣጫ ተቀምጧል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥር 26 ቀን 2018 ዓ.ም. በተካሄደው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘት፣ የፌዴራል መንግሥት የ2018 በጀት ዓመት የ6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የተለያዩ ዘመናዊ አማራጮችን በመጠቀም የመንግሥት አገልግሎትን ተገልጋዩ ባለበት ቦታ ማድረስ የሚቻልበት ሁኔታ እንደሚፈጠር፣ ይህም በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚሆን መጠቆማቸው ይታወሳል።

የዘመናዊነት፣ የዕድገት፣ የውበት፣ የምቹነት ... ተምሳሌትነቷን በተግባር እያረጋገጠች ያለችው ዓለም አቀፋዊቷ ከተማ አዲስ አበባ፣ አገልግሎቱን በመጀመር እንዲሁም ተደራሽነቱን በማስፋት ግንባር ቀደም ሆና እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች። በዚህ ረገድ እየተሠሩ ስላሉት ሥራዎች የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ አየለ ለዝግጅት ክፍላችን ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፣ ተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤቱን ከከፈተ በኋላ በቦሌ ቅርንጫፍ የጀመረው የማስፋፊያ ሥራ እጅግ ውጤታማ ሆኗል። ይህ ቅርንጫፍ ከተመረቀበት ከመስከረም 28 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ የካቲት 4 ቀን 2018 ዓ.ም. ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ40 ሺህ በላይ ነዋሪዎችን ማስተናገድ ተችሏል። ይህም የአገልግሎቱ ተፈላጊነት ምን ያህል ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

አክለው እንዳብራሩትም፤ ተቋሙ በቅርንጫፉ የታየውን ስኬትና የተገልጋዮችን ከፍተኛ ፍላጎት መሠረት በማድረግ፣ በ2018 በጀት ዓመት የቅርንጫፎቹን ቁጥር ወደ 11 ለማሳደግ በሦስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሰፊ ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በመጀመሪያው ምዕራፍ አራት ቅርንጫፎችን (በቂርቆስ፣ በአዲስ ከተማ፣ በጉለሌ እና በልደታ ክፍለ ከተሞች) ለመክፈት የዝግጅት ሥራዎች ተጠናቅቀዋል። እነዚህ ማዕከላት ከየካቲት 15 እስከ 30 ቀን 2018 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ለአገልግሎት ክፍት ይሆናሉ።

"እነዚህን አዳዲስ ቅርንጫፎች ለአገልግሎት ዝግጁ የማድረጉ ተግባር በአሁኑ ወቅት ከ85 በመቶ በላይ ተጠናቅቋል" ያሉት አቶ ደረጀ፣ የተሠሩትን ዋና ዋና ሥራዎች እንደሚከተለው አብራርተዋል፤ "በሁሉም ማዕከላት የኔትዎርክ ዝርጋታ፣ የእሳት አደጋ መጥሪያ (Fire Alarm)፣ የድምፅ ሥርዓት እና የመብራት ሥራዎች ተጠናቅቀዋል። የቢሮ ግብዓቶችን የማሟላት ሥራዎችም በመጠናቀቅ ላይ ናቸው። ይህም ተገልጋዩ ወደ ማዕከላቱ ሲመጣ ደረጃውን የጠበቀና ምቹ የሆነ ከባቢ እንዲያገኝ ለማድረግ የታለመ ነው።"

የአዲስ መሶብ ቅርንጫፎች መገኛ ቦታ የሚመረጥበትን ሁኔታ በተመለከተ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ ሲያስረዱ፤ "ዋናው መመዘኛ ለተገልጋዮች ያላቸውን አማካይ ቅርበት ታሳቢ በማድረግ ነው። ለምሳሌ የልደታ ቅርንጫፍ ከክፍለ ከተማው አስተዳደር ሕንፃ በተወሰነ መልኩ ራቅ ብሎ የተገነባው ነዋሪው በቅርብ ርቀት እንዲያገኘው ታስቦ ነው" ብለዋል።

በሁለተኛው ምዕራፍ ተጨማሪ አራት የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ቅርንጫፎች (የለሚ ኩራ፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ የአቃቂ ቃሊቲ፣ የየካ) ክፍለ ከተሞች ለመክፈት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አቶ ደረጀ ገልጸዋል። እነዚህን ቅርንጫፎች ለአገልግሎት ለማብቃት የሚሠራው ሥራ፣ ከሕንፃ ግንባታ ጀምሮ እንደ አዲስ የሚከናወን መሆኑን ጠቁመዋል። የሳይት ፕላን ዝግጅት፣ የመሬት (ቦታ) ልየታ፣ ደረጃውን የጠበቀ አዲስ ሕንፃ ግንባታን፣ መሠረተ ልማት ዝርጋታን እና ሌሎች ሥራዎችን ባካተተው የሁለተኛው ምዕራፍ ቅርንጫፎችን ለአገልግሎት የማብቃት ተግባር፤ እስከ G+5 ድረስ ከፍታ ያላቸው ሕንፃዎች ግንባታ እየተከናወነ እንደሚገኝ አስረድተዋል። በአሁኑ ወቅት የሕንፃዎቹ ግንባታ በአብዛኛው የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በቀጣይ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት እና ግብዓት የመዘርጋት፣ የማሟላት እና ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ይደረጋል ብለዋል፡፡

የአዲስ መሶብ ተቋም አገልግሎቱን ለማዘመንና ለማሻሻል ከሚጠቀማቸው ቁልፍ አቅሞች መካከል ቴክኖሎጂ እና የሰው ኃይል ተጠቃሾች ናቸው። በዚሁ መሠረት ለአዳዲስ ቅርንጫፎች የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችንና የሰው ኃይልን የማሟላት ሥራ ከወዲሁ እያጠናቀቀ ይገኛል። ሠራተኞችን የመመልመልና የማሰልጠን ሥራም ከባለድርሻ አካላት ጋር እየተከናወነ ነው። አቶ ደረጀ አየለ እንደገለጹት፣ "ሠራተኞቹ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን፣ በሥነ-ምግባርና በአገልጋይነት መንፈስ የታነጹ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቷል። ቅርንጫፎቹ አገልግሎታቸውን የሚጀምሩት በሥራ ቦታ፣ በሰው ኃይል፣ በግብዓትና በቴክኖሎጂ ሙሉ በሙሉ ተሟልተው ነው። ይህም ተቋሙ ለጥራት የሚሰጠውን ትኩረት ያሳያል" ብለዋል።

ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት (የካቲት 4 ቀን 2018 ዓ.ም.) ድረስ በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት እና ቦሌ ቅርንጫፍ ከ80 ሺህ በላይ ተገልጋዮች የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘታቸውን የተናገሩት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ የአገልግሎቱን ተደራሽነት በማስፋት፣ ማንኛውም የአዲስ አበባ ነዋሪ የነዋሪነት ቦታው ሳይወስነው፣ በተመቸውና በቀረበው ቅርንጫፍ ሄዶ አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል፣ በዚህም ቀደም ሲል የነበረውን "ወደዚህ ክፍለ ከተማ ሂድ" የሚል አድካሚ ቢሮክራሲ ሙሉ በሙሉ በማስቀረት የመንግሥት አገልግሎት ዘመናዊ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ከአድሏዊነት የጸዳ ማድረግን በተግባር ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው ብለዋል። ይህ እንዲሳካ የተቋሙ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላት እና የከተማዋ ነዋሪ ማኅበረሰብ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል።

ኢኮኖሚ

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# አዲሱ የህይወት ምዕራፍ

**• ከ2011 እስከ 2018 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 8 ሺ 874 የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን እና ቤተሰቦቻቸውን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ ተጠቁሟል**

**በይግለጡ ጓዴ**

ከተሞች ማደጋቸው እና መስፋፋታቸው ዓለም አቀፋዊ ልምምድ ነው፤ ነገር ግን አንዳንድ ከተሞች በዚህ ተፈጥሯዊ ሂደታቸው አካታችነትን፣ ሁሉን አቀፍና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ላይ ውስንነት ይታይባቸዋል። ከለውጡ በፊት ባሉ ዓመታት በአዲስ አበባ ከተማ ዳርቻ ይኖሩ የነበሩ አርሶ አደሮች በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተፈናቀሉት በዚህ አይነት ሁኔታ ነው። እነዚህ አርሶ አደሮች ነባር ይዞታቸውን እንዲለቅቁ የተደረገበት መንገድ ለተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች በሚያጋልጣቸው አኳኋን ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የነበሩ አርሶ አደሮች ከነባር ይዞታቸው ሲነሱ የካሳ ክፍያ ላይ ብቻ የማተኮር አዝማሚያ እንደነበር ይታወሳል፤ የካሳ ክፍያውም በወቅቱ ከነበረው የመሬት ዋጋ ጋር ተመጣጣኝነት እንዳልነበረው በአርሶ አደሮቹ በኩል ተደጋግሞ ይነሳ የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ኑሯቸውን በዘላቂነት ሊደግፉ በሚችሉ ስልቶች ላይ ማተኮር እንደሚገባም ይመከራል። ምክንያቱም ከመሬታቸው ሲፈናቀሉ የለመዱት የሥራ መስክ ይቋረጣል፤ አዳዲስ አማራጮችን ማመቻቸት ካልተቻለ የከፋ ምስቅልቅሎሽ ይከተላል። ስለዚህ ለተነሺዎች የሙያ ስልጠና በመስጠት በግንባታ፣ በእንስሳት እርባታ፣ በወተት ላሞች ልማት፣ በዶሮ እርባታ፣ በንብ ማነብ፣ በንግድ ሥራዎች እና ሌሎች መስኮችም እንዲሰማሩ ማድረግ ይገባል፡፡

አሁን አሁን የአገልግሎት ዘርፍም አማራጭ የስራ መስክ እየሆነ መጥቷል። ይህን ጨምሮ ከላይ የጠቃቀስናቸው መስኮች በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በመተግበር ላይ መሆናቸው የቀድሞ ስህተትን የሚያርም እና ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በከተማዋ መስፋፋት ምክንያት ከነባር ይዞታቸው ተፈናቅለው ለተለያዩ ችግሮች የተዳረጉ አርሶ አደሮችን እና ልጆቻቸውን በማደራጀት ልዩ ልዩ የማቋቋም ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል፤ በርካታ ቁጥር ያላቸው አርሶ አደሮችንም ተጠቃሚ አድርጓል፡፡

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ጻጋዬ ጅሩ ከእነዚህ ወገኖች ይመደባሉ፡፡ እኒህ ግለሰብ በልማት ምክንያት ከነባር ይዞታቸው ተፈናቅለው የነበሩ ሲሆን፣ መንግስት አርሶ አደሮችን መልሶ በማቋቋም ህይወታቸውን የሚለውጥ መርሃ ግብር ነድፎ ወደ ተግባር በመግባቱ ከከፋ የህይወት ምስቅልቅሎሽ ወጥተው







ፎቶ ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በተመቻቸላቸው ልዩ ልዩ የማቋቋሚያ መርሃ ግብሮች ተጠቃሚ ሆነዋል

አሁን የተቃና መስመር መያዛቸውን ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ ተናግረዋል፡፡

ታዴ እና ፀጋዬ ከነቤተሰቦቻቸው የተባለ ማህበር መስርተው አራት ሆነው በከብት ማድለብ ዘርፍ ተጠቃሚ መሆናቸውን የገለፁት አቶ ፀጋዬ፣ ከሶስት ዓመት ወዲህ በሬዎችን በማድለብ በበዓላት ወቅት ወደ ገበያ በማውጣት ይሸጣሉ፡፡ አሁን 8 በሬዎችን በማድለብ ላይ ይገኛሉ፡፡ መንግስት አርሶ አደሮችን በማሰባሰብ የስራ እድል መፍጠሩ መልሶ በማቋቋም ከበፊቱ የተሻለ ህይወት እንዲመሩ ያስቻላቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አርሶ አደር ጻጋዬ የአሰራር ተሞክሮአቸውን ወደ ሌሎች በማስፋት ሌሎች አርሶ አደሮችም ተጠቃሚ በመሆን ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረጋቸውን ይናገራሉ፡፡ በቀጣይም የብድር አቅርቦት፣ መብራት እና ውሃ ቢመቻችላቸው የማድለብ ዘርፉን የበለጠ አስፋፍተው በትኩረት ለመስራት ከወዲሁ መዘጋጀታቸውን ገልፀዋል፡፡

አቶ ንጉሴ ገብረጊዮርጊስ ነዋሪነታቸው በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ነው፤ የበንቲ ፍል ውሃና ሆቴል አገልግሎት ስራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ የፍል ውሃና ሆቴል አገልግሎት ድርጅቱ 32 አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ልጆችን በአባላትነት ያካተተ ሲሆን፣ እነዚህ አርሶ አደሮች ቀደም ብሎ በልማት ምክንያት የይዞታ መሬታቸው ተወስዶባቸው ለተለያዩ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ እንደነበሩ አስታውሰዋል፡፡

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ወደዚህ ስራ እንደገቡ የሚገልጹት አቶ ንጉሴ፣ በዚህ የልማት ድርጅት ውስጥ የተሰማሩ አርሶ አደሮች ህይወት እየተሻሻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አቶ ንጉሴ እና የማህበሩ አባላት በፍል ውሃ የአገልግሎት ዘርፍ በመደራጀት ገቢያቸውን አሳድገዋል፡፡ አሁን ደግሞ በሆቴል አገልግሎት፣ በምግብና ዝግጅት፣ በሱቅ ስራም ተሰማርተዋል፡፡

የአገልግሎት ዘርፉ ራሳቸውን ለማቋቋም እንደረዳቸው አቶ ንጉሴ በመጠቆም ዘርፉን ይበልጥ አሻሽለው ለመስራት እና ተጠቃሚ ለመሆን ዝግጁ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ መንግስት ለችግር ተጋላጭ የነበሩ አርሶ አደሮችን በተለያዩ ዘርፎች በማደራጀት ህይወታቸውን እንዲለውጡ በማድረጉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

በቦሌ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የስራ እድልና ማደራጀት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ጻጋዬ ካሳዬ በክፍለ ከተማው ቤተሰቦቻቸውን ጨምሮ የአጠቃላይ 5 ሺህ 960 የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን በመመዝገብ ፍላጎታቸው ተለይቶ በተለያዩ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ መደረጉን አስታውቃል፡፡

ከቤቶች ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር ለ3 ሺህ 111 የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው የጋራ መኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ተደርጓልም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ጻጋዬ ገለጻ በማህበር ለተደራጁ 51 የሚሆኑ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ልጆች የጋራ መኖሪያ ቤት ሱቅ የተሰጣቸው ሲሆን፣ በአጠቃላይ የአባላት ብዛት 330 ናቸው። በማህበራቱ በመደራጀት በንግድ፣ በከተማ ግብርና እና በአገልግሎት ዘርፍ ተሰማርተው እየሰሩ እንደሚገኙ አቶ ጻጋዬ ገልፀዋል፡፡

የልማት ተነሺ የሆኑ እና መስራት የማይችሉ 157 አባወራ እና እማወራ በየወሩ ለምግብ ፍጆታ የሚሆን ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ እየተሰጣቸው መሆኑን አቶ ጻጋዬ አስታውቀዋል፡፡

አጠቃላይ 165 ማህበራት የገንዘብ ድጋፍ ተደርጎላቸው እና ብድር ተመቻችቶላቸው ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉን የጠቆሙት አቶ ጻጋዬ፣ እነዚህ ማህበራት በከተማ ግብርና፣ በንግድ እና በአገልግሎት ዘርፍ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ውስጥም 51 ማህበራት መንግስት በሰጣቸው የኮንደምንየም ሱቅ፣ 31 ማህበራት በመንግስት በተሰራ ሼድ እየሰሩ ሲሆን፣ ቀሪዎች ደግሞ በራሳቸው ቦታ ላይ በከተማ ግብርና ማለትም በዶሮ እርባታ፣ በወተት ላም እርባታ እና ከብት ማድለብ ዘርፎች ተሰማርተው እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የአርሶ አደር መልሶ ማቋቋም ቡድን መሪ አቶ ለገሰ ወርቁ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ አርሶ አደሮችን በማህበር በማደራጀት መልሶ በማቋቋም ወደ ስራ የተገባ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

በከተማዋ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን በ1 ሺህ 99 ማህበራት በማደራጀት መልሶ ማቋቋም መቻሉን አቶ ለገሰ ጠቁመው፣ በተለይም በንግድ፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በኮንስትራክሽን፣ በከተማ ግብርና (በጓሮ አትክልት፣ በእንቁላል ዶሮ እርባታ፣ በወተት ላሞች ልማት፣ በከብት ማድለብ እና ንብ እርባታ) ዘርፎች ተደራጅተው የተሻለ ህይወት መምራት መጀመራቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ለገሰ ገለፃ፣ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ከምዝገባ ጀምሮ እስከ ድጋፍ ድረስ በእያንዳንዱ የምዝገባ እና የልየታ ሂደት በኮሚቴ ተጣርቶ በአግባቡ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በከተማ አስተዳደሩ በተገነባ የእንስሳት እርባታ ማዕከል፣ በንግድ ዘርፍ እንዲሁም በግል ይዞታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተሰርቷል፡፡

አርሶ አደሮቹ በፊት ከመሬታቸው በልማት ምክንያት በመነሳታቸው ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ሆነው እንደነበር አቶ ለገሰ በማስታወስ፣ አሁን ከአንዱ ማህበር ወደ ሌላኛው ማህበር ቢለያዩም ሁሉም አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ከ2011 እስከ 2018 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 8 ሺ 874 የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸውን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሁሉም ማህበራት የክህሎት ስልጠና እና የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘታቸውን አቶ ለገሰ ጠቁመዋል። ለ701 ማህበራት የብድር አቅርቦት እና የፋይናንስ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፣ በዚህም ውጤታማ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የሙያ እና የፋይናንስ ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ቡድን መሪው አስታውቀዋል፡፡

እስከ አሁን በተሰራ ስራ 114 ሞዴል ማህበራት የተፈጠሩ ሲሆን፣ አርሶ አደሮቹ በወተት ላም እርባታ፣ በከብት ማድለብ፣ በዶሮ እርባታ፣ በአገልግሎት እና በብሎኬት ምርት ዘርፍ ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን በማሳደግ ወደ ኢንቨስትመንት ደረጃ እየተሸጋገሩ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የፕላስቲክ ከረጢት እገዳና የአዋጁ ትግበራ

- ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል የፕላስቲክ ከረጢት (ፌስታል) መያዝ፣ ለግለሰብ ከ2 ሺህ እስከ 5 ሺህ ብር ያስቀጣል።
- የፕላስቲክ ከረጢት ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ለገበያ ማቅረብ ደግሞ በተቋማት ደረጃ ከ50 ሺህ እስከ 200 ሺህ ብር ቅጣት እና እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ተቀምጧል።

**በለይላ መሀመድ**

ከጥር 23 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ የፕላስቲክ ከረጢቶችን የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም ይዞ የተገኘ ማንኛውም ግለሰብ ከ2 ሺህ ብር የማያንስና ከ5 ሺህ ብር የማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እንደሚጣልበት የሚደነግገው አዋጅ ተፈፃሚ መሆን ጀምሯል፡፡ ነው። ለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የመዲናዋ ነዋሪዎች ምን ይላሉ? የሚለውን የዝግጅት ክፍላችን በንግድ ስራ የተሰማሩ ነጋዴዎችንና ሸማች የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዘዋውሮ አነጋግሯል።

የመጀመሪያ ቅኝት ያደረግነው በአንድ አትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ቤት ነበር። በምን መልኩ ግብይቱ እየተከናወነ እንደሆነ በሱቁ ያገኘነው ወጣት ንጉስ ረታ ሲገልጽ፤ “በእኛ በኩል ለጊዜው መያዣ ባለማዘጋጀታችን ‘የለንም፤ ይዛችሁ ኑ’ የሚል ምላሽ እየሰጠን ነው። ትንንሽ ነገር የሚገዙት ደግሞ በእጃቸው ይዘው ነው እየሄዱ ያሉት። አዋጁ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ዕለት ጀምሮ በተጨባጭ እየተገበያየን ያለንበት መንገድ ይህ ነው። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ መቀጠል ስለሌለበት በቀጣይ የራሳችንን አዋጭ የመሸጫ ከረጢቶች ለማዘጋጀት ጥረት እናደርጋለን” ብሏል።

የከተማዋ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ብርሀን ታደለ ደግሞ “በፌስታል ምርት አጠቃቀሜም ሆነ አወጋገዴ ብዙም ጠንቃቃ አልነበርኩም፤ የሚወገድ ፌስታልን እንዳገኘሁ ሜዳ ላይ ከመጣል በተጨማሪ እቃ ከሚታጠብበት ቆሻሻ ውሃ ጋር ቀላቅዬ ቱቦ ውስጥ እጥል ነበር። በዚህም በእኔና መሰል ግለሰቦች ምክንያት አካባቢያችን ከመቆሸሹ ባለፈ ቱቦ ይዘጋ ነበር። ይህ በተለይም በክረምት ለአስፋልት መንገድ ብልሽት ምክንያት ሲሆን እኔ ራሴ ተመልክቻለሁ። መንግስት ይህንን የፌስታል ምርት በከተማዋ ጥቅም ላይ እንዳይውል ክልከላ ማድረጉ አግባብነት ያለውና ብዙ ችግሮችን የሚያስወግድ እንደሆነ አምናለሁ” ሲሉ ሀሳባቸውን አጋርተውናል።

“በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ አንዳንድ ነዋሪዎች በቀላሉ ሊበሰብሱ የሚችሉ የእቃ መያዣዎችን እየተጠቀሙ ማየቴ፣ የማህበረሰቡ ግንዛቤ መለወጡን ትዝብት ከመውሰዴም በላይ ለህጉ ተፈጻሚነት የሰጡትን ፈጣን ምላሽ ያሳያል” ሲሉ አስተያየታቸውን የሰጡን ሌላው የከተማዋ ነዋሪ አቶ ፍቃዱ ተሾመ ናቸው። በግብይት ወቅት የታዘቡትን ሲገልጹም “በአንድ አትክልትና ፍራፍሬ ቤት ጁስ ለመግዛት ገብቼ ‘መያዣ እቃ አምጣ’ ተብያለሁ። አንዳንድ ሱቆች ደግሞ በወረቀት ጠቅልለው ሲሰጡ ተመልክቻለሁ። እነዚህ መያዣዎች ንጽህናቸው ያልተጠበቀና ለጤና ጎጂ የሚሆኑበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላልና አፋጣኝ መፍትሔ ሊበጅ ይገባል። ከዚህ



ፎቶ- ከገፀ ድር
ፌስታል አለመጠቀም የአካባቢን ስነ ምህዳር ከመጠበቅ አንፃር ትልቅ አበርክቶ አለው

በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የመገበያያ ከረጢቶች ከ80 እስከ 90 ብር እየተሸጡ በመሆኑ አቅምን ያገናዘበና ተመጣጣኝ ማድረግ ያስፈልጋል” ብለዋል።

ወይዘሮ ፀሐይ ታረቀኝም በተመሳሳይ በግብይት ወቅት ያጋጠማቸውን ገጠመኝ ነግረውናል። “ፌስታል መጠቀም በተከለከለበት ማግስት (እሑድ ዕለት) ጠዋት ከቤተ ክርስቲያን ስመለስ ከቤት ተደውሎ ዳቦ እንድገዛ ተነገረኝ። ልገዛ ዳቦ ቤት ስገባ ‘ፌስታል ስላቆምን መያዣ ይዘሻል?’ ብለው ጠየቁኝ። እኔም ወደ ቤቴ ተመልሼ ዳንቴልና ዘንቢል ይዤ በመምጣት ገዝቼ ሄድኩኝ። ይህንን ያደረግኩት ግን ቤቴ ቅርብ ስለሆነ ነው። ቤታቸው ሩቅ የሆኑ ሰዎች ግን ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው መገመት ይቻላል።” እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ ፌስታልን ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን ሲወሰን ህብረተሰቡ እንዳይቸገር ተኪ ምርት በስፋት ሊቀርብ ይገባ እንደነበር አክለዋል።

ከዚህ ውጪ ከአንድ ጊዜ በላይ አገልግሎት የማይሰጡ የፕላስቲክ ምርቶች (ፌስታል) መወገዳቸው ለከተማዋ ጽዳት ጥሩ ነው። በተለይም ፕላስቲኮቹ ባልተገባ መንገድ ስለሚወገዱ በክረምት ወቅት ቱቦዎችን ከመዘጋትና መንገዶችን ከአላስፈላጊ ብልሽት ለመታደግ እንደሚጠቅም ገልጸዋል።

## ፌስታል በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው ብክለት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት ጥናት ባለሙያ አቶ ሙላቱ ወሰኑ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት እንደገለጹት፤ አጠቃላይ የፕላስቲክ ውጤቶች “በመልሶ መጠቀም ጥቅም ላይ የሚውሉ” እና “ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም መስጠት የማይችሉ” በሚል በሁለት ይከፈላሉ። በመልሶ መጠቀም ጥቅም ላይ የሚውለው የተወሰነ ተቆርጦ፣ ተፈጭቶ ወይም በተለየ መልኩ ቅርጹ ተቀይሮ ጥቅም የሚሰጥ ማለት ነው። ከዚህ ውጪ ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም የማይሰጡ የፕላስቲክ ከረጢቶች ደግሞ ለመልሶ መጠቀም ስለማይውሉ አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ፤ የአካባቢ ብክለትም ያመጣሉ። አካባቢ ሲበከል ደግሞ አፈሩ፣ ውሃው እና አየሩ ይበከላል።

የፕላስቲክ ምርቶች በአፈር ውስጥ ተቀብረው ለመቶ ዓመታት የማይበሰብሱ ከመሆናቸው ባሻገር፣ በአፈር ውስጥ በቂ አየር እንዳይዘዋወርና ምርት እንዳይኖር ያደርጋሉ። እንዲሁም እንዲህ አይነት የፕላስቲክ ምርቶች በሚቃጠሉበት ወቅት የአየር ብክለት እንዲፈጠር በማድረግና በተለይም ለጤና ጎጂ የሆኑ ጋዞችን በማመንጨት ዜጎችን ለካንሰር በሽታ የማጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው። የሚለቁት ጋዝ ከሌሎች በካይ ጋዞች የበለጠ ነው። በጥቅሉ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል። አካባቢን በማቆሸሽ የአካባቢ ገጽታን ይቀይራሉ፤ የአፈር ለምነትን በማሳጣት ሥነ-ምህዳርን ያዛባሉ፤ የውሃ መጠንና ጥራትን ያጓድላሉ። እነዚህን ሁሉ ችግሮች የሚያስከትሉትን የፕላስቲክ ውጤቶች ማስወገድ ከተቻለ በዚህ ሳቢያ የሚከሰተውን የአካባቢ ብክለት ማስቀረት እንደሚቻል ባለሙያው ገልጸዋል።

## በአዲስ አበባ ምን እየተሰራ ነው?

የጥናት ባለሙያው አቶ ሙላቱ አያይዘውም፤ በመዲናዋ መሀል ከተማ ላይ ደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራ በትኩረት እየተሰራ በመሆኑ ንጹህና ውብ ሆኖ ይታያል። ነገር ግን አሁንም ድረስ በመዲናዋ ዳርቻዎች፣ በገበያ ስፍራዎች እንዲሁም በወንዝ ዳርቻዎች ላይ ተጥለው የሚታዩ የፕላስቲክ ውጤቶች ለአካባቢ ብክለት ስጋት ናቸው። ይህንንም ስጋት ለመከላከል መንግስት ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ፣ ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም የሚሰጥ እንዲሁም በመልሶ መጠቀም ጥቅም ላይ ከሚውለው የፕላስቲክ ውጤት ውጪ ያለው እንዲታገድ ከስድስት ወራት በፊት በፀደቀው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁጥር 1383/2017 ደንግጓል። አዋጁ የሚከለክለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም የሚሰጥ የፕላስቲክ ውጤት እንዳይመረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ፣ እንዳይከፋፈል፣ እንዳይሸጥ ወይም ማንኛውም ግለሰብ ይዞ እንዳይገኝ ነው።

ለአካባቢ ተስማሚ በሆኑ ተኪ ምርቶች መተካት አለበት ሲባልም ከወረቀት፣ ከክር፣ ከእንጨት፣ ከሳር እንዲሁም ከሌሎች የእንስሳት ውጤቶች የተሰሩና የተመረቱ ሊሆኑ ይችላሉ። እስከ አሁንም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የፕላስቲክ ውጤቶች (ፌስታል) በአካባቢ ብክለት ላይ ስለሚያስከትሉት ተጽዕኖ ግንዛቤ ከመፍጠር በተጨማሪ፣ ተኪ ምርት ማምረት ላይ የተሰማሩ አምራቾችን የማበረታታት ስራ ሰርቷል፤ እየሰራም ይገኛል።

“አዋጁ በሚያዘው መሰረት ወደ ትግበራ ተገብቷል” ያሉት የጥናት ባለሙያው፤ በአዋጁ በፌስታል አጠቃቀም ላይ የተጣሉት ቅጣቶችም ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፌስታል ይዞ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከ2 ሺህ እስከ 5 ሺህ ብር ይቀጣል። የፕላስቲክ ከረጢት ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ለገበያ ማቅረብ ደግሞ በተቋማት ደረጃ ከ50 ሺህ እስከ 200 ሺህ ብር ቅጣትና እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ተቀምጧል።

የተቋሙን የስድስት ወራት የእቅድ አፈፃፀምና የፕላስቲክ ክልከላን በተመለከተ መግለጫ የሰጡት የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ዲዳ ድሪባ፤ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በተለያዩ የንግድ ስፍራዎች በመዘዋወር ባደረጉት ክትትል፣ ህብረተሰቡ ከፕላስቲክ ውጪ የሆኑ የእቃ መያዣዎችን እየተጠቀመ እንደሚገኝ መታዘባቸውንና አጭር ጊዜ ቢሆንም የክልከላው ተግባራዊነት ውጤታማ መሆኑን ተናግረዋል።

በገበያው ላይ ፌስታልን የሚተካ በቂ ምርት አለመኖርና የተኪ ምርቶች ዋጋ መናር ጋር ተያይዞ ህብረተሰቡ የሚያነሳውን ጥያቄ በተመለከተም አቶ ዲዳ፤ በቂ የሆኑ ፌስታልን የሚተኩ ምርቶች ባይኖሩም ፌስታል መጠቀም ግን አይቻልም ብለዋል። በገበያው ላይ ያለውንና የራስን መፍትሔ መፈለግ ያስፈልጋል። በጊዜ ሂደት ተኪ ምርቶች በብዛት እየተመረቱ ዋጋቸውም እየቀነሰ እንደሚመጣ ተናግረዋል።

አምራቾች ፌስታልን የሚተኩ ምርቶችን በብዛት እንዲያመርቱ ከመደገፍና ከማበረታታት አኳያም፣ እንደ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለአምራቾች በከተማ ደረጃ መሬት፣ ማሽን፣ ፋይናንስና የተለያዩ ድጋፎች የሚሰጡ አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው የማገናኘት ስራ መስራቱን ዋና ስራ አስኪያጁ ጠቁመዋል።

በሥርዓተ ምህዳር እንዲሁም በሰዎች ጤና ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ተረድተው የፕላስቲክ ምርትን ያገዱ በርካታ ሀገራት መኖራቸውንና ከነዚህም መካከል እንደ ኬንያ፣ ሩዋንዳና ታንዛኒያ የመሳሰሉትን የአፍሪካ ሀገራት በምሳሌነት መጥቀስ እንደሚቻልም ተናግረዋል።

## የአፍሪካውያን... ከገጽ 6 የዞረ

እህትማማችነትና ወንድማማችነት የሚያጠናክር ነው፡፡

ለማሳያነትም የቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት የሰላምና የነፃነት አባት ኔልሰን ማንዴላ የተናገሩት ንግግር ይገኛል። "የ1896ቱ (እ.ኤ.አ) የዓድዋ ድል የአፍሪካን ህዝቦች አይበገሬነት ያሳየ እና በወቅቱም በመላ አህጉሪቱ ከቅኝ አገዛዝ ጋር ሲዋጉ ለነበሩ ሁሉ አነሳሽ ሆኗል" ሲሉ መናገራቸው ተከትቧል፡፡ መታሰቢያው ካሉት ሰባት በሮች መካከል መዘጋጃ ቤት በሚገኝበት አቅጣጫ ያለው አንደኛው በር ፓን አፍሪካኒዝም በር በሚል የተሰየመ ነው፡፡

ሌላኛው በመታሰቢያው የዓድዋ ጦርነትን የመሩ 12 የጦር መሪዎች ሐውልት ከግድግዳ ላይ ተሰርቶ የሚገኝ ሲሆን ማታ ላይ በእያንዳንዱ የጦር መሪ አናት ላይ የድል ችቦን የሚወክል መብራት ይበራል፡፡ ይህም የእነሱ መስዋዕትነት ለአፍሪካ ብርሃን መሆኑን ያሳያል፡፡ የጦር መሪዎች ሐውልት ካለበት ህንፃ ፊት ለፊትም የአፍሪካ ካርታ ስዕል ይታያል፡፡ ከፍተኛ አስጎብኚዋ ትዕግስት እንደምትናገረው የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ መሰረት እንዲይዝና እንዲጠናከር የዓድዋ ድል ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡

መታሰቢያው አፍሪካውያን የዓድዋ ድልን ታሪክ እንዲረዱና ከታሪካቸው ጋር እንዲገናኙ ያስችላል፡፡ ከፍተኛ አስጎብኚዋ ትዕግስት እንደምትገልፀው፣ "አፍሪካውያን መታሰቢያውን ሲጎበኙ በጣም ደስተኛ ናቸው፡፡ የአድዋን ድል የኢትዮጵያ ብቻ ድል አድርገው አይመለከቱም፤ 'የእኛም ድል ነው' የሚል መንፈስ አይቼባቸዋለሁ፡፡ የመታሰቢያ ሙዚየሙን ውበት፣ የታሪኩን ትልቅነት በማየት በጣም ይደነቃሉ፡፡ ብዙዎቹ ታሪኩን ያውቁታል፤ ወደ ራሳቸው በመውሰድ አድዋ አባቶቻቸው ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ በሚያደርጉት ትግል መነሳሳት እንደፈጠረላቸው፣ ኢትዮጵያ ድንቅ የሆነ ታሪክና ህዝብ ያላት ሀገር እንደሆነች ሁሌ ይነግሩናል፡፡"

በቅርቡም የአፍሪካ ህብረት መስራች አባቶች የሆኑት ጁሊየስ ኔሬሬ፣ ክዋሜ ንክሩማህ፣ ኬኔት ካውንዳ፣ ሙሀመድ ጋዳፊና ሌሎች ልጆችና የልጅ ልጆች መታሰቢያውን መጎብኘታቸውን የምታስታውሰው ትዕግስት፣ "ቅኝ ግዛት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ ስላልተገዛችሁ አታውቁም፤ የእናንተ ታሪክ ከቅኝ ግዛት እንድንላቀቅ መነሻ ሆኖናል፡፡ ወደ ሌላው ዓለም ስንሄድም የዓድዋ ታሪክ የእኛም በመሆኑ እንኮራለን፡፡" ይላሉ፡፡

ዮሴፍ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፣ የዓድዋ ድል ለአፍሪካና በመላው ዓለም የሚገኙ ጥቁር ህዝቦች ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ፣ ነፃነታቸውን እንዲጎናፀፉ የፈጠረው ተነሳሽነት በሚፈለገው ደረጃ አልተነገረም ነበር፡፡ አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት መላቀቅ ቢችሉም አሁንም ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ውስጥ ብዙ ፈተናዎች እያጋጠማቸው ይገኛል፡፡ አፍሪካውያን በአንድነት መቆምና መተባበር ካልቻሉ የትናንቱ ዕጣ ፈንታ ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ የዓድዋ ድል መታሰቢያ አፍሪካውያንን የሚያሰባስቡ ኮንፈረንሶች እየተካሄዱበት ነው፡፡ መታሰቢያው ወንድማማችነትን፣ እህትማማችነትን እና አንድነትን ለማጠናከር ትልቅ የመስፈንጠሪያ ስፍራ ነው፡፡

## የአዲስ... ከገጽ 16 የዞረ

ልማት የተሰሩ መንገዶች አንደኛ ደረጃ የሚባሉ ሲሆን በፈረቃ አራት ጊዜ ይጸዳሉ፡፡

ቆሻሻ ከቤት ለቤት የመሰብሰብ ስራ ወደ ማታ ባለው ክፍለ ጊዜ እንዲዛወር ተደርጓል፡፡ የውስጥ ለውስጥ መብራቶች እንዲኖሩ በመደረጉ ስራውን ያለምንም ችግር ለማከናወን አስችሏል። በተጨማሪም ደረቅ ቆሻሻ በባህሪው ሽታ ስላለው ይህንን ለመቀነስ ማታ አየሩ ቀዝቀዝ በሚልበት፣ የትራፊክ እንቅስቃሴ በሚቀንስበት፣ ያደጉ ሀገራት ውጤታማ አሰራር በመሆኑ ተሞክሮን በመውሰድ እየተሰራበት እንደሆነ ወይዘሮ ሀዳስ አስረድተዋል፡፡

እንግዶች ቢመጡም ባይመጡም ከተማዋ ዘወትር ጽዱ እንድትሆን ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ በተጨማሪም እንደ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የተለያየ ጉባኤ ሲካሄድ አዲስ አበባ ጽዱና ውብ ሆና እንድትሆን በተለየ ሁኔታ በንቃት ተሰርቷል፡፡ እንግዶች በሚያልፉባቸውና በሚያንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች አዋኪ የሆኑ ከግንባታ ጋር በተያያዘ መንገዶች ላይ ተረፈ ምርቶች፣ ቁፋሮዎች ካሉ ቶሎ እንዲነሱና እንዲስተካከሉ የማድረግ ስራ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በትብብር ስለመሰራቱ ወይዘሮ ሀዳስ ያነሳሉ፡፡

ድሮ እንግዶች ከየት ተነስተው የት እንደሚቆዩ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት እንግዶች በከተማዋ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተወሰነ አካባቢ የተገደበ አይደለም የሚሉት ዋና አማካሪዋ፣ በኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ በርካታ አካባቢዎች ለምተዋል፡፡ አዳዲስ መናፈሻዎች፣ ፓርኮችና ሌሎች የቱሪዝም መዳረሻዎች ስላሉ ሰፊ አካባቢዎች ላይ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

ለምሳሌ የአፍሪካ ህብረት መሪዎች ጉባኤ ተሳታፊዎች ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ጀምሮ እስከ የህብረቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ የሚገኝበት ሜክሲኮ፣ ሆቴሎች በአብዛኛው በሚገኙባቸው ካዛንቺስ ያርፋሉ፤ ወደ ሸሮ ሜዳ ለግብይት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ እንጦጦ ፓርክ ለጉብኝት ይሄዳሉ፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን ይጎበኛሉ፡፡ ወደ አዲስ አፍሪካ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከልም ይሄዳሉ፡፡ ከዚህ አኳያ እንግዶች ይንቀሳቀሱባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ አካባቢዎች የበለጠ ጽዱና ውብ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ህብረተሰቡ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ግንዛቤ እየተፈጠረ ነው፡፡ የሚሰበሰብ ቆሻሻ 24 ሰዓት ሳይሞላ በቶሎ እንዲነሳ በቅርብ ክትትል እንደሚደረግም ተናግረዋል፡፡

ወ/ሮ ሀዳስ እንደገለፁት፣ የኮሪደር ልማቱ የጽዳት ስራውን በማቃለል ትልቅ እፎይታ ፈጥሯል፡፡ ሰፋፊ የተሽከርካሪ፣ የሳይክል እና እግረኛ መንገድ፣ በየቦታውም የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በማካተት ጽዱ ሆነው ተገንብተዋል፡፡ ማህበረሰቡ ቆሻሻን በአግባቡ እንዲያስወግድ፣ አንዳንድ በቸልተኝነት ቆሻሻ የሚጥሉ ሲገኙ ራሱ ማህበረሰቡ "ለምን ትጥላላችሁ?" በማለት የሚጠይቅበትና ባለቤት የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ዋና አማካሪዋ እንደሚሉት፣ በከተማዋ ከዚህ ቀደም አብዛኛው የንግድ እንቅስቃሴዎች በእግረኛ መንገዶች ላይ ይካሄዱ ስለነበር የጽዳት ሰራተኞች መሀል አስፋልት ውስጥ ራሳቸውን ለአደጋ በሚያጋልጥ መልኩ በመግባት ያፀዱ ነበር፡፡ አሁን ግን ርቀታቸውን ጠብቀው፣ ከሰውና የንግድ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ከሚፈጠር ግፊያና ተፅዕኖ ነፃ ሆነው የሚያጸዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

አዲስ አበባ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገች የመጣች ሲሆን፤ በዚያው ልክ ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብ፣ የማጓጓዝና የማስወገድ አገልግሎቱን ለማዘመን እየተሰራ ነው። የመንገድ ጽዳት ስራው ከእናቶች ትከሻ ተላቅቆ በቴክኖሎጂ ተደግፎ፣ በአውትሶርስ (በግል የጽዳት ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች) እንዲሰጥ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ የአንደኛ ደረጃ (ቪአይፒ) መንገዶች (ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ጀምሮ እስከ ብሔራዊ ቤተ መንግስትና ሌሎች የከተማዋ አካባቢዎች የሚገኙ) ቆሻሻ በሚያነሱ መኪናዎች (Sweeper Cars) በመታገዝ እየጸዱ መሆኑን ወ/ሮ ሀዳስ ተናግረዋል፡፡

# ማስታወቂያ

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ለመኖሪያ አገልግሎት በካርታ ቁጥር 02/177/12720/00 በሴሪ ቁጥር 0119905 በግርማ አደራ ገለቱ ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት በላይነህ ሽለመ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የይዞታ ልዩ መለያ ኮድ AA000100803966 በሴሪ ቁጥር R 066118 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይዤዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፊኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ//ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 06 አቶ ወርቅነህ ወ/አማኑኤል እና ወ/ሮ ዝናቧ ሀይሌ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር ---- ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር የካ/250088/2013 የተሰጠበት ቀን 06/04/2013 ዓ.ም የሴሪ ቁጥር 0698741 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቀን 05/06/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው ሙብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የልደታ ክፍለ ከተማ የወረዳ 9 ፋይናንስ ጽ/ቤት በጨረታ ቁጥር ል/ክ/ከ/ወ/9/ፋ/ጽ/ቤት/02/18 አላቂ የቢሮ እቃወች፣ የፅዳት እቃዎች፣ የመኪና ጎማዎች፣ የመድረክ ዲኮርና ሙሉ ሳውንድ ሲስተም፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጥገና እና የህትመት ሥራዎችን በግልጽ ጨረታ መግዛት እና በውል ማሠራት ይፈልጋል፡፡

1. በጨረታ ለመካፈል የሚፈልጉ ተጫራቾች በዘርፉ ህጋዊና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች በገንዘብ ሚኒስተር በእቃ አቅራቢነት ዝርዝር በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡ እንዲሁም በ2018 ዓ.ም በጨረታ መሳተፍ የሚችሉ ለመሆናቸው ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ አካል የተሰጣቸውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ በአጠቃላይ የእቃወች ዋጋ 1% በባንክ በተረጋገጠ (CPO) በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ፋይናንስ ጽ/ቤት ስም በማስያዝ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማቅረብ አለባቸው፡፡

### ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ

(ሎት1):- አላቂ የቢሮ እቃዎች 2000 ብር (ሁለት ሺ ብር )

(ሎት2):- የፅዳት እቃዎች 3000 ብር (ሶስት ሺ ብር)

(ሎት3):- የመኪና ጎማ 10000 ብር (አስር ሺ ብር)

(ሎት4)፡- የመድረክ ዲኮርና ሙሉ ሳውንድ ሲስተም 2000 ብር (ሁለት ሺ ብር)

(ሎት5)፡- የህትመት ሥራዎች 2000 ብር (ሁለት ሺ ብር)

(ሎት6)፡- የትራንስፖርት አገልግሎት 2000 ብር (ሁለት ሺ ብር)

(ሎት7)፡- የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጥገና 2000 ብር (ሁለት ሺ ብር)

4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት በወረዳ 9 ፋይናንስ ጽ/ቤት አራተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 401 በመቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የሚጫረቱባቸውን እቃዎች አይነት ለመለየት የሚያስችል ናሙና ጨረታው ከመከፈቱ ከአንድ ቀን በፊት ማቅረብ አለባቸው ናሙና ለማይቀርብላቸው እቃዎች ስፔስፊኬሽን ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
6. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ በታሸገ ኢንቨሎፕ ኦሪጅናልና ኮፒ በማድረግ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ጨረታ ሲባል በተዘጋጀው ሳጥን ቢሮ ቁጥር 401 ማስገባት አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ 15% ታክስን ያካተተ መሆን አለበት ካላካተተ እንደተካተተ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
8. የጨረታው ሳጥን ማስታወቂያ በወጣበት 10ኛው ቀን ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ተዘግቶ በአስራ አንደኛው ቀን በ3፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቢሮ ቁጥር 401 ይከፈታል፡፡ ዕለቱ በዓል ከሆነ በሚቀጥለው ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
9. በጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅተው ለሚወዳደሩ አምራች ከሆኑ ለአምራችነታቸው የተሰጣቸውን ማስረጃ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን መወዳደር የሚችሉት በተደራጁበት ዘርፍ ብቻ መሆን አለበት፡፡
10. ወረዳው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡

**አድራሻ፡-** ባልቻ ሆስፒታል ከፍ ብሎ ሶሊያና ህንጻ ፊት ለፊት፡፡

**ስልክ ቁጥር፡-** 011-8-69-37-13/011-8-59-54-04

**በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እነ አስካለ ከልክሌ በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ - ቀበሌ- ወይም አዲሱ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር - የካርታ ቁጥር የካ/199398/09 ሴሪ ቁጥር 041133 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ መዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 13 በፍሬወይኒ ብርሃነመስቀል ስም የተመዘገበ ቤት የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥሩ AA000051306934 የተሰጠበት ቀን 23/09/2016 ዓ.ም የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር ወመ10/17076/18 በቀን 23/05/2018 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአየለች ተክለስላሴ ሙሉጌታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የመለያ ኮድ ቁጥር AA000050800236 ሴሪ ቁጥር R 058400 በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት/ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 በ ቄስ አለሙ ፋንታሁን ታፈረ የተመዘገበ ቤት- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ AA000070108719 በሴሪ ቁጥር 046292 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አበበ ሎምባሞ ደርሳቦ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 06 መለያ ቁጥር AA0000611026381098005 የሆነው ሰርተፍኬት በጽህፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ካርታ ሴሪ ቁጥር C 118213 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቸዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ዱባለ ንጉስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ካርታ ቁጥር ቦሌ ቦ/አራ/11/25/1/9/1023/00 በሴሪ ቁጥር 1412157 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ምህረት ፍቅሬ ማርቆስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007469470304 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ የ ኮ/ቀራንዮ ክ/ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር ----- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0086122999 የሚታወቀው ሀና እና ቅድስት ጓደኞቻቸው ሽ/ማ በግብር /ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ---- አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የተሰራበትና ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 01-50 (የተሰራበት) እስከ 251-300 (ያልተሰራበት) ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው ............ /ምዕራብ/ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- ሀና እና ቅድስት ጓደኞቻቸው ሽ/ማ**

## 2ኛ ዙር የጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2018 በጀት ዓመት ለመሥሪያ ቤቱ ስራ አገልግሎት የሚውሉ፡-

| የሎቱ ዓይነት | ሎቱ የሚወክለው ዘርፍ | ለየሎቱ የሚያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ መጠን |
|---|---|---|
| ሎት-1 | የፅህፈት መሣሪያ | 5000 / አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-2 | የደንብ ልብስ | 5000 /አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-3 | የፅዳት እቃ | 5000 /አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-4 | ኮምፒውተርና ፕሪንተር ተዛማጅ | 15000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-5 | ፈርኒቸር | 5000 /አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-6 | መጽሐፍት | 1000 /አንድ ሺህ ብር/ |
| ሎት-7 | የተለያየ የጥገና ስራ | 5000 |
| ሎት-8 | የጀነሬተር ጥገና | የለውም |

በጨረታ ቁጥር 04/018 አወዳድሮ እቃዎቹን እና አገልግሎቶቹን ለመግዛት ይፈልጋል በመሆኑም በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን በጨረታው እንዲሳተፍ ይፈልጋል።

1. ከላይ በዝርዝር ለተጠቀሱት ዕቃዎች አግባብነት ያለው ሕጋዊ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም አዲስ አበባ መስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ለመመዝገባቸው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉና ቫት ተመዝጋቢ የሆኑ እንዲሁም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና ግብር ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት፣ ዘወትር በሥራ ሰዓት ልደታ ክፍለ ከተማ በሚገኘው በዕውቀት ለፍሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመገኘት፣ ለሙሉ ሰነድ የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታውን ሰነድ መውሰድ ይችላሉ። ጨረታው የሚዘጋው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ በወጣ በ11ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ተዘግቶ በ5፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
4. ተጫራቾች እያንዳንዱን ዕቃ እና አገልግሎት የሚሸጡበትን ዋጋ ከነቫቱ መግለጽ አለባቸው፡፡
5. በተራቁጥር 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች እና ከተቋሙ የሚገዙትን ሰነድ ጭምር ኦርጅናሉን ኮፒ በማድረግ በ2 በተለያዩ ፖስታዎች አስገብቶ ኦርጅናልና ኮፒ ብሎ በመፃፍና በማሸግ ሙሉ አድራሻቸውን በመጥቀስ ሰነዱ ላይ በመፈረም ማህተም በመምታት በዕውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛደረጃ ት/ቤት በግዢ ቢሮ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡
6. በጨረታ ሰነዱ ላይ ዋጋ በሚሞሉበት ጊዜ ስተት ከተፈጠረ በአንድ መስመር ሰርዞ ካናቱ ፊርማ በማድረግ ማስተካከል ይፈቀዳል ነገር ግን በፍሉድ ማጥፋት እና ስርዝ ድልዝ ማድረግ አይፈቀድም፡፡
7. ተጫራቹ ዋጋ መሙላት ያለበት በተቋሙ ሰነድ ላይ ብቻ ሲሆን ከዚህ ውጪ ሌላ ሰነድ መጠቀም አይፈቀድም፡፡
8. ከተቋሙ ፍላጎት ወይም ስፔሲፊኬሽን ውጪ በራስ ፍላጎት ማርክ ጠቅሶ ዋጋ መስጠት አይቻልም፡፡
9. በሰነዱ ላይ ዋጋ በሚሞሉበት ወቅት የማይወዳደሩበትን እቃ ዋጋ መሙያ ቦታውን ባዶ መተው አይፈቀድም።
10. ተጫራቾች የተጠቀሱትን ዕቃዎች በሙሉ ወይም በከፊል መጫረት ይችላሉ በተጨማሪም መደበኛ የጨረታ ሰነዱን በተጫራች የሚሞሉትን እና መፈረም ያለባቸውን ቦታዎች በአግባቡ ሞልቶ ፈርሞ ማህተም አድርጎ መመለስ አለባቸው፡፡
11. በጨረታ ለቀረቡት እቃዎች ናሙና (ሳምፕል) የሚገቡ እቃዎች የማወዳደሪያ ሰነዱ ላይ ተጠቅሰዋል።ይሁን እንጂ ናሙና ማቅረብ ላልተቻለባቸው ዕቃዎች፣ የጨረታ ውጤት ከታወቀ በኋላ ናሙናውን በአካል አቅርቦ በማሳየትና ትዕዛዝ ሲሰጥም ገቢ ማድረግ ይኖርበታል።
12. ከላይ በተጠቀሰው መሰረት CPO በልደታ ክፍለ ከተማ እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ስም በማሰራት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
13. አሸናፊ ለሚሆኑ ተጫራቾች የውሉን 10 በመቶ ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡
14. የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ የሚወዳደሩትን የሎት መጠን ያክል ደምሮ በአንድ ሲፒኦ ማሰራት ይቻላል፡፡
15. ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አምራች ካልሆኑ በስተቀር በደብዳቤ የማናስተናግድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**አድራሻ፡-** የቀድሞ 3 ቁጥር ማዞሪያ ቶታል **ስልክ፡-** 011-8346370

**ልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እነ ተናኜ ወልደሰማያት የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ቀበሌ---- ወይም በቀድሞው ወረዳ ----- ቀበሌ ------ የቤት ቁጥር 242 የካርታ ቁጥር 66/4725/00/5230 ሴሪ ቁጥር 077310 እና 077311 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ሴሪ ቁጥር እና በእጃቸው ያለው ካርታ ሴሪ ቁጥር ልዩነት ስላለው በማንኛውም ምክንያት ይገፄዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ለመጀመሪያ ዙር የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ለ2018 በጀት ዓመት ለአካዳሚው አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች እና የአገልግሎት ግዥዎችን ቀጥሎ በቀረበው ዝርዝር መሠረት በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የዕቃዎች/ አቅርቦት ዓይነት | ሎት | ጨ/ ማስከበሪያ | የሎት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የጽህፈት ዕቃዎች ግዥ | 01 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |
| 2 | የጽዳት ዕቃዎች | 02 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |
| 3 | የ"IT & Electronics" ዕቃዎች ግዥ | 03 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |
| 4 | የህትመት አገልግሎት ሥራዎች ግዥ | 04 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |
| 5 | የደንብ ልብስ ግዥ | 05 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |
| 6 | የኮምፒውተር፣ የፕሪንተር እና የፎቶ ኮፒ ማሽን የጥገና አገልግሎት ግዥ | 06 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |
| 7 | የህጻናት መቆያ ግብዓቶች ግዥ | 07 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ--003/2018 |

ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዝርዝር መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በጨረታው እንድትሳተፉ ተጋብዛችኋል፡-

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው፣ በታክስ ባለስልጣን የተሰጠ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፊኬት ቲን ሰርተፍኬት ያለው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ቫት ተመዝጋቢ የሆነ፣ በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጄንሲ ድረ-ገፅ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ እንዲሁም የሚጠበቅባቸውን የግብር ግዴታ የተወጡና በጨረታ ላይ ለመሳተፍ የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ (ክሊራንስ) ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ጨረታ የማይመለስ ብር **200 (ሁለት መቶ)** በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታ ሰነዱን ከአራት ኪሎ አደባባይ ወደ ፒያሳ በሚወስደዉ መንገድ **ዳብር ህንፃ ሶስተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘዉ የአድስ አበባ አመራር አካዳሚ የግዥ ዳይሬክተር 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር-306** በሚገኘው ዘወተር የስራ ሰዓት በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች ከላይ በሰንጠረዡ ላይ በቀረበው የብር መጠን መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ "ለአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ" በሚል አድራሻ በባንክ የክፍያ ትዕዛዝ (C.P.O) ወይም ቅድመ ሁኔታ ባላስቀመጠ የባንክ ዋስትና ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ከሆነ ካደራጃቸው መ/ቤት የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ሰነድ በሁለት በታሸገ ኤንቬሎፕ (ፖስታ) ማለትም **ቴክኒካል** እና **ፋይናንሻል** በሚል የሚያቀርቡ ሲሆን **በአንደኛው ቴክኒካል ኤንቬሎፕ** (ፖስታ) ላይ **ንግድ ፍቃድ፣ ንግድ ምዝገባ፣ ቲን ስርተፍኬት፣ ቫት፣ የአቅራቢነት ምዝገባ፣ ክሊራንስ እና C.P.O)** በአንድ ላይ በሁለተኛው ፋይናንሻል ኤንቬሎፕ (ፖስታ) **የመወዳደሪያ ዋጋችሁን ብቻ** በመሙላት እና የሁለቱንም ኦርጅናል ሰነዶች አንድ አንድ ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቹዋል፡፡ ተጫራቹ ከአካዳሚዉ የወሰዱትን የጨረታ ሰነድ የተጠየቁትን ሞልተዉ እያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተም በምምታት ፖስታውን አሽጋው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጫራቾች በፖስታቸው ላይ የድርጅታቸውን ስም በመጻፍና የሚወዳደሩበትን ሎት በመጻፍ ለዚህ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ የጨረታ ሰነዳቸውን ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ከሎት 1-7ለ ለቀረቡት የጨረታ መክፈቻ ቀን ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ **ለ10 (አስር)** ተከታታይ የስራ ቀናት በአየር ላይ የሚቆይ ሲሆን **በ11ኛው** የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ዕለቱ 4፡30 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
6. የጨረታ ሰነድ መክፈቻ ቀን ላይ ህዝባዊ በዓል (ካላንደር የሚዘጋ) ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
7. አካዳሚው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ይሁን በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስለ ጨረታው ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ቀጥሎ ባለው የስልክ ቁጥር ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።**

**☎0116- 67-33-90**

**አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ**

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 11 ሽፈራው ካኔቦ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA000051102469 የተሰጠበት ቀን 26/01/2012 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር 229/25/18 በቀን 20/01/2018 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርቱ በአጀንዳ 2063 ዓይን



ፎቶ ከገፀ ድር

ስፖርት በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚንቀሳቀስበት እንደመሆኑ አፍሪካ ከዚህ ተጠቃሚ እንድትሆን አጀንዳ 2063 እየሰራ ይገኛል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

አጀንዳ 2063 አፍሪካን ዓለም አቀፍ ተፅዕኖ ፈጣሪ የማድረግ ግብን ያነገበ የ50 ዓመት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ነው። አህጉሪቱ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በማህበራዊ ዘርፎች የበለፀገችና አንድነት ያላት እንድትሆን ግብ ያስቀመጠም ነው። በዚህ ግዙፍ ዕቅድ ውስጥ ስፖርት አህጉራዊ ትስስርን የሚያፋጥን፣ ሰላምን የሚያሰፍንና በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚያመነጭ ስትራቴጂካዊ ዘርፍ ተደርጎ ተለይቷል።

ስፖርት በግጭት ቀጣናዎች ውስጥ እንደ 'ለስላሳ ዲፕሎማሲ' በማገልገል፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን በማጠናከርና ወጣቶችን ከአመፅ ተግባራት ማራቅን አልሞ ወደ ተግባር ስለመግባቱ የሕብረቱ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከስፖርት ኢንዱስትሪው በአህጉሪቱ ለሚገኙ ከ5 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ለሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (ጂዲፒ) እስከ አንድ በመቶ የሚደርስ ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ በአጀንዳ 2063 የስፖርቱ መስከ ቁልፍ የፖሊሲ ግቦች ተደርገው የተቀመጡ ዋና ዋና ግቦች መካከል ተጠቃሽ ነው።

የአፍሪካ ሕብረትም ስፖርት የፖለቲካ ልዩነቶች የማይገቡበት 'ገለልተኛ ሜዳ' በመሆኑ፣ በጦርነትና በትርምስ ውስጥ ለነበሩ ሀገራት ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር እንደ ትልቅ መሣሪያ እየተገለገለበት ይገኛል። በሌላም በኩል ሕብረቱ ስፖርትን 'ፓን-አፍሪካኒዝምን' ለማጠናከር እየተጠቀመበት ሲሆን፣ እንደ አፍሪካ ዋንጫና የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ያሉ መድረኮች ከአምስት ቢሊዮን በላይ ለሚሆኑ የዓለም ሕዝቦች የአፍሪካን አንድነትና ብዝሃነት የሚያሳዩ ትዕይንቶች ሆነው እንዲያገለግሉ እየተሠራ ነው።

የቀድሞው የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ ማሃማት "ስፖርት ለአፍሪካ ሰላም እና ለልማት ሥራዎቻችን እንደ ድልድይ ያገለግላል። አጀንዳ 2063ን እውን ለማድረግ ወጣቶቻችንን በስፖርት ማስተሳሰርና የአህጉሪቱን አወንታዊ ገጽታ ለዓለም ማሳየት አለብን" ማለታቸውም ለዚሁ ነው፡፡

በኬፕ ታውን ዩኒቨርሲቲ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው፣ ስፖርት በአፍሪካ ውስጥ ከፖለቲካዊ ድንበሮች በላይ የጋራ ማንነትን የመፍጠር አቅም አለው። ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ ስፖርት በተለይ በብሔር ማንነት ላይ የተመሰረቱ ግጭቶችን በማለስለስ ረገድ ወደር የሌለው መሣሪያ ነው። አህጉሪቱ የምታሰናዳቸው ስፖርታዊ መድረኮች ደግሞ አፍሪካዊያን በብሔርና በቋንቋ ሳይከፋፈሉ ለአህጉራቸው ኩራት እንዲሰማቸው ያደርጋሉ። ሕብረቱ ስፖርትን እንደ ድልድይ በመጠቀም፣ የፓስፖርት አገልግሎት ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት በስፖርት አማካኝነት የልብ አንድነትን ለማምጣት እየሠራ ነው።

ስፖርትን ከማህበራዊ ፋይዳው ባለፈ እንደ ኢንዱስትሪ የሚመለከተው አጀንዳ 2063፣ ስፖርት በዓለም አቀፍ ደረጃ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚንቀሳቀስበት ዘርፍ እንደመሆኑ አፍሪካ ከዚህ ተጠቃሚ እንድትሆን እየሠራ ይገኛል፡፡ በኬፕታውን ዩኒቨርሲቲም ስፖርት ለልማት (Sport-for-Development) በሚል ርዕስ የተደረጉ የኢኮኖሚ ትንታኔዎች፣ አፍሪካ የስፖርት ኢንዱስትሪዋን በአግባቡ ብትመራ የአህጉሪቱን ጠቅላላ ምርት (ጂዲፒ) በየዓመቱ ከ1 ነጥብ 5 በመቶ እስከ 2 በመቶ መካከል የማሳደግ አቅም እንዳለው ይጠቁማሉ።

አጀንዳ 2063 ስፖርትን ለሰላምና ለአንድነት እንዲውል ያስቀመጠው አቅጣጫ እንዲሳካ አባል ሀገራት በስፖርት ፖሊሲዎቻቸው ላይ ማሻሻያ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እንደዚሁም ዘመናዊ ስታዲየሞችና የስፖርት ማዘውተሪያዎች እንዲገነቡ ማበረታታት፣ ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ኩነቶችን በማስተናገድ የውጭ ምንዛሬና የሥራ ዕድል መፍጠር እና አፍሪካዊያን አትሌቶችና የእግር ኳስ ተጫዋቾች የአህጉሪቱ 'አምባሳደሮች' በመሆን የአፍሪካን ስም እንዲገነቡ ማድረግ የሚሉ ግቦችም ይገኙበታል።

የአፍሪካ ሕብረት ስፖርትን እንደ መደበኛ የፖሊሲ አካል በመቅረጽ ረገድ ላለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት ተጨባጭ ስኬቶችን አስመዝግቧል። እነዚህ ስኬቶች ከስታዲየም ባሻገር በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በዲፕሎማሲያዊ መስኮች የታዩ ናቸው። ሕብረቱ ስፖርትን በግጭት ቀጣናዎች ውስጥ እንደ የእርቅ መሣሪያ በመጠቀም ረገድ ውጤታማ ሥራዎችን ሠርቷል።

በደቡብ ሱዳን እና በሊቢያ በነበሩ የውስጥ ግጭቶች ወቅት፣ ሕብረቱ ከቀጣናዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የስፖርት ውድድሮችን በማዘጋጀት ተፋላሚ ወገኖች በሰላም እንዲነጋገሩ መድረክ አመቻችቷል። በተለይም 'የአፍሪካ ሰላም ቀን' (International Day of Peace) ሲከበር የሚደረጉ የወዳጅነት ጨዋታዎች፣ ወጣቶች ከጠመንጃ ይልቅ እግር ኳስን እንዲመርጡ የማድረግ ትልቅ ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

የአፍሪካ ሕብረት አባል ሀገራት ትልልቅ የዓለም ስፖርታዊ ኩነቶችን በብቃት እንዲያስተናግዱ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ በማድረግ የአህጉሪቱን ገጽታ ቀይሯል። እ.ኤ.አ በ2010 በደቡብ አፍሪካ የተካሄደው የዓለም ዋንጫ የአፍሪካ ሕብረት 'የአፍሪካ ዋንጫ ነው' ብሎ በጋራ የደገፈውና ያስፈጸመው ትልቅ ስኬት ነበር። ይህ ዝግጅት አፍሪካ ግዙፍ መሠረተ ልማቶችን የመገንባትና በዓለም አቀፍ ደረጃ በብቃት የማስተዳደር አቅም እንዳላት ለዓለም ያረጋገጠበት የታሪክ ምዕራፍ ነው።

ሕብረቱ ስፖርት በዘፈቀደ ሳይሆን በሕግና በሥርዓት እንዲመራ የሚያደርጉ ተቋማዊ ሥራዎችን አከናውኗል። 'የአፍሪካ ስፖርት ልማት ፖሊሲ ማዕቀፍ' (Architecture for Sport in Africa) መጽደቁም አንዱ ስኬት ሲሆን፣ ይህም ሀገራት የስፖርት በጀት እንዲመድቡ፣ ዶፒንግን (አበረታች መድኃኒት) በጋራ እንዲከላከሉ እና በስፖርቱ ውስጥ ያለውን ሙስና እንዲታገሉ መንገድ ከፍቷል። እንደ ዋዳ (World Anti-Doping Agency) ካሉ ድርጅቶች ጋር በጋራ መስራቱ የአፍሪካ አትሌቶች በዓለም መድረክ ተዓማኒነት እንዲኖራቸው አድርጓል።

በተለምዶ የወንዶች ብቻ ተደርጎ ይወሰድ የነበረውን ስፖርት፣ ሕብረቱ የሴቶች ማብቂያ መሣሪያ (Empowerment) እንዲሆን አድርጓል። የአፍሪካ የሴቶች እግር ኳስ ዋንጫ (WAFCON) በየዓመቱ በጥራትና በተመልካች ቁጥር እያደገ መምጣቱ የሕብረቱ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ስኬት ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን፣ ይህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካዊያን ሴት ልጆች በራሳቸው እንዲተማመኑና ከስፖርት ባለፈ በትምህርትና በንግድ ውጤታማ እንዲሆኑ አነሳስቷል።

ይህ በየአራት ዓመቱ የሚካሄደው ግዙፍ ስፖርታዊ ኩነት፣ የአፍሪካ ሕብረት አህጉራዊ አንድነትን በተግባር የሚያሳይበት መድረክ ነው። በቅርቡ በጋና የተካሄደው 13ኛው የአፍሪካ ጨዋታዎች፣ ከ50 በላይ ሀገራት የተሳተፉበትና በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ባህላቸውንና ስፖርታዊ ጨዋነታቸውን የተለዋወጡበት ነበር። ይህ መድረክ አፍሪካዊያን በራሳቸው ዳኞች፣ በራሳቸው ሜዳና በራሳቸው ደንብ የሚወዳደሩበት 'የአፍሪካዊያን ኦሎምፒክ' ተደርጎ ይወሰዳል።

ሕብረቱ ሀገራት በስፖርት መሠረተ ልማት ላይ እንዲያተኩሩ ባደረገው ግፊት፣ በአህጉሪቱ የታዩ የኢኮኖሚ ስኬቶች መካከል ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ በአጀንዳ 2063 መሪ ዕቅድ መሠረት ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ስታዲየሞች በአፍሪካ ተገንብተዋል።

የስፖርት ዘርፉ በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ለሚገኙ ከ5 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ የሥራ ዕድል ፈጥሯል። የስፖርት ቱሪዝም ለአፍሪካ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) በአማካይ 0 ነጥብ 5 በመቶ እስከ 1 በመቶ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ የአፍሪካ ልማት ባንክ መረጃ ያመላክታል፡፡

የአጀንዳ 2063 ስፖርት ነክ ግቦችን የሚከታተል የአፍሪካ ሕብረት የስፖርት ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸው 'Status of Sport in Africa' የተሰኙ ሪፖርቶች ቁጥራዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት 85 በመቶ የአፍሪካ ወጣቶች ስፖርትን እንደ 'ብሔራዊ አንድነት' መግለጫ ያዩታል። 60 በመቶ የሚሆኑት በግጭት ቀጣና የሚኖሩ ወጣቶች እንደዚሁ በስፖርት ተሳትፎ ምክንያት ከዓመፅ ተግባራት መራቃቸውን ይገልጻሉ። ባለፉት 7 ዓመታት ሴቶች በስፖርት አመራር ላይ ያላቸው ተሳትፎ 30 በመቶ ጨምሯል።

ለስላሳ ኃይል ማለት አንድ ሀገር ወይም አህጉር በኃይል ወይም በገንዘብ ሳይሆን፣ በባህል፣ በስፖርትና በዕሴቶቹ አማካኝነት የሌሎችን ልብ የመግዛትና ተፅዕኖ የማሳደር አቅም ነው። ለዚህም ነው አጀንዳ 2063 ስፖርትን የአፍሪካዊያን ማንነት መገለጫና የአንድነት ማሰሪያ አድርጎ እየሠራበት የሚገኘው።